የሁሉም አገር ሠርቶ አደሮች ተባበሩ

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መጠናት ያለበት ሳይንስ ነው

# ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ

## ክፍል አንድ

## የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምንነትና ቅድመ ካፒታሊስት ስልተምርቶች

ኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተዓለም መምሪያ
ለውይይት ክበቦች ተዘጋጅቶ የቀረበ
ኅዳር 1973

የሁሉም አገር ሠርቶ አደሮች ተባበሩ

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም መጠናት ያለበት ሳይንስ ነው

# ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ

## ክፍል አንድ

## የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምንነትና ቅድመ ካፒታሊስት ስልተምርቶች

proudly brought to you by
ww.binyamhk.wordpress.com


ኢሠፓአኮ ማዕከላዊ ኮሚቴ የርዕዮተ ዓለም መምሪያ
ለውይይት ክበቦች ተዘጋጅቶ የቀረበ
ኅዳር 1973

# ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፖለቲካ ኢኮኖሚ

## ክፍል አንድ

## የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምንነትና የቀደሙ ካፒታሊስት ስልተ ምርቶች

/ለውይይት ክበቦች ተዘጋጅቶ የቀረበ/




ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. ማዕከላዊ ኮሚቴ

ህዳር ·1973

ቀጽ 16–22–01/73

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገጽ**


መግቢያ ........................................ 1

ምዕራፍ 1 የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምንነት ........................ 9

1.0 የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረቶች ........................ 9

1.1 መሠረታዊ ፍላጎቶች ........................ 9

1.2 ከተፈጥሮ ጋር የሚደረግ ትግል ...... 13

1.3 የማምረት ተግባር ........................ 15

1.4 የፖለቲካ ኢኮኖሚ የጥናት መስክ ....18

ጥያቄዎች ........................................ 20

የሚነበቡ መጻሕፍት ........................................ 21

2.0 የማህበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት ...... 22

2.1 የኢኮኖሚ ሕግጋት ነባራዊ ባሕርይ ... 23

2.2 የሕግጋት ታሪካዊ ባሕርይ ...........26

2.3 የፖለቲካ ኢኮኖሚ መደባዊነትና ወገናዊነት29

ጥያቄዎች ........................................32

የሚነበቡ መጻሕፍት ........................................ 33

3.0 የፖለቲካ ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሳቦች መግለጫ ... 34

3.1 ሥራ ........................................ 35

3.2 የሥራ ተግባሮች ........................ 42

3.3 የሥራ መገልገያዎች ........................ 46

3.4 የምርት መገልገያዎች ........................ 49

3.5 የምርት ኃይሎች ........................51

3.6 የምርት ግንኙነት ........................53

3.7 ስለ ምርት ........................ 55

# ማውጫ

## አርዕስት — ገጽ


ጥ ያ ቄ ዎ ች ........................ 66
የሚነበቡ መጻሕፍት ........................ 67
ምዕራፍ 2 ቅድመ ካፒታሊስት ስልተ ምርቶች ........ 71
1.0 ጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተ ምርት .......... 72
1.1 የህብረተሰቡ አነሳስ ........ 72
1.2 የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች ዕድገት 73
1.3 የጥንታዊ ጋርዮሽ ህብረተሰብ የምርት ግንኙነት ................ 75
1.4 ተፈጥሮአዊ የሥራ ክፍፍል....... 76
1.5 የማህበራዊ የሥራ ክፍፍልና የምርት ልውውጥ አነሳስና ዕድገት ..... 77
1.6 የግል ሀብትና የመደቦች አነሳስ . 79
አጭር ማጠቃለያዎች ........................ 81
ጥ ያ ቄ ዎ ች ........................ 83
የሚነበቡ መጻሕፍት ........................ 83
2.0 የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ........ 84
2.1 የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት አመጣጥና የምርት ግንኙነት ......... 84
2.2 የመንግሥት አመጣጥ .......... 86
2.3 የምርት ኃይሎች ............ 87
2.4 የመደብ ቅራኔዎችና የስልተ ምርቱ መውደቅ ...................89
አጭር ማጠቃለያ ........................ 91
ጥ ያ ቄ ዎ ች........................... 92
የሚነበቡ መጻሕፍት ........................ 92
3.0 የፊውዳሉ ስልተ ምርት ............... 93

# ማውጫ

ጀገ

አ ር ዕ ስ ት | ገጽ


3.1 የፊውዳሉ ስለ ትምርት አመጣጥ .... 94

3.2 የፊውዳል ህብረ ተሰብ ምርት ግንኙነቶች96

3.3 የምርት ኃይሎች ዕድገት በፊውዳሉ ህብረ ተሰብ ..................102

3.4 የካፒታሊዝም በፊውዳሉ ሥርዓት ማህ ፀን ውስጥ መፀነስ ...........104

3.5 የመጀመሪያ ደረጃ ካፒታል ክምችት .106

3.6 የፊውዳሉ ሥርዓት ውድቀት ......108

አጭር መደምደሚያ ....................... 111

ጥ ያ ቄ ዎ ች ....................... 113

የሚነበቡ መጻሕፍት ................... 114

የቃላት መግለጫ ...................... 115

# መግቢያ

ይህ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም የማስተማሪያ ጽሑፍ ኢሠፓአኮ ያለ ቱክ ለሰና ያለተበረዘ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ርዕዮተዓለም በሰፊው ሕዝብ ውስጥ ለማሠራጨት ባለበት ኃላፊነት መሠረት ለውይይት ክበቦች የተዘጋጀ ነው። ውይይት ክበቦች ቀደም ሲል የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ ማስተማሪያ መድረክ ቢሆኑም በውይይት ክበቦች መካከል ከአንዱ ማዕከል የሚመነጭ አንድ ዓይነት ትምህርት ይሰጥባቸው ስላልነበረ የተዘበራረቀ ሁኔታ ታይቶባቸዋል። የአጠናኑም ዘዴ እንዲሁ የተዘበራረቀና ውል ያጣ ነበር። ይህንን ድክመት አስወግዶ ትምህርቱን በተስተካከለ መንገድ ለመስጠት ይህ የማስተማሪያ ጥራዝ የመጀመሪያ ሙከራ ነው።

የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ ሦስት የማይለያዩና የሚደጋገፉ ዘርፎች አሉት። እነዚህም ፍልስፍና፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚና ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ናቸው። እነዚህ ሦስት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ሳይንስ ዋና ዋና ዘርፎች እጅግ በጣም ሰፊና ውስብስብም ናቸው። የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንስ በሚገባ ለማወቅ ሦስቱን ዋና ዋና ዘርፎች ጠንቅቆ መገንዘብ ያሻል። የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንስ ውል ባለው መልክ ለመጨበጥ እንዲቻል ከማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መጀመሩ ይመረጣል። ከፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መጀመሩ ለምን ተመረጠ?

- የኅብረተሰብ ዋነኛ መሠረት ቁሳዊ ምርት በመሆኑና የቁሳዊ አመራረትም ሂደት ግንዛቤ የሚያገኘው በኢኮኖሚ ስለሆነ የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይንስ ለማጥናት ከፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መጀመሩ ጠቃሚ ስለሚሆን፣

- ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሠራተኛው ሕዝብ ከልምዱ ያገኛቸውን ተጨባጭ ሁኔታዎች በማንሳት በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ ውስጥ የብዝበዛን መንስዔ ገሃድ በማውጣት ሠርቶ አደሮች ከብዝበዛ ነፃ የሚወጡበትን መንገድ ሊያሳያቸው ስለሚችል፣

- ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሠራተኛው ሕዝብ በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆንበትን የማምረትንና የክፍፍልን ሕግጋት የሚያጠና በመሆኑ ከዕለት ዕለት ኑሮው ጋር በተያያዘና ቀለል ባለ ሁኔታ ሊቀርብለት ስለሚችል፣

- ሠራተኛው ሕዝብ በተጨባጭ ከሚያየው ሁኔታ መነሳት ደግሞ ለንድፈ-ሃሳብ ዕውቀት አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥርለት ከቀላል ወደ ከባድ ከተግባር ወደ ንድፈ ሃሳብ እንደገና ወደ ከፍተኛ ተግባርና ከፍተኛ ንድፈ ሃሳብ እንዲያድግ የመጀመሪያውን እርምጃ ሊሰጥ ስለሚችል ነው።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በአንድ በተወሰነ የታሪክ ወቅት ውስጥ የሚከናወንን የምርትና የክፍፍልን ሂደትና ይህ ሂደትም የሚመሠረትባቸውን ኢኮኖሚያዊ ሕግጋት የሚያጠና ሳይንስ ነው፤ በዚህ ሳይንስ አማካኝነት በምርት ሂደት ውስጥ የሚከሰቱት ነገሮች በመካከላቸው ያለው ውስጣዊ መስተጋብርና መያያዝም ይጠናል። አንዱ መደብ በሌላው ወዝ የመደለቡ፣ ሌላው መደብ ደግሞ ሌት ተቀን እየማሰነ ለድኅነት የመዳረጉ ምስጢር በዚህ ሣይንስ አማካኝነት ይፋ ይወጣል። ሠርቶ አደሮች ከብዝበዛና ጭቆና ነፃ የሚወጡበትን መንገድ ያመለክታል። ብዝበዛና ጭቆና በሌለበት ኅብረተሰብም ውስጥ የሠራተኛውን ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቀው የኢኮኖሚ ዕድገት እንዴት መገንባት እንዳለበትም ትክክለኛውን መንገድ ይጠቁማል።

ሰዎች ነባራዊ ሕግጋትን እንደፈለጓቸው ሊቀይሯቸው የማይችሉ ቢሆንም እነዚህን ሕግጋት በሚገባ ተገንዝበው ፍላጎታቸውን እንዲያገለግሉ ማድረግ ግን ይችላሉ። በኅብረተሰብ ውስጥ የሚከናወኑትን ክስተቶች ምንነት ለመረዳትና ሂደቱንም በሚገባ ለመገንዘብ ደግሞ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ማወቅ ያስፈልጋል። የኅብረተሰብን የወደፊት ዕድገት በማመልከት ረገድ የተብራራ ሳይንሳዊ መልስን ይሰጣል።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የኅብረተሰብ ታሪካዊ ሳይንስ ነው። ታሪካዊ በመሆኑም በየዘመኑና በየዕድገት ደረጃው ህብረተሰብ ያለፈበትን የታሪክ ሂደት፣ የአሁኑን ይዞታና የወደፊት ዕድገቱንም አቅጣጫ ያመለክታል። በአንድ በተወሰነ ሥልተ ምርት ውስጥ የቁሳዊ ሀብት አመራረትን፣ ይህ አመራረት የሚገዛባቸውን ቁጠባዊ ሕግጋትና ውስጣዊ ባሕርይውን ገልጦ የማሳየት ተግባር የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተግባር ነው። የኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሕግጋት ነባራዊ ናቸው። እነዚህ ሕግጋት ከሰው ፍላጎት ውጭ በቁሙና በተወሰኑ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ላይ ተመሥርተው የሚመነጩና ተግባራቸውንም በዚህ መሠረት የሚያከናውኑ ናቸው። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ ውስጥ ነባራዊዎቹን የኢኮኖሚ ሕግጋት የመጠቀም ጉዳይ መደባዊ ይዞታና መልክ ያለው ነው። በአንድ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ ተራማጅ መደብ እነዚህ ኢኮኖሚያዊ ሕግጋት የኅብረተሰቡን ዕድገት እንዲያፋጥኑ አድርጎ ሲጠቀምባቸው ገታቹ መደብ ግን ተግባሩን በተቃራኒው ያከናውናል። እነዚህ ኢኮኖሚያዊ ምስጢሮችና የሚያስከትሉት ውጤት በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አማካኝነት ይገለጣሉ።

እያንዳንዱ ስልተ ምርት የራሱ የሆነ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ያለው ነው። ይህ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ ደግሞ የዚያን ስልተ ምርት ሕልውና ከመተርጎም በላይ ዋና ዋና ገጽታዎችንና የዕድገት ሂደቱንም የሚወስን ይሆናል።

የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዓይነተኛ ተግባርም ይህን ሁኔታ ገልጦ ማሳየት ነው። ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መጀመሪያ በምርትና በክፍፍል ተግባር ውስጥ እያንዳንዱ ደረጃ የሚጋዘበት ዝግመታዊ ሂደት የሚመሠረትበትን ነባራዊ ሕግ ይመረምራል። በዚህ ላይ በመመሥረትም አጠቃላዩ ምርትና የክፍፍል ተግባር የሚመራበትን ነባራዊ ሕግ ያሳያል።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በታሪክ የሚታወቁትን የጥንታዊ የጋርዮሽ ኅብረተሰብን የባሪያ አሳዳሪውን፣ የፊውዳሊዝምን፣ የካፒታሊዝምንና የሶሺያሊዝምን የምርት ግንኙነቶች ያጠናል። የጥንታዊው የጋርዮሽ ኅብረተሰብ ቅድመ መደብ ኅብረተሰብ

ሲሆን የባሪያ አሳዳሪው የፊውዳሉና የካፒታሊስት ኅብረተሰቦች ግን በሠራተኛው መበዝበዝና ባርነት ላይ የተመሠረተ የበዝበዛ ሥርዓቶች ናቸው። የሶሺያሊስት ኅብረተሰብ ደግሞ ከሰዎች መበዝበዝ ነፃ የሆነና በንፁህ ወንድማማችነትና መግባባት ላይ የተመሠረተ ኅብረተሰብ ነው። በነዚህ የተለያዩ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ ማኅበራዊ አመራረት የሚያልፍባቸው ውስብስብ የዕድገት ደረጃዎች በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አማካኝነት ይመረመራሉ። ከቀላል ወደ ውስብስብ ያደገው ማኅበራዊ አመራረት ለሶሺያሊስት ስልተ ምርት ደለ አዶሬጊነት ሁኔታዎችን እንዴት እንደሚያመቻች የሚጠናው በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አማካኝነት ነው። ከዚህም በላይ የሶሺያሊዝም ኢኮኖሚያዊ ሕገጋት፣ የሶሺያሊስት ኅብረተሰብ የሚመነጭበት ኢኮኖሚያዊ መሠረትና ሶሺያሊዝም ወደ ኮምዩኒዝም የሚያደርገው ከፍተኛ የዕድገት ሽግግር በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አማካኝነት ይጠናል።


የሰዎችን፣ የኅብረተሰብንና የመደቦችን ፍላጎቶች የሚነኩ እውነተኛና ሕያው ጥያቄዎች የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሠረታዊ ጥያቄዎች ናቸው። ይህ በመሆኑም ምክንያት ለሁሉም መደቦች የጋራ ጥቅም የሚውል አንድ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አይኖርም። በመሆኑም ለተለያዩ መደቦች ፍላጎቶች የቆሙ የተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚዎች እንዲኖሩ የግድ ነው። የቡርዧው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ፣ የሠራተኛው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ከላይ የጠቀስነውን የሚያረጋግጡ ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው።

በካርል ማርክስና በፍሪዴሪክ ኤንግልስ አማካኝነት የተቀረው ማርክሳዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ኋላም በሌኒን አማካኝነት ዳብሮና ሰፍቶ ሶሺያሊዝምን በመገንባት ረገድ ለሚነሱ ወሳኝ ጥያቄዎች መፍትሔ ይሰጣል።

ሠራተኛው መደብና ሌሎችም ሠርቶ አደሮች ከካፒታሊዝምም ሆነ ከማንኛውም ዓይነት ጭቆና ነፃ እንዲሆኑ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን በትግል መሣሪያነት መጠቀም አለባቸው። ይህ ሣይንስ ይጨበጥ ዘንድ ግን ያላሰለሰ ጥረትንና ያልተቆጠበ ጥናትን ይጠይቃል።


ይህ የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ማስተማሪያ ጥራዝ የተዘጋጀው እስካሁን በተገኙ ልምዶች ላይ ተመሥርቶ ቢሆንም ወደፊት ከውይይት ከበቦች ተሳታፊዎች፣ ከአስተማሪዎችና ከካድሬዎችም ተሳትፎ በሚገኘው የላቀ ልምድ ላይ ተመሥርቶ ሊዳበር የሚችል በመሆኑ እያንዳንዱ በዚህ ጥራዝ ተጠቃሚ የሆነ ሁሉ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይጠበቅበታል።

ኢሠፓአኮ



# ምዕራፍ 1

## የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምንነት



## ምዕራፍ 1

## የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምንነት

ይህ ምዕራፍ፣ ሦስት ዐበይት ክፍሎችን ይዟል። እነዚህም የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረቶች፣ የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋትና የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረታዊ ጽንሰ ሃሣቦች ናቸው።

የፖለቲካ ኢኮኖሚ የማምረትንና የማከፋፈልን ተግባር የሚያጠና ሳይንስ ሲሆን ማምረት፣ ማከፋፈል ለምን? ለማን? እንዴት?.. ብለን ስንጠይቅ የሰውን ፍላጎት ለማርካት፣ ለሰው ... የሚለውን መልስ እናገኛለን፤ ይህ በመጀመሪያው ክፍል የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረቶች በሚለው ውስጥ ይብራራል። በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ይህ ሳይንስ የሚያጠናቸው የኢኮኖሚ ሕግጋት ምን እንደሆኑና አጠቃላይ ባሕርያቸውን እንመለከታለን። በምዕራፉ የመጨረሻ ክፍል ከፖለቲካ ኢኮኖሚ ዐበይት ጽንሰ ሃሣቦች ውስጥ መሠረታዊ የሆኑትን ዘርዘር አድርገን እናጠናለን።

### 1.0 የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረቶች

#### 1.1 መሠረታዊ ፍላጎቶች

"ሰው ስለፖለቲካ ስለሳይንስ ስለሥነ ጥበብ ስለ ሃይማኖት ወዘተ... ከማሰቡ በፊት በመጀመሪያ መብላት መጠጣት መጠለያና ልብስ ማግኘት ይኖርበታል።"/ማርክስና ኤንገልስ ምርጥ ሥራዎች፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 162።/

ሰው መሠረታዊ ፍላጎቶች አሉት፣ እነዚህን ፍላጎቶችን በመጠኑም ቢሆን ማሟላት ወይም ማርካት ግዴታው ነው፤ ይህንን ካላደረገ ወይም ካላሟላ በሕይወት ለመኖር ወይም ሰው ለመሆን አይችልም።

እነዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶች ለመሆኑ ምንድናቸው? ከራሳችን ብንጀምር ወይም ብንነሳ በቀላሉ ልንገነዘባቸው እንችላለን። እንደኛው መሠረታዊ ፍላጎት ምግብ× ነው፣ ካልበላን ካልጠጣን ለመኖር አንችልም። እርግጥ ሰው ያለምግብ ሁለት ሦስት ቀን ከዚያም አልፎ ሣምንት ወይም ከዚያም በላይ ሊኖር ወይም ሊቆይ እንደሚችል ይነገራል። እንደዚሁ ያለውሃም የተወሰኑ ቀናት ይቆያል ይባላል። ይህ አባባል ታዲያ ሰው ከሆነ በኋላ እንጂ መጀመሪያውኑ ከሰውነት ደረጃ ከመድረሳችን በፊት ሊሆን የሚችል አይደለም። ሰው ገና ከጥንሱ ጀምሮ መመገብ ይኖርበታል፣ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ እንደሁኔታውና እንደ ዕድገት ደረጃው በምግብ ኃይል ነው የሚኖረው። እንዲያውም ይህ የምግብ አስፈላጊነት በአጠቃላይ ሕያው ለሆነ፣ ሕይወት ላለው ማናቸውም ነገር አስፈላጊ መሆኑን እንገነዘባለን። በመሠረቱ መመገብ፣ አንዱን የቁስ አካል ክፍል /አንዱን ነገር/ ወደሌላ የመለወጥ ሂደት ነው። ለምሳሌ እንጀራ፣ ሥጋ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ... ስንበላ ውሃ ስንጠጣ ከዚህ ውስጥ ገሚሱ ወደሰውነታችን/የሰው ደም ሥጋ.../ ይለወጣል፣ ሌላው ቆሻሻ ሆኖ /ሽንት፣ ዓይነ ምድር ላብ.../ ይወጣል። አዲስ ነገር ይሆናሉ። ሆኖም ይህ አጠቃላይ አባባል እንደነገሩና እንደሁኔታው የተለያዩና ውስብስብም ነው። ይህ የመለወጥ የማዋሃድ አዲስ ነገር የመፍጠር ሂደት በአጠቃላይ በእጽዋት፣ በእንስሳትና በሰው ያለና የሚከናወን ሲሆን በመካከላቸው ግን ከፍተኛ ልዩነት አለ።/

የሰው የምግብ ፍላጎት ከአንድ ደረጃ ቢነሣም ብዙ መልክና ቅርጽ አለው፣ የምግብን ፍላጎት ለማርካት ልዩ ልዩ ነገሮችን እንመገባለን፣ በተለያዩ ቅርጾች ልዩ ጣዕም አበጅተንላቸው ወይም እንዲኖራቸው አድርገን እንመገባለን። እርግጥ ይዘታቸው ማለትም ከንጥረ ነገሮችና

---

×ምግብ ስንል መጠጥንም የሚያጠቃልል መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ከመጋቢነታቸው ለሰውነታችን ከሚሰጡት አገልግሎት አንፃር ውስን ናቸው። ገንቢነታቸው አጠንካሪነታቸው ጠጋኝነታቸው አንቀሳቃሽነታቸው ወዘተ... ሊሰፋ የሚችለው ቀስ በቀስና የዕድገት ደረጃን ተከትሉ ነው። ሰው ለመኖር የምግብ ፍላጎትን ማሟላት ይኖርበታል። ይህንንም ፍላጎትን ለማሟላት ከተፈጥሮ ጋር በመታገል ይበልጥ ስብእናውን እያዳበረና እያሟላ ይሄዳል። መጀመሪያውኑም ከእንስሳነት ዓለም የወጣውና ሰው ለመሆንም የበቃው ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ አካባቢውንና ራሱንም በመለወጥ ስለሆነ በዚሁ መንገድ ይቀጥላል።

የተሟሉ የምግብ ዓይነቶች የሚያስፈልገው የተሟላ ጤናማነት ለማግኘትና በሥራ እንቅስቃሴ በጥናትና ምርምር የተፈጥሮን አስከፊ ገጽታዎች ለመለወጥና ለሰው ሕይወት ተስማሚና አስደሳች ለማድረግ ነው። የምንመገባቸው የምግብ ዓይነቶች ኃይል ጤና ይሰጡናል፤ በዚህ የበለጠ የሥራ እንቅስቃሴ በማድረግ ምርታማነታችንን ለማሳደግ አካባቢያችንን ማለትም ተፈጥሮን የበለጠ ለመቆጣጠር ለማወቅ ለማድነቅ እንችላለን፤ በዚህ ወደፊት በገፋን ቁጥር ስብእናችን የበለጠ እየተሟላ ይሄዳል። ይህ እንግዲህ በአጠቃላይ የሰው ለመኖር የምግብ ፍላጎትን ማሟላት ዓላማ ወይም ምክንያት ሲሆን በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ አብዛኛው የበዝባዥ መደብ አባላት የሚኖሩት ለመብላት ነው ለማለት ይቻላል። እነዚህ የብዙኃኑን አምራች የሥራ ውጤት በመዘረፍ ቁጭ ብለው ይንደላቀቃሉ፤ የቅንጦት ሕይወት ይቁጫሉ ወይም ሥጋቸውን ያደልባሉ እንጂ የሰው መሠረትና ምክንያት የሆነውን ተግባር አያከናውኑም።

ሌሎች የሰው መሠረታዊ ፍላጎቶች ልብስና መጠለያ ናቸው፤ ሰው ያለእነዚህ በሕይወት ለመኖር ቢችልም ሙሉ ስብእና አለው ለማለት ግን ከቶ አይቻልም። ልብስም ሆነ መጠለያ የሚያስፈልገን በመሠረቱ ከተፈጥሮ ልዩ ልዩ ሁኔታዎችና ድርጊቶች ለምሳሌ ከብርድ ከሙቀት ከልዩ ልዩ አደገኛ

ለመጠበቅ ነው።

አውሬዎች ተውሳኮችና ከመሳሰሉት ራሳችንን ሕይወታችንን በእነዚህ አማካይነት ሰው የራሱን አካባቢ ይመሠርታል፣ ይህ የሰው አካባቢ ደግሞ ከተፈጥሮ አካባቢ ወይም ከእንስሳት አካባቢ የተለየ ነው። እንስሳት የተለያዩ የአየር ጠባይና አካባቢ ቢያስፈልጋቸውም በመሠረቱ በአጠቃላይ በተፈጥሮ አካባቢ ውስጥ ይኖራሉ። ራሳቸውን ከተፈጥሮ አስማምተው በተለያዩ ተፈጥሯዊ አካባቢዎች ውስጥ ይኖራሉ። የሰው ግን የተለየ ነው። ተፈጥሮን ለራሱ እንደሚስማማ አድርጎ በተለየ ሰብዊ አካባቢ ነው የሚኖረው፣ ይህንንም አካባቢ የሚፈጥረው ከላይ በተመለከቱት ልብስና መጠለያዎች አማካይነት ነው።

ሰው በረጅምና ውስብስብ የዕድገት ሂደት ውስጥ እነዚህ ፍላጎቶችን የሚያሟላው እንደ ዕድገት ደረጃው ነው። ቀደም ብሎ ከእንስሳነት ዓለም ሲወጣ ቅጠላ ቅጠልን የአውሬ ቆዳና ፀጉርን የአካሉ መከለያ የብርድና የሙቀት መከላከያ በማድረግ ሲጠቀም በመጠለያ በኩል ደግሞ የዛፍ ቅርንጫፍና ግንድ፣ ዋሻ፣ ጎጆና የመሳሰሉት አገልግለውታል። እነዚህ እየተሻሻሉ መጥተው ዛሬ ሰው የሚለብሳቸውን የልብስ ዓይነቶችና የሚኖርባቸውንና የሚሠራባቸውን ሕንፃዎች ስንመለከት እነዚህን መሠረታዊ ፍላጎቶች በማሟላት በኩል ሰው ከምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ እንገነዘባለን።

ሰው እነዚህን ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚታገለው የበለጠ ጤናማና ምርታማ በመሆን አካባቢውን ተፈጥሮን በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ዕውቀትን ለማዳበር ብሎም የሰውን ባሕርይ ከፍ ለማድረግ ነው። ይህም ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴን የሚጠይቅ ሲሆን ሰፊው አምራች ሕዝብ የደከመበትን እየበዘበዙ በቅንጦት ዓለም ውስጥ የሚኖሩት የገዢ መደቦች ግን ሚናቸው የተባይ ነው። የእነዚህ ተባዮች መወገድ የሰው ልጅ እነዚህን ፍላጎቶችን የበለጠ ለማሟላት የሚያደርገውን ጥረት ፍሬያማ እንደሚያደርገው እሙን ነው።

ለማጠቃለል የሰው መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት ከሕልውናው ጋር የተያያዘ ነው፣ የሰውነት ባሕርዮን ለመቀዳጀት የቻለው እነዚህን እንደ ዕድገት ደረጃው የበለጠ እየተሟሉ የሚሄዱትን ቁሳዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ባደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው:: እነዚህን ለማሟላት በሚያደርገው ትግል ተፈጥሮን የበለጠ ለማወቅና በመቆጣጠር በመለወጥ ሰብእናውን ያሟላል:: ወደፊት በሰፊው እንደሚብራራው ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያደረገውና የሚያደርገው ትግል ሰብእናውን ሊያገናጽፈው የቻለውና ወደፊትም የበለጠ ሊሟላ የሚችለው ትግሉ የተናጠል ሳይሆን ማኅበራዊ በመሆኑ ነው፣ ስለዚህ የሰው ፍላጎቶች መሟላት በሙሉ የማኅበራዊ ትግልና እንቅስቃሴ ውጤት ነው::

## 1.2 ከተፈጥሮ ጋር የሚደረግ ትግል

ሰው መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከተፈጥሮ ጋር ትግል ያደርጋል ብለናል፣ እንዴት ነው የሚታገለው? በምንድነው የሚታገለው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይሆናል:: ከእነዚህ ጥያቄዎች በመነሳት ከተፈጥሮ ጋር የሚደረገውን ትግል ቀረብ ብለን ለማየት እንሞክራለን::

ሰው ራሱ የተፈጥሮ አካል ወይም ቁራጭ ነው፣ የቁስ አካል ከፍተኛው የዕድገት ደረጃ ነው:: ሰው ራሱ የተፈጥሮ አካል ወይም የቁስ አካል ክፍል ሆኖ ከተፈጥሮ ጋር ይታገላል:: ከላይ እንደተመለከተው ይህንን ትግል የሚያካሂደው መሠረታዊ የሆኑትን ፍላጎቶችን ለማርካት ወይም ለማሟላት ነው:: ሕያዋን የሆኑት ሌሎቹ የተፈጥሮ ክፍሎች እንስሳትና እጽዋት ራሳቸውን ከተፈጥሮ ጋር ያስማማሉ እንጂ ከተፈጥሮ ጋር ታግለው ለራሳቸው እንደሚስማማቸው አድርገው ለመለወጥ አይችሉም፣ ሰው ግን በሚሊዮን በሚቆጠሩ ዓመታት የዳበረው አዕምሮው የማሰብ ችሎታውን ከፍ ስላደረገው ተፈጥሮን ለራሱ እንደሚስማማው አድርጎ ለመለወጥ መቻሉ ከእንስሳትና እጽዋት ፍጹም ልዩ አድርጎታል::

በሚቀጥሉት ክፍሎች በሰፊው እንደሚብራራው ሰው የቻለው ተፈጥሮን ለራሱ ተስማሚ ለማድረግ /ለመለወጥ ሲሞክር/ የበቃው በአራት እግሮች እንደ እንስሳ እንዝብስ ከመሄድ ተላቆ በሁለት ቀን የፊት እግሮቹን ነፃ በማውጣትና ቆሞ ለመሄድ ስለቻለ ነው:: ይህ ቆሞ መሄዱ ረጅም ጊዜ የፈጀ ቀስ በቀስ የተከናወነ ነው:: ነፃ በወጡት እግሮቹ ኃይል እጅ በሆኑት አማካይነት እንደ ድንጋይ የመሳሰሉትን በማሾል ግርድፍ መሣሪያዎችን እየሠራ በእነዚሁ ሥራ ሥሮችን እየቆፈረ አውሬዎችን እየገደለ መመገብ ጀመረ:: በዚሁ ሂደት ውስጥ እሳትን በማግኘት ለምግብ ማብሰያና ለልዩ ልዩ ተግባሮች ማከናወኛ ተጠቀመበት:: ቀስ በቀስ እንደ መዳብ እንደ ብረት ያሉት ማዕድናት በመጠቀም መሣሪያዎችን አሻሻለ:: በዚህ ውስብስብና አያሌ ዘመናት በፈጀው ሂደት ውስጥ በእጆቹ የሚያደርገው እንቅስቃሴ አንጎሉን እያንቀሳቀሰው አእምሮውን እያዳበረው ንግግር፣ ቋንቋ፣ በማኅበር መሥራት፣ በማኅበር ማምረት እየዳበረና እየተስፋፋ መጣ::/

በአጭሩና በጣም በአጠቃላይ ሰው ከእንስሳነት ዓለም የወጣው በዚህ ሂደት ውስጥ አልፎ ሲሆን የሰውነቱ /ሰው የመሆኑ/ መሠረት ሥራ ሆኖ እናገኘዋለን:: ለዚህም ነው ታላቁ ቁስ አካላዊ ፈላስፋ ፍሬዴሪክ ኤንግልስ ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው ያለው:: ሥራ የሚለው ቃል ያዘለው ጽንሰ-ሃሳብ ወደፊት በሰፊው የሚብራራ ሲሆን እዚህ ጠቅለል ለማድረግ ያህል ሰው መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት የአካባቢውን ተፈጥሮ በሥራ እንቅስቃሴ ይለውጣል:: በዚህ ሂደት የተፈጥሮን ወይም የቁስ አካልን ልዩ ልዩ ክፍሎች ምንነትና ባሕርይ ያውቃል ይገነዘባል፣ በመሠረቱ የዕውቀታችን ምንጭ ይህ ነው:: አዕምሮአችንና ሐሳባችን የተገኙት ከዚህ ሂደት ውስጥ ነው::

## 1.3 የማምረት ተግባር

ሰው በሥራው ለፍላጎቱ ማሟያ ሲያመርት ተፈጥሮን ይለውጣል፣ ሰው በተፈጥሮ ላይ ተጽእኖ በማድረግ/ለምሳሌ በመስኖ ውሃ ደረቅን ሥፍራ በማለምለም፣ ጫካ በመመንጠር ወይም ዛፍ በመትከል.../ ወይም ካንድ ሁኔታ ወደሌላው በመለወጥና ለፍላጎቶቹ ማርኪያ በማድረግ የሚያገኘው ውጤት ምርት ተብሎ ይጠራል። ምርት የሰው የሥራ ውጤት ነው። ለልዩ ልዩ የሰው ፍላጎት ማሟያ የሚያገለግል ነው፣ ስለዚህም መሠረታዊ ነገር ነው። ሰው መሬትን አርሶ እህል አትክልት ፍራፍሬ ወዘተ... ያመርታል፣ እንስሳትን ተንከባክቦ መግቦ አራብቶ ሥጋ ወተት ቅቤ ወዘተ... ያመርታል፣ ማዕድናትን ፈልጎ ቆፍሮ ለዩ ለዩ መሣሪያዎችን፣ ቁሳ ቁሶችን ያመርታል። የማምረት ተግባር አጅግ በጣም ሰፊ መሆኑን በቀላሉ እንገነዘባለን፣ ይህ ሁሉ ተረትከላይ ከፍ ብለን ካየናቸው የሰው ፍላጎቶች ማሟላት ጋር የተያያዘ ነው።

የማምረት ተግባር የማያቋርጥና የማይቆም ሂደት ነው፣ ለምን ቢባል የሰው ፍላጎት ዘወትር ሳያሰልስ መሟላት ያለበት ስለሆነ ነው፣ መብላት መጠጣት መልበስ መጠለልና ሌሎችም ፍላጎቶች ወቅታቸውንና ጊዜያቸውን ጠብቀው መሟላት አለባቸው፣ ሙሉ በሙሉም ባይሆን ለመኖር ያህል መሟላት ይኖርባቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ፍላጎቶች በየጊዜው እየጨመሩ፣ እያደጉ የሚሄዱ ናቸው። ያለውንና አዲስ ብቅ ብቅ እያለና እየተከሰተ የሚሄደውን የሰው ፍላጎት ለማርካት ምርት በዓይነት በመጠንና በጥራት ይመረታል፣ በሌላ አባባል ፍጆታ /ኮንሰምሽን/ ማለትም ፍላጎቶችን ማርካት የማምረትን ተግባር ያንቀሳቅሳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ማምረት ከማከፋፈል ጋር የተያያዘ ነው፣ የተመረተው ለኅብረተሰቡ አባላት መከፋፈል ወይም መዳረስ አለበት። እርግጥ ይህ ውስብስብና እንደ ስልተ ምርቱ የሚለያይ ነው፣ ይህንንም

ጉዳይ ወደፊት በዝርዝር እንመለከታለን። ሆኖም የምርት መገልገያዎች የግል ንብረት በሆኑበት ኅብረተሰብ /ባሪያ፣ ፊውዳል፣ ካፒታሊስት/ ውስጥ የምርት ክፍፍል የተዛባ ነው፣ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የምርት ተገበሮች /መሬት እንጨት ማዕድን ውሃ.../ በግል ንብረት የያዙት መደቦች አባላት በድሎት ሲኖሩ ሌሎች ግን ከባድ ችግር ውስጥ ይኖራሉ። የማምረቻ መሣሪያዎችና የምርት ተገብሮች የወል ወይም የጋርዮሽ በሆነ ኅብረተሰብ ውስጥ ምርት በሚገባ ይከፋፈላል፣ ለምሳሌ በጥንታዊ ጋርዮሽ ከኅብረተሰቡ ዕድገት ዝቅተኛነት የተነሣ የምርት መጠንና ዓይነት አነስተኛ ቢሆንም ያው ለኅብረተሰቡ አባላት እኩል ይከፋፈል ነበር፣ በኮምዩኒስት ኅብረተሰብ ግን የሚመረተው በብዛትና በጥራት ስለሚሆን እያንዳንዱ ሰው የፍላጎቱን ያህል ይወስዳል።/

ለምርት ማደግና ለማምረት ተግባር መስፋፋት አንደኛው ምክንያት የምርት ለውውጥ ነው። አንድ ግለሰብ የሚያስፈልጉትን ነገሮች በሙሉ ሊያመርት አይችልም። ስለዚህ የምርት ለውውጥ ይጀመራል። የምርት ለውውጥ ስንል አንዱ ከፍጆታው በይበልጥ ወይም ትርፍ ያመረተውን ለምሳሌ እህል ወይም ልብስ ወይም ሌላ ነገር ለሌላው ወይም ለሌሎች በመስጠት ለእርሱ አስፈላጊ የሆነውን አንድ ዓይነት ቁሳቁስ ማግኘት መቻል ማለት ነው። ለምሳሌ አንዱ እህል ብቻ ከሚያስፈልገው በላይ ያመርትና ከሌላው ልብስ ብቻ ከሚያመርተው እህል ሰጥቶ ልብስ ይወስዳል፣ ይህ በሰፊው ሊታይና ሊበዛ ይችላል። የምርት ለውውጥ መሠረት ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ነው፣ ቀደም ብሎ እንዳመለከትነው አንድ ሰው ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ብቻውን ለማምረት ስለማይችል የግድ አንድ ሰው የተወሰነ የሥራ መስክ ሌላው ወይም ሌሎች በተለያዩ መስኮች ተሰማርተው ማምረትና ምርትን መለዋወጥ ይገባቸዋል። ወደፊት እንደሚታየው ይህም የምርት ለውውጥ ተግባር ከትንሽ ወይም ዝቅተኛ ደረጃ ተነስቶ ቀስ በቀስ እያደገ የመጣ ነው። ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል የሰዎችን የማምረት

ችሎታ ከፍ ያደርገዋል፣ የተለዩና የተሻሉ መሣሪያዎችን ያስገኛል፣ በዚህ አኳኋን ምርት ያድጋል። ይህ ሁኔታ ወይም ድርጊት የበለጠ የሥራ ክፍፍልን ያስከትላል፣ የምርት ለውውጥም በዚሁ ሂደት ይዳብ ራል፣ ወይም ይጠናከራል። እንዲያው ለምሳሌ ያህል የሸመናን ወይም የሸማ መሥራትን ሥራ እንውሰድ፣ በመጀመሪያ ላይ በጥንት ጊዜ ማለት ነው፣ አንድ ሰው ጥጥን አምርቶ ፈትሎ ለብሱን ሠርቶ ይለብሳል፣ መረ ትንም አርሶ ዘርቶ አምርቶ በመጠቀም ቢሆን የምግብ ፍላጎቱን ያሟላል። ከዚያም ሌላውን ትቶ ልብስ በመሥራት ወይም በሸመናው ተግባር ላይ ያተኩራል፣ ልብስ አምርቶ በመሸጥና እህልና የመሳሰለውን ከሌሎች በመግዛት ወይም በመለወጥ ይወስናል። ይህ በማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል አንድ ደረጃ ነው። ወደዘመናዊ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የመጣን እንደ ሆነ የሸመናው ሥራ በመቶ ወይም ከዚህ በላይ በሚቆጠሩ የሥራ ዓይ ነቶች ተከፋፍሎ ሲንቀሳቀስ እናያለን። የእያንዳንዱ ሠራተኛ ተግባር አንድ የሥራ እንቅስቃሴ የሚያከናውን ማሽን/መኪና/ የሥራ ሂደት መቆጣጠር ሆኖ እናገኘዋለን። በመጨረሻም ይህ የሥራ ክፍፍልና የማሽን ሰውን መተካት ምርታማነትን ከፍ ያደርገዋል፣ ይህም ለውውጥን ያሳድጋል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ የሥራ ክፍፍል ነው። የሰው ልጅ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እየተራቀቀ በሄደ መጠን አብዛኛው ሥራ በማሽን የሚከናወን ይሆንና የሰው ሚና ዛንዲት ሥፍራ ሆኖ አንዲት ነገር ነካ ማድረግና የማሽኖችን እንቅስቃሴ ማየትና መቆጣጠር ብቻ ይሆናል። ይህ ሂደት የሰውን ድካም ከማቃለሉም በላይ ምርትን በጣም ያሳድጋል፣ የሰውም ፍላጎት የበለጡ ይሟላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከዚህ ሂደት የምንገነዘበው ዐቢይ ጉዳይ የማምረት ተግባር ምን ያህል ማኅበራዊ እንደሆነ ነው። ከሥር ጀምሮ ማምረት መተጋገዝንና መደጋገፍን መተባበርን የሚጠይቅ ቢሆንም

ኅብረተሰብ እያደገ በሄደ ቁጥር ይህ የማምረት ማኅበራዊነት በጣም ጉልህ ሆኖ ይታያል። ታዲያ ለምሳሌ በካፒታሊስት ስልተምርት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወዝአደሮች ባንድ ፋብሪካ ውስጥ በመሥራት የሚያስገኙትን ምርት ለእነርሱ በሕይወት ማቆያ የምትሆን መጠነኛ ክፍያ ካፒታሊስቱ ይወረውርላቸውና የቀረውን አብዛኛውን የምርት መገልገያዎች ባለቤት በመሆኑ ብቻ ገል ኪሱ ውስጥ ያስገባል። ይህም የበዝባዥና የተበዝባዥ ግንኙነት በሁለቱ ዐቢይ መደቦች በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል በሚፈጠረው የማይታረቅ ቅራኔ ምክንያት በሚካሄደው ትግል የካፒታሊስቱ ስልተምርት ተደምስሶ የማኅበራዊ ተግባር ውጤት የሆነው ምርት በሙሉ ለኅብረተሰቡ ጥቅም እንዲውል ይደረጋል። ማምረቱም ማከፋፈሉም ማኅበራዊ ይሆናል። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በሶሺያሊስት ሥርዓት ብቻ ነው።

## 1.4 <u>የፖለቲካ ኢኮኖሚ የጥናት መስክ</u>

ቀደም ሲል ሰው መሠረታዊ ፍላጎቱን ለማርካት ወይም ለማሟላት በአካባቢው የሚገኙትን ልዩ ልዩ የቁስ አካል ክፍሎች በሥራው እንደሚለውጥ፣ ይህ ደግሞ ማምረት መሆኑን ምርት ከማከፋፈል ከመለዋወጥ ከፍጆታ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማመልከት ተሞክሯል።

ሰዎች በማኅበር ሆነው ሲያመርቱ በመካከላቸው ግንኙነት ይፈጥራሉ፣ የዚህ ግንኙነት አምበርት የምርት መገልገያዎች የይዞታ ዓይነት ማለትም የግል ወይም የወል የመሆኑ ጉዳይ ነው። የማምረቱ፣ የመለዋወጡ የማከፋፈሉና ለፍጆታ የማዋሉ፣ የልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መደቦች ቡድኖች ሚናና ሥፍራ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት አኳያ ይታያል ይወሰናል። የእነዚህ ሁሉ የግንኙነት ድር ከዚህ ማዕከል ነው የሚደራው። የኅብረተሰብና የምርት ኃይሎች ዕድገት ከምርት ግንኙነቶች ጋር በቅርብ የተሳሰረና የተወሳሰበ ነው። ስለዚህ ነው ማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሳይንስ የጥናቱን መስክ የምርት ግንኙነቶች ያደረገው።

የፖለቲካ ኢኮኖሚ የጥናት መስክ የምርት ግንኙነቶች ናቸው ስንል ከላይ እንደተጠቀሰው ምርትን፣ ልውውጥን፣ ክፍፍልን ፍጆታን የሚገዙት ሕግጋት በዚሁ ውስጥ ይጠቃለላሉ፣ ይጠናሉ ማለት ነው። የምርት ኃይሎች ከምርት ግንኙነቶች ጋር ያላቸውን መስተጋብራዊ ግንኙነቶችና ውስብስብ ቁርኝት የኅብረተሰብን ዕድገት የሚወስኑት ሕግጋትም በዚሁ በፖለቲካ ኢኮኖሚ ሳይንስ ይተነተናሉ ይጠናሉ። ለዚሁም ማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ኅብረተሰብ ከሥር ጀምሮ እንዴት እያደገ እንደመጣ የሚያሳይ በመሆኑ ታሪካዊ ባሕርይም አለው። በአጠቃላይ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ከምርት ግንኙነቶች በመነሳት ወይም ከእነዚህ ጋር በማጣመርና በማያያዝ በልዩ ልዩ ወቅትና የዕድገት ደረጃዎች ሰዎች እንዴት እንደሚያመርቱና እንደሚከፋፈሉ በምን እንደሚያመርቱ በዚህ ሂደት ውስጥ ባገኙ የተወሰነ ደረጃ ላይ ኅብረተሰብ እንዴት በመደብ እንደሚከፋፈል፣ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች፣ በአምራችና በዝባዥ መደቦች መካከል ቅራኔዎች እንዴት እንደሚፈጠሩና እንደሚፈቱ በመጨረሻም ላይ ኅብረተሰብ ወደሶሺያሊዝም ብሎም ኮሙኒዝም እንደሚሄድ ይህንን ሂደት የሚገዙትንና የሚወስኑትን ሕግጋት ይተነትናል፣ ይመረምራል፣ ያጠናል።



# ጥ ያ ቄ ዎ ች

1. የሰው መሠረታዊ ፍላጎቶች ምንድናቸው? ተጨባጭ ምሳሌዎችን በመስጠት አብራራ።

2. መሠረታዊ ፍላጎታችንን ለማሟላት ምን ማድረግ አለብን?

3. ሰው ሰው ሊሆን የቻለው እንዴት ወይም በምንድነው? አብራራ።

4. ሰው "ማኅበራዊ እንስሳ ነው" ስንል ምን ለማለት ነው?

5. ሰው "መሣሪያ /ማምረቻ/የሚሠራ እንስሳ ነው" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አብራርተህ አስረዳ።

6. ምርት፣ ለውውጥ፣ ክፍፍል፣ ፍጆታ ምን ግንኙነት አላቸው? ተጨባጭ ምሳሌዎችን ሰጥና አብራራ።

7. በማምረትና በማከፋፈል ሂደት ውስጥ ምን ሚና ትጫወታለህ?

8. ምርታማነት እንዴት ያድጋል? ተጨባጭ ምሳሌ በመስጠት አስረዳ።

9. በምርት ኃይሎችና በሥራ ክፍፍል መካከል ያለውን ግንኙነት አስረዳ።

10. የሰውና የኅብረተሰብ ዕድገት መሠረትና እንቅስቃሴ ኃይል ምንድነው? አብራራ።

# የሚነበቡ መጻሕፍት

1. የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሠረተ ሃሣቦች — ኒኪቲን /አማርኛ ትርጉም/
   —ብለጢ አንዳርጌ፣ ገጽ.1 — 19

2. የማርክሲስት ሌኒኒስት ፖለቲካ ኢኮኖሚ [illegible]
   —ጌታቸው ገበሬ /አማርኛ/

3. የፖለቲካ ኢኮኖሚ ቀላል አቀራረብ — ወንድወሰን አሰበ

4. *Political Economy - Capitalism - Koslov pp. 11 - 31*

5. *Anti-Duhring - Engels pp. 169 - 182*

6. *A Contribution to the Critique of Political Economy*
   *- Marx pp. 8 - 30*

7. *Political Economy - Eaton pp. 10 - 14*

8. *The Part Played by Labour in the Transition from Ape to Man - Marx - Engels Selected Works Vol. I, pp. 354 - 365.*

## 2.0 የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት

ሰው ከተፈጥሮ ጋር እየታገለ ፍላጎቶቹን ያሟላል፤ የሰው ፍላጎቶችና የማሟላት ሂደት በልዩ ልዩ ደረጃ የሚወሰን ነው። ባለፈው ክፍል ውስጥ በዝርዝርና ቁልል አድርገን ለማየት የሞከርነው መሠረታዊ ፍላጎቶችና ከእነዚህ የሚመነጩት ባለማቋረጥ ብቅ ብቅ የሚሉት የልዩ ልዩ ደረጃ ፍላጎቶችም አሉ። መሠረታዊ ፍላጎቶች በመጠኑም ቢሆን ካልተሟሉ ሰው በሕይወት ለመኖር እንደማይችልና ለእነርሱም በሙሉ ሊሆንም እንደማይችል ግልጽ ነው። እነዚህ እየተደራረቡ የሚመጡት ፍላጎቶች በመጀመሪያ ላይ ይህንን ያህልም አስፈላጊ መስለው ባይታዩም ወይም የቅንጦት ባሕርይ ቢኖራቸውም አብዛኞቹ ውለው አድረው አስፈላጊ እጅግ በጣም አስፈላጊ እየሆኑ ይሄዳሉ። በምሳሌ ለማብራራት እንሞክር። እንጀራና ወጥ በልተን ለመኖር እንችላለን፤ ከዚህ የምናገኘው ንጥረ ነገር የተወሰነ ኃይል ወይም ጉልበት ስለሚሰጠን የተወሰነ ሥራ ለመሥራት እንችላለን። ጤናማነታችንም እስከ ተወሰነ ደረጃ እንጂ ማናቸውንም በሽታ ለመከላከል አያስችለንም። ነገር ግን ልዩ ልዩ አትክልትና ፍራፍሬ ሌሎችንም ከፍተኛ ምግብነት ያላቸውን ነገሮች መመገብ በመጀመሪያ ላይ ይህንን ያህልም አስፈላጊ ላይመስል ወይም እንደቅንጦት ሊታይ ይችል ይሆናል፤ ሆኖም እንደኛ እነዚህ ከተለመዱ ሁለተኛ ከምንሠራው ሥራና ከሚሰጡን ኃይልና ጤናማነት የተሟላን ለመሆን ከሚያደርጉት አስተዋጽኦ አንፃር የታዩ እንደሆን አስፈላጊነታቸው ከፍ ይላል። በሌሎችም መስኮች እንደዚሁ ነው፤ ባለፈው ክፍል እንደተመለከተው የፍላጎቶች ያለማቋረጥ ብቅ ብቅ ማለት የዘላለማዊነት ባሕርይ አለው።

ሰው ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚችለው በጋራ በሚያደርገው ጥረት ነው፤ በማኅበር በማምረት ነው። ወደፊት እንደሚገለጸው በዚህ ሂደት ውስጥ በመደብ ከተከፋፈለ በኋላ በአንድ በኩል ከተፈጥሮ ጋር ሲታገል በሌላ በኩል ደግሞ የመደብ ትግል እያካሄደ በዚህም ከዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ወደከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ሊደርስ ችሏል። ይህ የኅብረተሰብ ዕድገት እንደዚሁ በዘፈቀደ የሚሄድ ወይም

የሚካናወን ሳይሆን የሚመሩት የሚገዙት ሕግጋት አሉት፤ ሂደቱ ዕድገቱ በእነዚህ ሕግጋት መሠረት የሚካናወን ነው። እነዚህ የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋት የቅሰ ለካለን የእንቅስቃሴ፤ የለውጥና የዕድገት አጠቃላይ ሕግጋትን ይከተላሉ። በተፈጥሮና በሰው እንደዚሁም በመደቦች መካከል ያሉት ቅራኔዎች አንቀሳቃሽ ሞተሮች ናቸው፤ በመደቦች መካከል ያለው ቅራኔ በኮምዩኒስት ኅብረተሰብ የሚያከትም ሲሆን ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግን ዘላቂ ዝንተ ዓለማዊና የማያቋጥ ይሆናል።

የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት የኅብረተሰብ የዕድገት ሕግጋት አካልና አምብርት ናቸው፤ መሠረታቸው ምንጫቸው የሰው ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚደረገው ትግል ነው። እነዚህን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማርካት የሚደረገውን ጥረት አቅጣጫ የሚሰጡትና የሚመሩት ሕግጋት ከሌሎች የኅብረተሰብ ሕግጋት የበለጠ የወሳኝነት ሚና አላቸው።

እነዚህ የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት በማኅበራዊ የማምረት የለውጥ የማከፋፈልና ፍጆታ ሂደት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ዐበይት ነገሮች ናቸው። የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት የምርት ግንኙነቶችን ይገልጻሉ፤ ከምርት ኃይሎች ጋር ያላቸውንም ዝምድና ይወስናሉ።

## 2.1 የኢኮኖሚ ሕግጋት ነባራዊ ባሕርይ

የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት ነባራዊ ባሕርይ ከየት ነው የሚፈልቀው? ምን ያስገነዝበናል? ይህንን ለይቶ ማወቅ ለምን ይጠቅማል? እነዚህን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ እነዚህን ሕግጋት በመጠኑም ቢሆን ቀረብ ብለን ለማየት እንሞክራለን።

የእነዚህ የኅብረተሰብ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት ነባራዊ ባሕርይ የሚረጋገጠው በራሳቸው ሕልውና ያላቸው በመሆናቸው ነው። ይህ ምን ማለት ነው? እነዚህ ሕግጋት ከሕሊናችን ውጭ የነበሩ፣ ያሉና የሚኖሩ ናቸው፣ የሰው ሕሊና ስሜት፣ አስተሳሰብ የወለዳቸው ወይም የፈጠራቸው አይደሉም፣ ሰው ስለፈለገ የመጡ ስላልፈለጋቸው የሚጠፉ አይደሉም፣ ከእኛ ፍላጎት ፈቃድ ውጭ በራሳቸው የሚኖሩ ናቸው። ለምሳሌ በጥንታዊ ጋርዮሽ ሰዎች ሥራ የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችና ምርታቸውንም በጋራ ይጠቀሙባቸዋል፣ ይህ የሆነው በዚህ ህብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች ስለፈለጉ ሳይሆን በዚህ ዝቅተኛ በሆነው የዕድገት ደረጃ ለመኖር የሚቻለው በዚህ ዓይነት ዘዴ ወይም መንገድ ስለሆነ ብቻ ነው፣ በሌላ ዓይነት መንገድ በመጠቀም ቢሆን ተፈጥሮን ለመቆጣጠርና ለሕይወት አስፈላጊ የሆነውን ነገር በማግኘት ከአውሬና ከሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ለመከላከል ስለማይቻል ነው። ይህ የጥንታዊ ጋርዮሽ ኅብረተሰብ ሲፈራርስና በባሪያ ኅብረተሰብ ሊተካ የቻለውም በሰዎች ፍላጎት ወይም ፈቃድ ሳይሆን ምርትን የበለጠ ለማሳደግና ፍላጎቶችንም በበለጠ ሁኔታ ለማሟላት ኅብረተሰቡ ባደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የተፈጠረውን ቅራኔ መፍታት የግድ ስለነበረ ነው።

ሌላው የማኅበራዊ ዕድገት ኢኮኖሚ ሕግጋት ነባራዊነት የሚገፀባረቅበት መስከ የኅብረተሰብ በልዩ ልዩ ሥርዓተ ማኅበራት ውስጥ ማለፍ ጉዳይ ነው። በአጠቃላይ ሲታይ የኅብረተሰብ ዕድገት ከጥንታዊ ጋርዮሽ ወደ ባሪያ አሳዳሪ ኅብረተሰብ ከዚህ ወደ ፊውዳል ከዚህ ለጥቆ ወደ ካፒታሊስት ከዚህ ደግሞ ወደ ሶሺያሊስት—ኮምዩኒስት ነው። ይሁንና በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች አንድን ሥርዓተ ማኅበር ሙሉ በሙሉ ባይጨርሱ ወደሌላው ለመሸጋገር እንደሚቻል በታሪክም

ተመዝግቧል። ለምሳሌ ከከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት ስልተ ምርት በበጢራዊ ቢሮክራሲያዊ አብዮት አድርጎ ወደ ሶሺያሊዝም ብሎም ኮምዩኒዝም ለማለፍ እንደሚቻል በአሁኑ ወቀት እየታየ ነው። ከኮምዩኒስት ኅብረተሰብ ገና ባይደረስም ዛሬ በርከት ያሉ አገሮች የዚሁ ኅብረተሰብ የመጀመሪያ ደረጃ የሆነውን ሶሺያሊዝምን በመገንባት ላይ ያሉና በዚህ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ይገኙባቸዋል። በመልክአ ምድራቸው በአቀማመጣቸው በአየር ጠባያቸው በሕዝባቸው አኗኗርና ባሕርይ የተለያዩ አገሮች ለምሳሌ ሶቪዬት ሕብረት፣ ጂ.ዲ.አር.፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ እንግሊዝ፣ ቻይና፣ ኢትዮጵያ፣ ሕንድ ወዘተ... ባነሰ ገደል በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ሥርዓተ ማኅበራት አልፈው ገሚሶቹ ካፒታሊስት፣ ሌሎቹ ሶሺያሊስት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንገልስ በሳይንሳዊ ኮምዩኒዝም ንድፈ ሃሣብ እንዳረጋገጡት ኅብረተሰብ በሙሉ ወደሶሺያሊዝም ብሎም ኮምዩኒዝም መሄዱ የማይቀር ነው። ይህ ሁሉ የሆነውና የሚሆነው ከግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ መደቦች ፍላጎትና ፈቃድ ውጭ ነው። እነዚህ ወደፊትም ጠሉም የኅብረተሰብ የዕድገት ሕግጋት የሰው ፍላጎቶች መሟላት የሰው ነፃ መሆንና በአጠቃላይም ሙሉ ሰብአናውን መጎናጸፍ በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ እንዲያልፍ በመጨረሻም የሰው ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ ሊሟሉ ወደሚችሉበት ወደኮምዩኒስት ኅብረተሰብ እንዲደርስ የኅብረተሰብ የኢኮኖሚ ሕግጋት ያስገድዱታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ወዝአደሩ የሚያካሂደው የዕለት በዕለት ትግል፣ ሶሺያሊዝምን ብሎም ኮምዩኒዝምን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት የእነዚህን ሕግጋት አስፈላጊነትና ከፍተኛ ሚና ያሳያል። እነዚህን ሕግጋት በሰፋትና በጥልቀት አጣርቶ ማወቅ የቡርዧ አፈ ቀላጤዎች ለማሳመን እንደሚሞክሩት የካፒታሊስት ሥርዓት ዘላቂ ወይም ዘላለማዊ ሳይሆን ጊዜያዊ አላፊ ሥፍራውንም ለሶሺያሊዝም ብሎም ለኮምዩኒዝም

የሚለቀና በዚህ መዝገቱ የማይቀር ጉዳይ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ሕግጋቱን ደህና አድርጎ ማወቅ ትክክለኛ የትግል ታክቲክና ስትራተጂን በመቀየስ ለሶሺያሊዝም የሚደረገውን ትግል ያፋጥነዋል። የበዝበዛውን ሥርዓት በመገርሰስ ድልን የተቀዳጁት አገሮች የአድኅሮትንና የኢምፔሪያሊስቶችን የቀለበሳ ሤራ እንዴት ለመቋቋምና ለማክሸፍ እንደሚችሉ ከዚያም አልፈው እሢሩን ኅበረተሰብ ለመገንባት ኃይላቸውንና ሀብታቸውን እንዴት [illegible] ማስተባበር ማቀደት፣ በየትኛው መደመር የትኛውን ማስከተል፣ በቀዳሚያ መከናወን ያለባቸው ነገሮች የትኞቹ እንደሆኑ የትኛው ተግባር የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጠው መቼ፣ ወዘተ... በአጠቃላይ የግንባታው ስትራተጂና ታክቲክ ቀደም ተከተል ምንና እንዴት እንደሆነ የማርክሳዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ሕግጋት በደንብ ያስገነዝባሉ። በፕላን መሥራት፣ በልዩ ልዩ የግንባታ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መጠበቅ የሚገባው ሚዛን የምርት ኃይሎች እንዴት በተፋጠነ መንገድ ለማደግ እንደሚችሉ፣ ምን ያህል ከዚህ ከዚያ መመረት ምን ያህሉ ለፍጆታ፣ ምን ያህል ለዕድገት መዋል እንደሚገባው ለመገንዘብ የሚቻለው እነዚህን ነባራዊ የኢኮኖሚ ሕግጋት በጥልቀትና በስፋት በመገንዘብ ነው። ይህ ሁሉ በወዝአደሩ የትግል እንቅስቃሴና በሶሺያሊስት አገሮች የግንባታ ልምድ ተረጋግጧል፣ በመረጋገጥም ላይ ይገኛል።

## 2.2 የሕግጋት ታሪካዊ ባሕርይ

የኅብረተሰብ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት ከጊዜ ቀደም ተከተልና ከዕድገት ደረጃ ማለትም ከኅብረተሰብ የዕድገት ታሪክ ሂደት አንፃር ሊታዩ ይችላሉ፣ እንደዚህም ሲሆን ታሪካዊ ባሕርያቸው ጎልቶ ይታያል። እነዚህ ሕግጋት ከታሪክ ሂደት አንፃር ሲገመገሙ፣ አንዳንዶቹ በሁሉም ስልተ ምርቶች ወይም በአብዛኞቹ ውስጥ ይንፀባረቃሉ፣ የቀሩት ደግሞ ለተወሰኑ ስልተምርቶች ብቻ የሚያገለግሉ ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ

የማምረት የማከፋፈልና የፍጆታ ሕግጋት ከጥንታዊ ጋርዮሽ አንስቶ በሁሉም ስልተምርቶች በቋሚነት ይሠራሉ፣ በእነዚህ ሁሉ ሰዎች ማምረት አለባቸው፣ የተመረተው መከፋፈልና ለፍላጎት ማርኪያ መዋል አለበት፤ የእነዚህን ሂደት አሠራርና አፈጻጸም የሚወስኑት ሕግጋት በተግባር ላይ ይውላሉ፣ ዘላቂነት ያላቸው ሕግጋት ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ለውጥን በገወሰዱ በጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተምርት ማከተሚያ ገደማ ብቆ ያለ ሲሆን ለዚህ እኩልነት ላይ ለተመሠረተ ስልተምርት፡ መፈራረስ ዐቢይ ምክንያት የሆነውን የግል ንብረትን የግል ሀብትን ያስገኘ እሱ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። የጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተምርት ዓይነተኛ ባሕርይ አል ነበረም ማለት ነው። እንደዚሁም በኮምዩኒስት ኅብረተሰብም ውስጥ በማከፋፈል ወይም በመከፋፈል/ምርትን በመከፋፈል/ ስለሚተካ በግል ንብረት ላይ በተመሠረቱ ስልተምርቶች/ባሪያ፣ ፊውዳልና ካፒታሊስት/ ይዘትና ቅርጽ አይኖርም። ወደኮምዩኒዝም መሸጋገሪያ በሆነው በሶሺያሊዝም ውስጥ ቢኖርም ቀስ በቀስ መልኩን እየለወጠና በምርት መከፋፈል የሚተካ ይሆናል። ግልጽ ለማድረግ ለውጥ ስንል መሸጥ መግዛት ማለታችን እንጂ በሥራ ክፍፍል አንዱ አንድ ዓይነት ነገር ወይም ዕቃ አምርቶ ለሌላው ወይም ለሌሎች መስጠትንና እንደዚሁ ሌሎች ያመረቱትን ወስዶ መጠቀምን አይደለም። ሌሎችም ተመሳሳይነት ያላቸው ሕግጋት አሉ።

አንዳንዶቹ ሕግጋት የአንዱን ስልተምርት ባሕርይ አጉልተው የሚያሳዩ ይሆናሉ፣ ለምሳሌ የባሪያ አሳዳሪ ስልተምርትን ዓይነተኛ የሚያደርገው ሰው ሰውን እንደዕቃ አድርጎ የሚጠቀምበት፣ የሚያሠራው፣ የሚሸጠው፣ የፈለገውን የሚያደርገውና የሚፈጽምበት የከፋና የከረፋ ጭቆናና ብዝበዛ የሚካሄድበት ስልተምርት መሆኑ ነው። በፊውዳል ስልተምርት መሬትን እንደዋና የምርት ምንጭ፣ የበዝባዥና ተበዝባዥ መደቦች ግንኙነት እምብርት አድርጎ ይወስዳል፣ በመሣፍንቱ በመኳንንቱ በተዋረድና በየደረጃው በገባሮች ላይ የሚደረገው ብዝበዛ የሚመሠረተው ደሩ የሚዘረጋው

በመሬትና በገበርና ተገባር አካባቢ ነው። የካፒታሊስትን ስልተ ምርት የወሰዱን እንደሆነ የሚገዛው ሕግ የተረፈ እሴት መፈጠር ነው፤ በዚህ ካፒታሊስቱ ትርፍን ያጋብሳል፤ ወዛደሩን ይበዘበዛል፤ ይህ እንግዲህ በካፒታሊስት ሥርዓት እንጂ በሌሎች የማይገኝ ወይም የማይኖር ነው። እንደዚሁም የሸቀጥ ግንኙነትን/በሸቀጥ ዕቃዎች አማካይነት ወይም አካ ባቢ የሚፈጠረው የሰዎች/ግንኙነት ብገወሰዱ በካፒታሊስት ስልተ ምርት ወሳኝነት አለው፤ የምርት ተገባር መሠረትና አንቀሳቃሽም ነው። በሶሺያ ሊስት ስልተምርት ግን በተለይም በመጀመሪያውና የዕድገት ደረጃው ዝቅተኛ በሆነበት ወቅት መጠነኛና ለየት ያለ ባሕርይ ያለው የሸቀጥ ግንኙነት ይኖራል፤ ግን ወሳኝነት የለውም። የኢኮኖሚው ዕድገት የሚመራው በፕላን ሲሆን ወሳኙና አንቀሳቃሹም የኅብረተሰቡን ፍላጎቶች ደረጃ በደረጃ በማሟላት ሰው የተደላደለና የተሟላ ሕይወት ሊኖር የሚችልበትን ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ መቀዳጀት ይሆናል። በመጀመሪያው ደረጃ ማለትም በሶሺያ ሊዝም የማምረቱና የማከፋፈሉ ተገባር "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያ ንዳንዱ እንደሥራው" የሚለውን ሲከተል፤ በሁለተኛው ደረጃ ማለትም በኮምዩኒዝም ደግሞ "ከእያንዳንዱ እንደችሎታው ለእያንዳንዱ እንደፍላጎቱ" በሚለው ዐቢይ መርህ ይገዛል።

በተለያዩ ስልተምርቶች የተለያየ ባሕርያት ያላቸው ሕጋጋትም አሉ፤ ለምሳሌ ያህል የሥራን ምርታማነት/ሌበር ፕሮዳክቲቪቲ/ እንውሰድ፤ ይህ የሰውን ፍላጎት ለማሟላት ዓይነተኛና መሠረታዊ ስለሆነ በሶሺያሊስ ትም ሆነ በካፒታሊስት ስልተምርት ውስጥ ያለ ነው። ይሁንና በካፒታሊስት ስልተምርት የሥራ ምርታማነት ዓላማ የቡርዧውን የትርፍ መጠን ከፍ ለማ ድረግ ነው፤ ሆኖም ቡርዧው የወዛደሩን የሥራ ሰዓት በማራዘም ወይም ምንዳውን በመቀነስ ይህንን ግብ ለመምታት ይችላል። በሶሺያሊስት ስልተ ምርት የምርታማነት ዓላማ የኅብረተሰቡን ዕድገት ለማፋጠን የአባሎቱን

ሕይወት ለማሻሻል ፍላጎታቸውን ለማሟላት ነው፣ ይኸውም የሚገኘው በማያቋርጥ የኢኮኖሚ ዕድገት በፕላን በመሥራት የምርት ኃይሎችን በማዳበር ይሆናል። እሴት በካፒታሊስት ስልተምርት የሸቀጦች መለዋወጫና የዋጋ መሠረት በመሆኑ የወሳኝነት ሚና ይጫወታል። በሶሺያሊስት ስልተምርት ግን ሚናው የተወሰነ ወይም መጠነኛ ነው። የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በኅብረተሰቡ ፍላጎት መሟላት ላይ የሚያተኩር ስለሆነ የማምረቱ የማከፋፈሉ ለፍጆታና ለልማት የሚውለውን ድርሻ የሚደለደሉ የሸቀጦች ዋጋና የመሳሰሉት ሁሉ በዚህ አንፃር በመንግሥትና በኅብረተሰቡ ይወሰናሉ።

## 2.3 የፖለቲካ ኢኮኖሚ መደባዊነትና ወገናዊነት

በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ ፖለቲካ ኢኮኖሚ መደባዊ ባሕርይ አለው። በመሠረቱ ከተፈጥሮ ጋር የሚደረገው ትግል በቀጥታ እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ ባይኖረውም ህብረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለና መደብም ሙሉ በሙሉ እስካልተወገደ ድረስ በሁለት አቅጣጫዎች ማለትም በመደቦች መካከልና ከተፈጥሮ ጋር የሚደረጉት ትግሎች የተወሳሰቡና የተያያዙ ስለሚሆኑ ፖለቲካ ኢኮኖሚም የወገናዊነትና የመደብ አመለካከት ይኖረዋል። ይህንን ባሕርይ የቡርዧ የኢኮኖሚና የህብረተሰብ ሳይንስ ሊቃውንት ሊክዱት ቢሞክሩም ማርክሳዊ ሌኒናዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ግን ግልጥልጥና ጥርት አድርጎ ያስቀምጠዋል። ማርክስና ኢንግልስ በኋላም ሌኒን ባደረጓቸው ሳይንሳዊ ጥናቶችና ምርምሮች የቡርዧ ሊቃውንት እንደሚሉት የካፒታሊስት ስልተምርት ከሰው ተፈጥሮ ጋር የተያያዘ ወይም ከዚህ የሚመነጭ ተፈጥሯዊ ወይም ዘላለማዊነት ያለው ሳይሆን ጊዜያዊና አላፊ በሶሺያሊዝም ብሎም በኮምዩኒዝም የሚተካ መሆኑን አስገንዝበዋል። ሶሺያሊዝም ብሎም ኮምዩኒዝም ሊመጣ የሚችለው በወዝአደሩ መደብ መራራና ውስብስብ ትግል፣ በዚህም የወዝአደሩ የሰፊው ሠርቶ አደር ሕዝብና በአጠቃላይም የጭቁኖች ጥቅምና ደኅንነት የሚጠበቅ፣ የሰው ልጅ በአጠቃላይ

ከብዝበዛና ከጭቆና ነፃ የሚወጣበትና ሙሉ ሰብአናን የሚጎናጸፍበት መሆኑን የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም መሥራቾች በጥልቅ ትንተናቸው አስረድተዋል።

ካፒታሊዝም ከፊውዳሊዝም ጋር ትግሉን ያፋፍም በነበረበት ወቅት ስወቅቶ የነበሩት የቡርዧ የኢኮኖሚና የኅብረተሰብ ሳይንስ ሊቃውንት የቡርዧውን ተራማጅ ገጽታ በማሳየት በመጠኑም ቢሆን ተከከለኛውን የካፒታሊስት ስለ ተምርት ግንኙነት አንፀባርቀው ነበር። በመጠኑም ቢሆን ይህ ትንተናቸው የሳይንሳዊነት ባሕርይ ነበረው። ይሁንና በቡርዧው እና በወዝአደሩ መደቦች መካከል ያለውን ተፃራሪ ቅራኔ አድበስብሰውት አልፈዋል፣ የወዝአደሩ ትግል መፋፋም ሲጀምር የቡርዧውን ሥርዓት ዘላለማዊነት ለማሳየት ምንም ዓይነት ሳይንሳዊነት የሌላቸው ንደፈ ሃሣቦችን ለመንደፍ ሞክረዋል፣ ሆኖም አላዋጣቸውም። በሌላ አንፃር የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች ካፒታሊዝምን ተፈጥሯዊ ዘላለማዊ አድርገ የማቀረብ ሙከራ ራሱ የዚሁ መደብ አፈቀላጤነታቸውንና የአቋማቸውን ወገናዊነት ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በዛሬው ጊዜ የቡርዧ ኢኮኖሚስቶች የሚያካሂዱት ጥናቶችና ምርምሮች ካፒታሊስቶች ትርፋቸውን እንዲያሳድጉና የኢምፔሪያሊዝም ይዞታ አቁልቁሉ እንዳይወርድ የተቻላቸውን ያህል ርዳታ ቢያደርጉም መጠነኛ የነበረው ሳይንሳዊነታቸው ግን ሙሉ በሙሉ ካከተመ ቆይቷል። የወዝአደሩና የሰፊው ሕዝብ ትግል መፋፋምና የተቀዳጃቸው ድሎች የዓለም ሲሣው የሶሺያሊስትን ገንባታ ሂደት በማፋጠን ላይ መገኘት የሶሺያሊዝምን የበላይነት አረጋግጧል፣ በማረጋገጥ ላይም ይገኛል። ሳይንስን የሚያራምደውና የሚያሳድገው ሶሺያሊዝም አልፎም ኮምዩኒዝም መሆኑን በማያጠራጥር አኳኋን እየተረጋገጠ ነው።

የፖለቲካ ወገናዊነት የሚንፀባረቅበት ሌላው ገጽታ ሕጎችን ተግባራዊ ለማድረግ በሚሞከርበት ጊዜ የሚያስነሳው መደባዊ ተቃውሞ ነው።

የበላይነትን የጠበጠው መደብ ጥቅሙን ለማስከበር ሕግጋትን ተግባራዊ ለማድረግ ሲነሳ ጥቅማቸው የሚነካባቸው መደቦች ደግሞ ይቃወማሉ፣ ሥራ ላይ እንዳይውሉ ባላቸው አቅም ሁሉ ይታገላሉ። ለምሳሌ ካፒታሊዝም ፊውዳሊዝምን ድል አድርጎ የበላይነትን ሲያስፋፋ ባንድ በኩል ከወደቀው ስልተምርት ርዝራዦች በሌላ በኩል ከወዝአደሩና ከሌሎች ጭቁኖች የሚገጥመውን ተቃውሞ በኃይል ይቋቋምና ይደመስስ ነበረ። ወዝአደሩም ካፒታሊዝምን ደምስሶ የበላይ ገዢነትን ሲመሠርት የተሸነፈው መደብ አባላት አዲሱ ስልተምርት በተግባር ላይ እንዳይውል ከባድ ትግል ያካሂዳሉ፣ በሶቪዬት ሕብረትና በሌሎችም የሶሺያሊስት አብዮት ባካሄዱት አገሮች፣ እንደታየው የተሸነፉት አድኃሪ መደቦች ከኢምፔሪያሊስት ኃይላት ገን ተሰልፈው ገብ ገብ ገጥመዋል። ይህ ሁኔታ በእኛም አብዮት ሂደት ውስጥ ባለፉት ስድስት ዓመታት ቁልጭ ብሎ ታይቷል፣ በመታየትም ላይ ይገኛል። ሆኖም ተቃውሞውንና ጣልቃ ገብ ወረራውን አክሽፍ የሶሺያሊዝምን የኢኮኖሚ ሕግጋት በሥራ መተርጎም ተችሏል። የእኛም ልምድ እንደሚቻል እያሳየን ነው።

ለማጠቃለል የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሳይንስ የህብረተሰብን ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት የሚያጠናና የሚመረምር ነው፣ እነዚህ ሕግጋት ነባራዊና ታሪካዊ ባሕርይ አላቸው። የምርት ኃይሎችንና የምርት ግንኙነቶችን የመጣጣም ወይም የአብሮ መጓዝ ሁኔታና የማምረትንና የፍላጎት ማሟላትን ውስብስብ ግንኙነት የሚገዙት ሕግጋት ለሁሉም ስልተምርቶች የሚያገለግሉ ናቸው። ለአንድ ስልተምርት ወይም ለተወሰኑ ስልተምርቶች የሚያገለግሉ ሕግጋትም አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ የፖለቲካ ኢኮኖሚ የመደብ ባሕርይ አለው፣ የቡርዧ ፖለቲካ ኢኮኖሚ የካፒታሊስቶችን ጥቅም የሚንከባከብ ሲሆን የማርክሳዊ ሌኒናዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ ደግሞ የወዝአደሩንና የሠርቶ አደሩን ሰፊ ሕዝብ ጥቅም የሚያስከብር ነው።

## ጥያቄዎች

1. የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት መነሻ ወይም መሠረት ምንድነው? ምሳሌዎችን በመስጠት አብራራ።

2. ሕግጋት ነባራዊ ናቸው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ሰፋ አድርገህ አስረዳ።

3. ሕግጋት ታሪካዊ ናቸው ስንል ምን ማለታችን ነው? አብራራ።

4. ለሁሉም ስልተ ምርት የወል የሆኑትን አንዳንድ ሕግጋት ጥቀስና በየስልተ ምርቱ እንዴት እንደሚሠሩ አስረዳ።

5. የእያንዳንዱ ስልተ ምርት ዓይነተኛ ወይም መሠረታዊ ሕግጋት አመልከት።

6. እነዚህን የማኅበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት ጠንቅቆ ማወቅ ለምን ይጠቅማል? በምሳሌ አብራራ።

7. ለኢትዮጵያ አብዮት መፈንዳት ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች ከእነዚህ ሕግጋት ጋር በማገናዘብ አብራራ።

8. በሶሺያሊስት ስልተ ምርት ማምረትና ማከፋፈል ማኅበራዊ ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አብራራ።

9. የሶሺያሊስት ኢኮኖሚ ዕድገት ዓላማ ምንድነው?

10. የፖለቲካ ኢኮኖሚ መደባዊና ወገናዊ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? በእያንዳንዱ ስለ ትምርት ውስጥ እንዴት እንደሆነ አብራራ።

## የሚነበቡ መጻሕፍት

ባለፈው ክፍል መጨረሻ ላይ በገጽ 18 የተጠቀሱትን መመልከት ነው።



## 3.0 የፖለቲካ ሳይንስ ጽንሰ ሃሳቦች መግለጫ

የሰው ልጅ ተፈጥሮንና የኅብረተሰብ ዕድገት ሕግጋትን ለመረዳትና በተፈጥሮ ላይ ያለውን ቁጥጥር ለማጠናከር ሰፊ ያሉ ምርምሮችንና ጥናቶችን አካሂዷል። በዚህ የማያቋርጥ የመመርመርና የማወቅ ጥረት የዕውቀት ክምችቱም ከዘመን ወደ ዘመን እየዳበረ በመሄዱ የዕውቀት ዘርፎችም እንዲሁ እየተስፋፉ መጥተዋል። በዚህ መሠረት ቀደም በፍልስፍና ላይ ብቻ ያካበበ የነበረው ዕውቀት በልዩ ልዩ ዘርፎች እየተከፈለ ሊሄድ ችሏል። ከዕውቀት ዘርፎች መስፋፋት ጋር እያንዳንዱ የዕውቀት መስክ የራሱ የሆነ ሕግጋትና ጽንሰ ሃሳቦችን እያዳበረ መጥቷል።

የፖለቲካ ሳይንስ ከዕውቀት ዘርፎች አንዱ ነው። በረጅም ዘመን ዕድገቱ እንደሌሎች የዕውቀት መስኮች የራሱ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦችን አዳብሯል። እርግጥ ጽንሰ ሃሳቦችን ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ቃላቶች ወይም ሐረጎች የሚመነጩት ህብረተሰቡ ከሚጠቀምባቸው ቋንቋዎች ነው። ሆኖም የቃላቶቹ ወይም የሐረጎቹ ትርጉም ግን በተራ አገላለጽና አጠቃቀም ከሚያዘሉት ትርጉም የበለጠ ስፋትና ጥልቀት አለው። "ግራ" የሚለው ቃል ለምሳሌ ለማናቸውም ሰው ግልጽ በመሰለም ሳይንሳዊ ትርጉሙና ይዘቱ ግን በቋንቋ ችሎታችን ከምንረዳው የበለጠ ሰፊ ነው። በተመሳሳይ መልክ የማምረቻ መሣሪያዎች፣ የምርት ግንኙነት፣ የምርት ተገበሮች የምርት መገልገያዎች፣ ስለ ትምርት... የመሳሰሉት ጽንሰ ሃሳቦች እንዲሁ ከተራ አጠቃቀማቸው የጠለቀ ትርጉም አላቸው። የፖለቲካ ሳይንስ ዕውቀታችንን ለማዳበር በተከታታይ በቀደም ተከተል የሚቀርቡልንን ትምህርታዊ የውይይት ርዕሶች በሚገባ ለመከታተል በቀዳሚያ አንዳንድ ቁልፍ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦችን መግለጫ መረዳት ጠቃሚ ይሆናል። በዚህም መሠረት ይህ ክፍል በጽንሰ·ሃሳቦች ትንተና ላይ ያተኩራል።

## 3.1 ሥራ

ካርል ማርክስና ፍሬዴሪክ ኤንገልስ ዝነኛ በሆነው "ጀርመን ኢዲዮሎጂ" በተባለው ሥራቸው እንዳመለከቱት "ሰዎች ታሪክ ለመሥራት ከመብቃታቸው በፊት ለመኖር መቻል አለባቸው።" ለመኖር ደግሞ ከማናቸውም ነገር በፊት መብላት፣ መጠጣት፣ መልበስና መጠለያ ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ የሰው ልጅ በሕይወት ለመኖር ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የመሳሰሉትን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማርካት መቻል አለበት። እነዚህን መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት የሚያደርገው ጥረት የመጀመሪያው ታሪካዊ ድርጊት ይሆናል።

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡሮች በማይለይበት ዘመን መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ሁሉ ሳያመርት እንዳሉ ከተፈጥሮ ያገኝ ነበር። ምናልባትም ዛሬ ጦጣ፣ ዝንጀሮና የመሳሰሉት የዛፍ ቅጠልና ፍሬ እንዳለ እየሸመጠጡ ምንም ሳይለውጡ እንደሚበሉትና በዛፍ ላይ እንደሚያድሩት ዓይነት ይኖር ነበር። በረጂም ዘመን ሂደት የሰው ልጅ ራሱን ከሌሎች ፍጡሮች ከፍ እያደረገ ሲመጣ ግን በተፈጥሮ እንዳሉ በሚያገኛቸው ነገሮች ሊረካ አልቻለም። ስለዚህ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት በአካባቢው የሚገኙትን ልዩ ልዩ የተፈጥሮ አካሎች እንደሚስማሙት አድርጎ ለመለወጥና ለመጠቀም ማምረት፣ መሥራት ጀመረ። በመጀመሪያ የሚመገባቸውን ነገሮች እያበሰለ ማዘጋጀት ጀመረ። ከዚያም በተለያዩ አየር ሁኔታዎች ለመኖር ራሱን ከብርድ ለመከላከል ልብስና መጠለያ የመሳሰሉትን ለማሟላት ቻለ። የመጀመሪያ ደረጃ መሠረታዊ ፍላጎቶች መሟላት ተጨማሪ ፍላጎቶችን እየፈጠረ ሄደ። ተጨማሪዎችን ፍላጎቶችን ለማርካት ተጨማሪ ምርት ማምረት አስፈለገ። በዚህ የማያቋርጥ የመሥራት፣ የማምረት ሂደት የሰው ልጅ ከጊዜ ወደጊዜ ተፈጥሮን በይበልጥ በቁጥጥሩ ሥር በማዋል ዛሬ የሚገኝበት አስደናቂ ዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል።

ይህንን መሠረታዊ ጠቀ ለማረጋገጥ የምንገኝበት ኅብረ ተሰብ መሥራት፣ ማምረት፣ ቢያቁም ደርጊቱ በኅብረ ተሰቡ አባላት ላይ የሚያስከትለውን ውጤት ለአንድ አፍታ በሕሊናችን ውስጥ ለመገመት እንሞክር። የእህል ምርት ቢያቁም ቢያንስ ሕይወት በለመዱነው መልክ ሊቀጥል አይችለም። ለጥቂት ጊዜ ሰዎች ሕይወታቸውን ለማዳን በተፈጥሮ የሚያገኙትን ቀጠላ ቀጠል ለመገቡ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም የሰው ባሕርይ በቀጠላ ቀጠል ከሚኖረው እጥንታዊ ሰው ባሕርይ በጣም ስለ ተለወጠ በዚህ ዓይነት ለመጋገብ ብዙ ሊገፋ አይችለም። አንድ ሰው ወይም ጥቂት ሰዎች ዛሬ በደረሰገበት የዕድገት ደረጃ የሚያስፈልጉትን ወይም የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ በራሱ ወይም በራሳቸው አያመርቱም። ስለሆነም ፍላጎትን በጥቀል ለማርካት በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሌሎች እምራቾች በልዩ ልዩ ዘርፍ የሚያመርቱትን ውጤት በገበያ አማካኝነት መለዋወጥ የግዴታ ይሆናል። ሌላውን ትተን የመገናኛ አገልግሎት እንኳን ቢቋረጥ በአንድ ህብረ ተሰብ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መገመት አያዳግትም። ሌሎችም ምሳሌያችን መጥቀስ ይቻላል። ባጭሩ ምርት ከቆመ የሰው ልጅ ሕልውና ሊኖረው አይችለም። ህብረ ተሰብ ለማኅበራዊነቱ፣ ለግንኙነቱና ለመሰባሰቡ መሠረት ምርት እንደመሆኑ ምርትም የሚመጣው በሥራ በመሆኑ ሥራ ከቆመ ኅብረ ተሰብ የሚባል ነገር ሊኖር አይችለም።

ታላቁ ፈላስፋ ካርል ማርክስ ስለሥራ በሰጠው መግለጫ ሥራ በመጀመሪያ ሰውና ተፈጥሮ የሚሳተፉበት፣ ሰው በራሱ አነሳሽነት በእሱና በተፈጥሮ መካከል የሚፈጠረውን ተደጋጋሚ ቁሳዊ ድርጊቶች የሚቆጣጠርበት የሚያርቀበት ሂደት ነው። ሰው የተፈጥሮ የራሷ አንዱ ኃይል ሆኖ ራሱ ከተፈጥሮ ጋር በመታገል የተፈጥሮን ልዩ ልዩ ክፍሎች /ፍሬዎች/ ለራሱ ፍላጎቶች ማርኪያ ለማዘጋጀት ክንዶቹንና ቀለጥሞቹን እዕምሮውንና እጆቹን የሰውነቱን ተፈጥሯዊ ኃይል ያንቀሳቀሳል" ብሎ አጠቃሎታል።/ካፒታል ቀጽ 1፣ ገጽ 173፣ ፕሮግረስ አሳታሚ 1954/።

ነው። ስለዚህ ሥራ የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት በተፈጥሮ የሚያገኛቸውን ቁሶች የሚለውጥበትና ለራሱ ፍላጎት የሚያዋህድበት ዓላማ ያለው ክንዋኔ ነው። ስለሆነም የሰው ልጅ በጊዜ ብዛት እየጨመሩ የሚሄዱትን ፍላጎቶቹን ለማርካት ከተፈጥሮ ጋር የማያቋርጥ ትግል ያካሂዳል። በረጅም ዘመን ትግሉ የተፈጥሮን ለስበራ ገጽታዎች በቁጥጥሩ ሥር ለማዋልና በተፈጥሮም ላይ ያለውን የበላይነት እያጠናከረ በመምጣቱ ዛሬ ከአራቱ ዓለም አልፎ ስለሌሎች ዓለሞች/ለምሳሌ ጨረቃ፣ ማርስ ወዘተ.../ አስደናቂ ምርምሮችን በማካሄድ ላይ ይገኛል። በጫካ ውስጥ ከአውሬ ከማይሻል ኑሮው ተላቆ ዛሬ የደረሰበት ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ለመድረስ የቻለው ግን <u>በሥራ ነው።</u> ስለዚህ ወደሀብትነት የሚለወጧቸውን ቁሶች ከምትለግሰው ከተፈጥሮ ቀጥሎ <u>የሰው ልጅ ሀብትና ዕድገት ምንጭ ሥራ ነው።</u>

በኅብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ሥራ ለሰው ልጅ ሕልውና አስፈላጊ የሆኑ ቁሶችን ከማስገኘት የበለጠ ታሪካዊ ሚናም ተጫውቷል። ፍሬዴሪክ ኤንግልስ እንዳለውም "ሰውን ራሱን ሰው ያደረገው ሥራ ነው"። ይህ አባባል የሥራ ክቡርነትና ሥራም ለሰው ልጅ የማቴሪያል ዕድገት ያደረገውን አስተዋጽኦ ከማስገንዘብ የሚያልፉ ጠለቅ ያሉ መሠረታዊ ሃሳቦችን ያዘለ ነው።

የሰው ልጅ ስለአካባቢውና ስለራሱም ተፈጥሮ መመራመር ከጀመረ ጊዜ አንስቶ መሬት፣ እጽዋት፣ እንስሳትና ሰው እንዴት ሕልውና ሊያገኙ እንደቻሉ ለማወቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በዚህ መሠረት ከጥንታዊ የግሪክ ፈላስፎች ጀምሮ በየዘመኑ የተነሱት ፈላስፎችና ሊቆች የተፈጥሮንና የሰውን ልጅ አመጣጥና ዕድገት ለመግለጽ የተለያዩ ንድፈ ሃሳቦችን አቅርበዋል። ጥያቄው በጣም አወዛጋቢና ውስብስብም በመሆኑ በአንድ ሊቅ ወይም ፈላስፋ ጥረት ምላሽ ሊያገኝ አልቻለም። በረጅም ዘመን ጥረት

በኋላ እንቅ ፈላስፋ እንቅን ባሕርይ፣ ሌላው የቀረውን በመግለጽ በተለያዩ የዕውቀት መስኮች በተደረሰባቸው አዳዲስ ዕውቀቶች በመመሥረት በመጨረሻ ላይ ኢንግልስ እንዳስቀመጠው "ማናቸውም ተፈጥሮ ከትንሽ እስከ ትልቁ፣ ከአሸዋ ብናኝ እስከ ፀሐዮች፣ ከሕዋስ እስከ ሰው ድረስ ያሉት ሕልውና መሠረት ዘላለማዊ በሆነ ሕይወት ማግኘት /መወለድ/ ሕይወት ማጣት/መሞት/ በማያቋም ሂደት፣ በማያቋርጥ እንቅስቃሴና ለውጥ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ተረጋገጠ።

የሰው ልጅ ስለ ተፈጥሮ በመጨረሻ ላይ በደረሰበት ዕውቀት መሠረት ሰው ራሱ ቀስ በቀስ የመጣ፣ ከእንስሳነት ወደሰውነት ለመድረስ በሚሊዮን የሚገመቱ ዓመታት የፈጀበት መሆኑ ተረጋገጠ። ሰው ራሱን ከእንስሳነት ዓለም ለመለየትና ኅብረተሰብም ለመመሥረት ባለፈባቸው ውስብስብ ሂደቶች ውስጥ ሥራ ከፍተኛውንና ወሳኝ የሆነውን ሚና ተጫውቷል። እርግጥ ከሰው በፊት ሥራ አልነበረም። የመጀመሪያው ሰው መሰል ዘርዮቻችን ራሳቸውን ከተናካሽ ፍጡሮች ለመከላከልና ምግብ የሚሆናቸውን ለመያዝ የሚጠቀሙት ከተፈጥሮ እንዳሉ በተገኙ ቁሶች ነበር። ሰው በዚህ ዕድገት ደረጃው መሠረታዊ ፍላጎቶቹን የሚያረካው በተፈጥሮ እንዳሉ በጥሬ በሚያገኛቸው ቁሶች በመሆኑ ከእንስሳት የሚለይ አልነበረም። ከረጅም ጊዜ ዕድገት በኋላ ቀስ በቀስ በኋላ እግሮቹ ቆሞ በመሄድ የፊት እግሮቹ ነፃ ወጡ። የፊት እግሮቹ ለመሄጃ፣ ለመራመጃ ከማገልገል ነፃ ሲወጡ እንዳንድ ገርደፍ መሣሪያዎችን በእጁ መሥራት ጀመረ። ከነዚህ ገርደፍ መሣሪያዎች ጋር በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያስገኘው ሥራ፣ በሰብአዊ መልኩ እየተከሰተ መጣ።

ከመሣሪያዎች ማምረት ጋር የተከሰተው ሥራ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ ሁለት መሠረታዊ ለውጦች አስከትሏል። አንደኛው የሰውን ተፈጥሮ የሚመለከት ነው። የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማርካት በመሣሪያዎች

ለማኸኘነት ማምረት፣ መሥራት ከጀመረ ወዲህ ተፈጥሮው ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ብቻ ሳይሆን ከሚያደርገው እንቅስቃሴም ጋር እየተዋሃደ መጥቷል። ስለሆነም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት የፈጀ ቢሆንም የከንፉና የእጆቹ እንቅስቃሴና ቅርጽ፣ የጣቶቹ የመላው ሰውነቱ ቅርጽ፣ እንቅስቃሴና ተግባር እንዲሁም አዕምሮው ጭምር እየዳበረ ለመጣ የቻለው የራሱን ተፈጥሮ ሥራ ከሚጠይቀው እንቅስቃሴ ጋር ለማዋሃዱ ባደረገው ጥረት ነው።

ሥራ ከመጀመሪያውም የጋራ ጥረትን የሚጠይቅ ማኅበራዊ ተግባር ነበር። ስለሆነም የሰው ልጅ ከእንሰሳት ደረጃ ከፍ ብሎ ማምረት ሲጀምር እርስ በርስ ግንኙነት በመፍጠሩ በማኅበር ለመሰባሰብ ችሏል። በዚህ የማምረት ሂደት ውስጥ ሰዎች እርስ በርሳቸው ሃሣብ ለሃሣብ ለመለዋወጥ በመቻላቸው ንግግርና ቋንቋ ሊዳብሩ ችለዋል። ስለዚህ የንግግር፣ ቋንቋ ግንኙነትና ህብረተሰብ መቋቋም መሠረት ሥራ ነው። ይህ ሥራ በሰው ተፈጥሮ ላይ ያስገኘው ሁለተኛው ለውጥ ነው። ኤንግልስ እንዳለውም "ከመጀመሪያ ሥራ፣ ከእሱም በኋላና ከእሱ ቀጥሎ ንግግር" የሰውን ልጅ አዕምሮ ከእንሰሳት የበለጠ ለማዳበር ረድቷል። ከአዕምሮ ዕድገት ጋር የአምስቱ ሕዋሳት መዳበር ለሥራና ለቋንቋ በይበልጥ መዳበር አመቺ ሁኔታን ፈጠረ። በዚህ ዓይነት የአንዱ ዕድገት ለሌላው የተሻለ መሠረት በመፍጠር ከህብረተሰብ መመሥረት ጋር በአካሉ፣ በእጁ፣ በአዕምሮውና በሕዋሳቱ /ማየት፣ መስማት፣ ማሽተት፣ መዳሰስ፣ መቅመስ/ ባሕርይ የሰው ልጅ ከእንሰሳነት ፈጽሞ የተለየ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሏል። በመጀመሪያዎቹ ሰው መሰል ዝርያዎቻቸንና በመጨረሻው ሰው መካከል በሚሊዮን የሚገመት ዓመታት የዕድገት ጊዜ አልፏል። በሁለቱ መካከል የምናየው መሠረታዊ ልዩነት ግን ኤንግልስ እንዳስቀመጠው "ሥራ ነው"። ስለዚህ ሥራ ሰውን ሰው አደረገው ለማለት ይቻላል።

ሥራ ደ የመሬቱ ይሰ ዐይነቶ መሠረቶ በመሆኑ ባሕርይው የህብረ ተሰቡ ዕውነቶ ከጣውያ በግል ማኅበራዊ ኑሮ ጋችና በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ማኅበራዊ ግንኙነት ይወሰናል። በጥንታዊ የጋር ዮሽ ሥርዓት ማኅበር ህብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ከተፈጥሮ የሚያገኙት ቁሶች /መሬት፣ መረት፣ ማዕድን/ እ ነዚህን ወደምርት ነት ለመለወጥ የሚጠቀሙባቸው ቀና ቀና የማምረቻ መሣሪያዎች በኅብረ ተሰቡ በወል የተያዙ በመሆና ቸው በዚህ ሥርዓት ማኅበር ውስጥ ሥራም በእኩ ልነትና በጋራ ጠረዳዳት ላይ የተመሠረተ ነው። የሥራም ውጤት /ምርት/ በአባሎቹ በእኩልነት ይከፋፈላል። ከዚህም በላይ ምንም መሠረት አንዳለ በትና አንዱት መሠረት አንዳለበትም የሚለጠፉ በጋራ በአምራቾች በመ ሆኑ ሁሉ ቸው እኩል ጣቢትና ለምርት ሂደት ባይተዋር አለ ነበረም። ስለሆነም በጥንታዊ የጋር ዮሽ ሥርዓት ማኅበር ውስጥ የሰው ኀብረት በግና ፍጹም ዓይነት የዝበራ ነፃ ነበር።

ከዚህ ቀጥሎ በተከሰቱት በባሪያ፣ በፊውዳሉና በካፒታሊስት ሥርዓቶች ግን ኅብረ ተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት የሚያበረ ክተው መሠረታዊ ነገሮች በግል በመያዛቸው ሥራም የተለየ ባሕርይ እየ ያዘ መጣ ታል። በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ለምሳሌ ባሪያው በኃይል በጌታው ተገዶ የተያዘ የማምረቻ መሣሪያዎችም ሆኑ ምርት ለማምረት የሚያገለግሉ ቁሶች ባለቤት ባለመሆኑ የማምረት ኃይሉ አንዳይቀነስ ጌታው ከሚያበላውና ከሚያጠጣው በስተቀር በሥራው ውጤትም ሆነ በምርት ሂደት ውስጥ በሚደረጉት ውሳኔዎች ምንም ዓይነት ተሳትፎ አይደረገውም። በፊውዳሉም ሥርዓት ጭሰኛው ጠንካራ መሬትና የማምረቻ መሣሪያ ቢኖረውም ከሚያመርተው ከፊሉን ለባለርስቱ ከማስገረሉም በላይ ለፊውዳሉ በየጊዜው ነፃ የሥራ አገልግሎት ያበረክታል። በካፒታሊስት ሥርዓት አምራቹ /ሠራተኛው/ ጉልበቱ ከምንም ዓይነት የማምረቻ መሣሪያና ለምርት የሚ

ያገለግሉ ነገሮች ባለቤትነት ስለ ተወገደ የሚተዳደረው ጉልበትን በመሸጥ ብቻ ይሆናል። በሚያመርተው የምርት ውጤት ባይ ነት፣ መጠንና አመራረት ዘዴ ምንም ድምጽ ስለሌለው ሠራተኛው ለምርቱ ውጤትና ሂደት ባይተዋር ይሆናል። ስለዚህ በዚህ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ሠራተኛው ሥራን የሚሠራው በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማግኘት እንዲያስችለው በመሆኑ ሥራ የገዳጅ መልክ ይይዛል። በዚህም የተነሣ የአዕምሮና የአካል ችሎታውን ሙሉ በሙሉ ሊያዳብር አይችልም። በአጠቃላይ መሬትና ሌሎችም የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ከተፈጥሮ የምናገኛቸው ቁሶችና የማምረቻ መሣሪያዎች በጥቂት የህብረተሰቡ አባላት በግል በተያዘባቸው ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ሥራ በአስፈላጊነት ሳይሆን በጭቁና፣ ለጋራ ብልጽግና ሳይሆን፣ ለጥቂቶች መገደላቀቂያ የሚሠራ በመሆኑ በምዝበራ ላይ የተመሠረተ ነው። ስለሆነም በነዚህ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ሥራ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ አካል መሆኑ ቀርቶ በገዳጅ መልክ ስለሚካናወን ሠራተኛውን ወደ "ሎሣሪያነት" ወይም ዕቃነት ይለውጠዋል።

በህብረተሰብ ዕድገት ውስጥ ሠራተኛው የተገፈፈውን መብት የሚቀዳጀው በሶሺያሊስት ሥርዓተ ማህበር ነው። ለጭቁናና ለመበዝበዙ ምክንያት የሆኑት የማምረቻ መሣሪያዎችና ለምርት የሚያገለግሉ ነገሮች ሁሉ በህብረተሰቡ ቁጥጥር ሥር ስለሚውሉ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሥራ የሕልውና ምንጭ ብቻ ሳይሆን የደስታና የተስፋ ምንጭም ነው። ሠራተኛው ምን እንደሚያመርት፣ እንዴት እንደሚያመርት ስለሚያውቅ ለወዙ ውጤትና ለምርት ሂደት ባይተዋር መሆኑ ቀርቶ ባለቤት ይሆናል። ስለዚህ ሥራም በይበልጥ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ አካል እየሆነ ስለሚመጣ የሠራተኛው የፈጠራ ችሎታም ከጊዜ ወደጊዜ እየዳበረ ይሄዳል።

ለማጠቃለል ከፍ ሲል ከቀረበው ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት መሥራት አለበት። ስለዚህ ሥራ የሰው ልጅ ሕልውና መሠረት ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮ ከሚያገኛቸው ቁሶች ጋር የማቴሪያል ዕድገትም መሠረት ነው። ሥራ ከመጀመሪያው ማኅበራዊ ባሕርይ ያለው በመሆኑ ከህብረተሰብ ውጭ ሊከሰት አይችልም። የህብረተሰብ መቋቋም መሠረቱም ሥራ ነው። የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ተፈጥሮን ለመለወጥ ባደረገው ጥረት የራሱንም ተፈጥሮ ለውጧል። ስለዚህ ሥራ ሰውን ሰው አደረገው ለማለት ይቻላል። በተለያዩ ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ የሥራ ባሕርይም ይለያያል። በእኩልነትና በጋራ ብልጽግና ላይ በተመሠረቱ ሥርዓተ ማኅበሮች ሥራ ለጋራ ጥቅም ይውላል። ከብዝበዛም ነፃ ይሆናል። በብዝበዛና በጭቆና ላይ በተመሠረቱት ሥርዓተ ማኅበሮች ውስጥ ሥራ የብዝበዛ ምንጭ ነው።

## 3.2 የሥራ ተግባሮች

ሥራ የሰው ሕልውናና ማቴሪያል ዕድገት መሠረት እንደመሆኑ የማያቋርጥ ሂደት ነው። በየዕለቱ ሰዎች ለኑሮአቸው መሻሻል፣ ለኅብረተሰብ ደኅንነትና ዕድገት ይሠራሉ፣ ያመርታሉ። ሥራ ለመሥራት ግን የተወሰኑ ነገሮች መሟላት አለባቸው። ይህንን ለማየት በየጊዜው የሚከናወኑትን አንዳንድ ተግባሮች በምሳሌነት ወስደን ለመተንተን እንሞክራለን።

አንበል የተሰማራንበት ሥራ እርሻ ነው። እርሻ ለማረስ ምን ያስፈልገናል? ከሁሉ በፊት ሥራውን ለማከናወን ሙያው ያለው ሰው መኖር አለበት። ቀጥሎ የምንፈልገውን የምርት ዓይነት ሊያፈራልን የሚችል ተስማሚ መሬት መገኘት አለበት። የሁለቱ ሁኔታዎች መሟላት ብቻ ተግባራችንን ለማከናወን አያስችለንም። መሬትን ለመመንጠር፣ ለማረስ፣

ለማለስለስ፣ ለመዝራት፣ ለማረም፣ ለማጨድ፣ የሚያስፈልጉት መሣሪያዎች መሟላት አለባቸው። ለዘር የሚያገለግሉት ፍሬዎችም መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ዘሩ ገና ሌሎችም መሣሪያዎችን ለማጓጓዝ የእርሻውን ውጤት ለመሰብሰቢያና ለማከማቻ ወዘተ... የሚያገለግሉ ቁሶችም ያስፈልጋሉ።

ሌላም ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። እንበል ይህ የፋብሪካ ሥራ ነው። ከሁሉ በፊት አሁንም አስፈላጊው ሙያ ያላቸው ሠራተኞችና የማምረቻ መሣሪያዎች መኖር አለባቸው። የኃይል ምንጭ ያስፈልጋል። የማምረቻ መሣሪያዎች የሚቋቋሙበት መሬትና ቤት ያስፈልጋል። ወደምርትነት የሚለወጡ ጥሬ ዕቃዎችም መዘጋጀት አለባቸው። ይህ ፋብሪካ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ነው ብንል አስፈላጊው የጥጥ ዓይነትና መጠን በቅድሚያ መመረት ይኖርበታል። ከጥሬ ዕቃው ሌላ ጨርቀን የተለያዩ ቀለሞችና ጥንካሬ ለመስጠት የሚያስችሉት ልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮችም መሟላት አለባቸው። የጥሬ ዕቃዎችንና የምርት ውጤትን ለማጓጓዝ፣ ለማከማቻ የሚያስፈልጉት ተሽከርካሪዎችና መጋዘኖች መገዛትና መሠራት አለባቸው። መንገድ፣ ውሃ የመሳሰሉትም አገልግሎቶች መዘርጋት ይኖርባቸዋል።

ከቀረቡት ምሳሌዎች መገንዘብ እንደምንችለው የሥራ ሂደት ሦስት መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን መሟላት ይጠይቃል። እነዚህም፣

ሀ. ሥራ፣ የሰው ልጅ ተግባራዊ ክንዋኔ — ያለዚህ መንቀሳቀስና ስለምርትም ማሰብ አይቻልም። ይህንን ቀደም ሲል በመጠኑም ቢሆን በስፋት ተመልክተነዋል።

ለ. የሰው ሥራ የሚያርፍባቸው ወይም ወደምርትነት የሚለወጡ ቁሶች ወይም ነገሮች፣

ሐ. የማምረቻ መሣሪያዎች ናቸው።

የሥራ ተገብሮች የምንላቸው በሀለተኛው ተራ ቀጥር የተመለከ ቱትን የሚያጠቃልሉ ናቸው። በአጠቃላይ ስንነጋገር የሥራ ተገብሮች የሰው ልጅ በጉልበቱና በመሣሪያዎች አማካኝነት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማምረት በምርት ሂደት ውስጥ ወደ ዕቃነት የሚቀይራቸውና የሚለውጣቸውን ቁሶች ሁሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው።

የሥራ ተገብሮች በሦስት መልክ የሚገኙ ቁሶችን ያጠቃልላሉ። እነዚህም፣

1. የሰው ጉልበት ሳይፈስባቸው፣ ከሰው ሕልውና ውጭ በተፈ ጥሮ እንዳሉ የምናገኛቸው ቁሶች። በዚህ ክፍል መሬት፣ አፈርና ውሃ የመሳሰሉት ይገኛሉ። እነዚህ ሁለንተናዊ የሥራ ተገብሮች ይባላሉ።

2. ባሕርያቸውን በሥራ ኃይል ሳንለውጣቸው ከአካባቢያችን በመቁረጥ፣ በመቆፈር፣ ወይም በማጥመድ የምናገኛቸው ነገሮች። በዚህ ክፍል ከውሃ ውስጥ በማስገር የምን ይዛቸው ዓሣዎች፣ ከደን ውስጥ በመቁረጥ የምናገኛቸው እንጨትና እንዲሁም ከመሬት ውስጥ በመቆፈር የምናወጣ ቸው ማዕድናት ይገኙበታል።

3. ማናቸውም ዕቃ ለማምረት የምንገዛቀምባቸው የጥሬ ዕቃዎችም የሥራ ተገብሮች ናቸው። ምሳሌ ጥጥ፣ ብረት፣ የእህል ዘሮች፣ ወዘተ...

የሥራ ተገብሮች የሚባሉት ከፍ ሲል ያመለከትናቸው ሲሆኑ ቁሶች በምርት ሂደት ውስጥ የተለያየ ጥቅም ስላላቸው አንድ ቁስ በምርት ሂደት ውስጥ እንደሚይዘው ሥፍራ የሥራ ተገብሮ ወይም የሥራ መገልገያ ወይም

ምርት ሊሆን ይችላል። መሬት ለምሳሌ ሁለንተና ዊ የሥራ ተገበር ነው። መሬት ለእርሻ ጥቅም ሲውል ዋና ባሕርይው የሥራ ተገበርነት ነው። በሌላ በኩል መሬት ለአንድ ፋብሪካ ሕንፃዎች መሥሪያ/ማኖሪያ/ ሲያገለግል ግን በተዘዋዋሪ መንገድ ካልሆነ በስተቀር በቀጥታ ፋብሪካው ለሚያመርተው ምርት አስተዋጽኦ አያደርግም። ስለዚህ በዚህ ሁኔታ የሥራ ተገበርነት ባሕርይ አይኖረውም። ሆኖም ፋብሪካው በአየር ላይ ተንጠል ጥሎ ሊያመርት ስለማይችል ለምርት ሥራ መከናወን የማምረቻ መሣሪያዎችን ጥሬ ዕቃዎችንና የምርት ውጤቶችን ለማኖሪያና ለማከማቻ ለሚሠራ ቸው ቤቶች መሬት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በዚህ ረገድ መሬት የሚያገለ ገለው እንደሥራ መገልገያ ነው። ሌላ ምሳሌ እንውሰድ። ወይን ተለቅሞ በፍሬነቱ በቀጥታ ጥቅም ላይ በመዋል ፍላጎትን ሊያረካ ይችላል። በዚህ አገልግሎቱ የወይኑ ባሕርይ የምርትነት ባሕርይ ነው። በሌላ በኩል ይኸው ወይን በፋብሪካ ውስጥ በጥሬ ዕቃነት ጥቅም ላይ ውሎ የወይን ጠጅ ለማምረት ያስችላል። በዚህ ጥቅሙ ወይኑ የምርትነት ባሕርይውን ተቀ እንደጥሬ ዕቃ ስለሚያገለግል የሥራ ተገበር ይሆናል።

የሥራ ተገበሮች ዓይነተኛ ባሕርይ በራሳቸው የማይንቀሳቀሱና የማይለወጡ መሆናቸው ነው። ስለዚህ አንድ ህብረተሰብ በምርት ሂደት ውስጥ የሚጠቀምባቸው የሥራ ተገበሮች ዓይነት የሚገለገልባቸውን ቁሶች ባሕርይ እንጂ የኅብረተሰቡን ዕድገት ደረጃ ወይም በተፈጥሮ ላይ ያለውን የቁጥጥር ደረጃ ሙሉ በሙሉ አያመለክትም። ዛፍ በመጥረቢያ ሊቆረጥና ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። በተመሳሳይ መልክ ስንዴ በበሬ፣ ምፈር ቀንበርና በማረሻ ይመረታል። በትራክተርም ሊመረት ይችላል። የዛፉም ሆነ የስንዴ ጥቅም ላይ መዋል ህብረተሰቡ የሚጠቀምባቸውን የሥራ ተገበሮች ዓይነት እንጂ ህብረተሰቡ በተፈጥሮ ላይ ያለውን የበላይነት ደረጃና የአምራቹን ሕዝብ ምርታማነት አያመለክተንም። ይህንን የሚያመለክተን ዛፉን ለመቁረጥ ወይም ስንዴውን ለማምረት የሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች የቴክኖሎጂ ደረጃ ነው።

## 3.3 የሥራ መገልገያዎች

ሰው የሥራ ተገበሮችን በምርት ሂደት ውስጥ ለመለወጥና ለማምረት በቀጥታ የሚጠቀምባቸው ማምረቻ መሣሪያዎችና እንዲሁም በቀጥታ በምርት ሂደት ውስጥ ባይጠቀምባቸውም ለምርት መከናወን አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ ነገሮች ሁሉ የሥራ መገልገያዎች ይባላሉ። የሥራ መገልገያዎች ሠራተኛው በመተር ኃይልም ሆነ በአካሉ ብቻ የሚጠቀምባቸውን የማምረቻ መሣሪያዎች እና ለምርት ተገባር የሚያገለግሉ ሕንፃዎችን መሬት፣ መንገድ፣ መጋዘኖች፣ የትራንስፖርት መገልገያዎች፣ የመስኖ አገልግሎቶችን የኃይል ምንጭ የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ።

ቀደም ሲል ካቀረብነው ምሳሌ እንደተገነዘብነው የእርሻን ሥራ ለማከናወን እንደህብረተሰቡ ዕድገት ደረጃ የተለያዩ ቢሆኑም የማምረቻ መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ። ከአገራችን ምሳሌ እንውሰድ፤ አብዛኛው ገበሬ የሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች በሬ፣ ሞፈር፣ ቀንበር፣ ወገልና ማረሻ ሲሆኑ በተጨማሪም ለመመንጠሪያ ገጀራ ወይም ቀንጨራ፣ ሰብሉን ለማጨጃ የሚሆን ማጭድ የመሳሰሉትም ያስፈልጉታል። እነዚህ በቀጥታ ለማምረት ተገባር ባይጠቀሙም ለምርት ሂደት መከናወን የሚያስፈልጉ ቁሶች ይኖራሉ። ዘሩንና የምርትን ውጤት መያዣ ስልቻ፣ ማከማቻ ጎተራ ያስፈልጋሉ። ዘሩንም ሆነ ምርትን ለማጓጓዝ በአህያ፣ በፈረስ፣ ወይም በበቅሎ መጠቀም ይኖርበታል። ከዚህም ምሳሌ እንደምንገነዘበው የአንድ ገበሬ የሥራ መገልገያዎች፣

- በሬ
- ሞፈር፣ ቀንበር — የማምረቻ መሣሪያዎች
- ወገል፣ ማረሻ
- ገጀራ፣ ቀንጨራ
- ማጭድ

- ለህያ፣ በቀሎ፣ ፈረስ
- በለቻ
- ጎተራ
- መጧኛ
- ወዘተ...

ለምርት መከናወን የሚያገለግሉ ነገሮ

የመሳሰሉ ናቸው።

ከሥራ መገልገያዎች መካከል በሰው ልጅ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የማምረቻ መሣሪያዎች ናቸው። እንደፍራፍሬ ከመሳሰሉት ከእጅ ሌላ የተለየ የማምረቻ መሣሪያ ከማይጠቀሙት በስተቀር የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ከሥራ ተገብሮችም በፊት የማምረቻ መሣሪያዎች ማግኘት ይኖርበታል። ሰው የመጀመሪያውን የማምረቻ መሣሪያዎች ያገኘው ከተፈጥሮ ነው። ራሱን ከአውሬ ለመከላከል እና የሚፈልጋቸውን ነገሮች ለመቁጧና ለመፍጪያ ያገለገለውን ድንጋይ /የመጀመሪያውን ማምረቻ መሣሪያ/ ያገኘው ከተፈጥሮ ነው። ስለዚህ ማርክስ እንዳለውም ተፈጥሮ ራሷ የሰው ልጅ የመጀመሪያ የማምረቻ መሣሪያ መገኛ ናት። ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደሞከረው ሥራ ራሱ በሰብዓዊ መልኩ የተከሰተው ከማምረቻ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ መዋል ጋር ነው። ሥራ የሰው ልጅ የተለየ ባሕርይ እንደመሆኑ ሁሉ የማምረቻ መሣሪያ የማምረቱም ተግባር የሰው ልጅ የተለየ ባሕርይ ነው። ስለዚህም ሰው ራሱ የማምረቻ መሣሪያ የሚያመርት እንስሳ ነው።

ከሥራ ዕድገት ጋር የሰው ልጅ የሚጠቀምባቸው መሣሪያዎች እየተሻሻሉ በመምጣታቸው ከተጠረቡ ድንጋዮች ተነስተ ዛሬ እጅግ የተራቀቁ መሣሪያዎች ላይ ለመድረስ ተችሏል። እርሻ ለምሳሌ በቀድሞዎቹ ህብረተሰቦች ዘንድ የሚካሄደው በመጀመሪያ መሬትን በእንጨት ቆፈር ቆፈር አድርጎ በመዝራት ነበር። ከዚያም የቤት እንስሳትን ለማዳ

ለማድረግና በበረት ለመጠቀም ሲቻል በእንስሳት ኃይል የሚጎተቱ ማረሻዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ቻሉ።
ቀስ በቀስ የማምረቻ መሣሪያዎች እየዳበሩ በመምጣታቸው ዛሬ በኢኮኖሚ ዕድገት በተራመዱት አገሮች እርሻ ራሱ እንደፋብሪካዎች ሙሉ በሙሉ በዘመናዊ መሣሪያዎች ኃይል የሚካሄድ ተግባር ሆኗል። መሬት የሚመነጠረው፣ የሚታረሰውና የሚከሰከሰው በመኪና ነው። ዘር የሚዘራው በመኪና ነው። ሰብሉ የሚታጨደውና የሚወቃውም እንዲሁ በመኪና ነው።

የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል የሚያስገኘው ዓይነተኛ ጥቅም የሠራተኛውን የማምረት ኃይል/የሥራ ውጤት/ ለማዳበር ወይም ለማሳደግ ማስቻሉ ነው። የተሻሻሉ ማምረቻ መሣሪያዎች ከመጠቀም ጋር የምርት ሂደት አወቃቀር ራሱ እየተሻሻለ ይመጣል። የሥራም ክፍፍል ይበልጥ ይዳብራል። የዚህ ዓይነቱም መሻሻል በአነስ ጊዜና ወጭ ከፍ ያለ ምርት ለማስገኘት ይረዳል። የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻልና ይህም የሚያስገኘው የሥራ ቅልጥፍና የሠራተኛውን ምርታማነት ለማሳደግ ምን ያህል እንደሚረዳ በበሬ የሚያርስ ገበሬና በትራክተር የሚጠቀም ገበሬ መካከል የሚኖረውን የሥራ ውጤት ልዩነት መገመት በቂ ይሆናል። ስለዚህ ከሥራ መገልገያዎች መካከል የሰው ልጅ የደረሰበትን የማቴሪያል ዕድገት ደረጃና በተፈጥሮ ላይ ያለውንም የበላይነት የሚያመለክቱን የሚጠቀምባቸው ማምረቻ መሣሪያዎች ናቸው።

የማምረቻ መሣሪያዎች ሌላ ባሕርይ ሥራ የሚካናወንበትን ማህበራዊ ሁኔታ የሚወስኑ መሆናቸው ነው። ሥራ በግል ማለት በአንድ ሰው ጥረት ወይም በቡድን፣ በጋራ ጥረት ማለት በህብረት ሊካናወን ይችላል። የሥራ ሂደት በአንድ ሰው ጥረት/ግል/ ወይም በቡድን/ሕብረት/ መካሄዱ በግለሰቦች ምርጫ ሳይሆን በማምረቻ መሣሪያዎቹ ባሕርይ የሚወሰን ነው። ይህንን በሚገባ ለመገንዘብ የተለያዩ የማምረቻ መሣሪያዎች በመጠቀም ሊካሄድ የሚችል አንድ ዓይነት የምርት ሂደት

በምሳሌነት እንውሰድ። አገበለ ምሳሌያችን አንድ ሸማኔና የዚህ የምርት ሂደት የተራቀቀ ደረጃ የሆነውን የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የሚመለከት ነው። ሸማኔው በሚጠቀምበት የማምረቻ መሣሪያ የምርቱን ሂደት በአጠቃላይ የሚያከናውነው እራሱ ነው። ስለዚህ የሥራው ሂደት በአንድ ግለሰብ ጥረት የሚጠናቀቅ ነው። የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካውን ብንወስድ ግን ሥራው በልዩ ልዩ መሣሪያዎች የሚቀናጅ እንደመሆኑ የምርት ሂደቱ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሠራተኞችን ህብረት ይጠይቃል። የማምረቻ መሣሪያዎችን ከሚያንቀሳቅሱት በተጨማሪ የኃይል ምንጩን የሚያካሂዱ፣ ጥሬ ዕቃውን የሚያቀርቡ፣ የተመረተውን የሚያከማቹና ለአምራች ሠራተኞች ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ሌሎች ሠራተኞችም ያስፈልጋሉ። ስለዚህ ፋብሪካው ሙሉ በሙሉ ምርታማ እንዲሆን እንደማምረቻ መሣሪያዎች አቅም የብዙ መቶ ወይም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን የጋራ ጥረት ይጠይቃል። ይህ ሥራ ከሸማኔው ጋር ሲወዳደር ይበልጥ ማህበራዊ እንደሆነ ግልጽ ነው። በአጠቃላይ በአብዛኛው በመሣሪያ ኃይል የሚከናወኑ ተግባሮች የሥራ ሁኔታ ህብረትን የሚጠይቅ ሲሆን የማምረቻ መሣሪያ ኋላ ቀርና በእጅ ሥራ መልክ የሚካሄዱ ተግባሮች የሥራ ባሕርይ ግን በግል ጥረት የሚከናወን ነው። ስለሆነም ይዘታው ግላዊም ሆነ ህብረተሰባዊ የማምረቻ መሣሪያዎች ሥራ የሚካሄድበትን ማህበራዊ ሁኔታ ይወስናሉ።

## 3.4 የምርት መገልገያዎች

የምርት ሂደት ከውጤቱ ማለት ከሚመረተው ምርት አንፃር ሲታይ በሂደቱ ውስጥ ልዩ ልዩ አገልግሎት ያላቸው የሥራ ተግባሮችና የሥራ መገልገያዎች በጥቅሉ የምርት መገልገያ ተብለው ይጠራሉ። አሁንም ቀደም ሲል ከጠቀስነው ምሳሌያችን ብንወስድ በሬ፣ ሞፈር፣ ቀንበር፣ ወገል፣ ማረሻ፣ ገጀራ፣ ቀንጨራ፣ ማጭድ፣ ጎተራ፣ ስልቻ፣ ወዘተ... የመሳሰሉት የሥራ መገልገያዎችና መሬትና ዘር የመሳሰሉት

በዚህ ሂደት ውስጥ በሥራ ተገብሮነት የሚያገለግሉት ቁሶች በጥቅል የምርት መገልገያ ይባላሉ። አጠራሩ ራሱ እንደሚጠቁመው ማናቸውም አንድን ምርት ለማምረት የምንጠቀምባቸው ቁሶች ሁሉ በምርት መገልገያ ውስጥ ይጠቃለላሉ።

የምርት መገልገያዎች መሬት፣ ማዕድን፣ የመሳሰሉትን የሥራ ተገብሮች፣ የማምረቻ መሣሪያዎችና ሌሎችም ለምርት ሂደት ከንዋኔ አስፈላጊ የሆኑ ቁሶችና አገልግሎቶችን ባጭሩ ለአንድ ህብረተሰብ ኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ መሠረቶችን ያጠቃልላሉ። የምርት መገልገያዎች የህብረተሰብ የማቴሪያል ዕድገት መሠረት እንደመሆናቸው ይዞታቸው የህብረተሰቡ አባላትን የምርት ውጤት ድርሻ/ገቢ/ና እንዲሁም በምርት ሂደቱና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚኖረውን ማኅበራዊ ሥፍራ ይወስናል። ይህንን መሠረተሃሣብ በሚገባ ለመገንዘብ በተለያዩ ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ የሚኖረው የምርት መገልገያዎች ይዞታ የሚያስከትለውን ሁኔታ ባጭሩ እንመለከት።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማኅበር ህብረተሰቡ የሚጠቀምባቸው የማምረቻ መሣሪያዎች እጅግ ኋላቀር በመሆናቸውና የሥራ ክፍፍልም እምብዛም ባለመዳበሩ የምርት መገልገያዎች በአምራቾች የወል ይዞታ ሥር ነበሩ። ህብረተሰቡ በዚህ የዕድገት ደረጃው መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማርካትና ሕልውናውን ለማረጋገጥ በጋራ ከመሥራት ሌላ አማራጭ ስላልነበረው የምርት መገልገያዎችም በጋራ መያዛቸው አስፈላጊ ነበር። የምርት መገልገያዎች በወል የተያዙ በመሆናቸው የምርት ውጤት በአምራቾች መካከል በእኩልነት ይከፋፈል ነበር። ስለሆነም የግል ልዩነትና ብዝበዛ አልነበረም። መደቦችም ሊፈጠሩ አልቻሉም።

በማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻልና ይህም ባስከተለው የሥራ ክፍፍል መዳበር የጥንታዊው የጋርዮሽ ሥርዓት ሲወድቅ የግል ይዞታ ማቆጥቆጥ በመጀመሩ የምርት መገልገያዎች የግለሰቦችና የቡድኖች ሀብት ሆኑ። መሬት፣ ከብቶችና ሌሎችም የምርት ምንጮችና የማምረቻ መሣሪያዎች በግል በመያዛቸው የምርት ውጤትም በወል መከፋፈሉ ቀርቶ በምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ይወሰን ጀመረ። ስለሆነም ከጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት በኋላ በምርት መገልገያዎች የግል ይዞታ ላይ በተመሠረቱት በባሪያ፣ በፊውዳልና በካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ ከሚመረተው ምርት አብዛኛው እጅ በምርት መገልገያዎች ባለቤቶች ቁጥጥር ሥር ዋለ። ከግል ይዞታ መስፋፋት፣ የሥራ ክፍፍል መዳበርና የሥራ ውጤት ማደግ ጋር የምርት መገልገያ ባለቤቶች በሌሎች ጉልበት የሚተዳደሩበት ሁኔታ ተፈጠረ። በአንፃሩ የምርት መገልገያ ባለቤት ያልሆኑት ምርጫ ጉልበታቸውን በመሸጥ መተዳደር ብቻ ሆነ።

የምርት መገልገያዎች በግል መያዝ ቀጥተኛ ውጤት ህብረተሰቡን ሀብታምና ደሃ፣ "ያላቸውና የሌላቸው" በማለት በኑሮ ደረጃ መለየቱ ነው። ይህም የገቢ ልዩነት በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ሥፍራ ይወስናል። ስለዚህ ከምርት መገልገያዎች የግል ይዞታ ጋር መደቦች ይፈጠራሉ። በዚህ መሠረት በግል ይዞታ ላይ በተመሠረቱ ሥርዓተ ማህበሮች ውስጥ የባሪያና የጌታ፣ የገባርና የባለመሬት፣ የወዛደርና የካፒታሊስት መደቦች ለክሰቱ ችለዋል።

## 3.5 የምርት ኃይሎች

የምርት መገልገያዎች ማለት የሥራ ተገብሮችና የሥራ መገልገያዎች በራሳቸው የምርት ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም። ምንም ያህል የተራቀቀ ቴክኖሎጂ ቢሆን ያለሰው ዋጋ የለውም። በመጀመሪያም ያለሰው

ተሳትፎ የሥር ተገበሮች ወደ ማምረቻ መሣሪያነትም ሊለወጡ አይችሉም። የማምረቻ መሣሪያዎችንና የሥራ ተገበሮችን አንቀሳቃሹ ኃይል ሰው እንደመሆኑ ምርት ያለሰው ተሳትፎ ሊታሰብ አይችልም። ስለዚህ የምርት መገልገያዎችና የነዚህ አንቀሳቃሽ የሆነው የሰው ኃይል በጥቅል የምርት ኃይሎች ተብለው ይጠራሉ። የምርት ኃይሎች ስንል ከምርት መገልገያዎች ጋር የሰው የምርምር ውጤት የሆኑትን ሳይንስን፣ ቴክኖሎጂንና ጥበብን ያጠቃልላል። እርግጥ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና የሰው ዕውቀት ደረጃ ህብረተሰቡ በሚጠቀምባቸው ማምረቻ መሣሪያዎች መንፀባረቃቸው አይቀርም። እዚህ ላይ በተለይ የጠቀስናቸው የምርት ኃይሎች ዕድገት የዕውቀት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት መሆኑን ለመጠቆም ያህል ብቻ ነው።

የምርት ኃይሎች ዓይነተኛ ባሕርይ አዳጊ መሆናቸው ነው። ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ሰው በረጂም ዘመን ታሪኩ በድንጋይ ከመጠቀም ተነስቶ ዛሬ በጣም የተራቀቀ መሣሪያዎች የሚጠቀምበት ደረጃ ደርሷል። ይህ የማምረቻ መሣሪያዎች ዕድገት የሰው ጥረት ውጤት እንደ መሆኑ ከማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻል ጋር የአምራቹም ሕዝብ ሙያ፣ ዕውቀትና ምርታማነት ከጊዜ ወደጊዜ እየዳበረ መጥቷል። ስለዚህ የማምረቻ መሣሪያዎች ዕድገት የምርት ኃይሎች ዕድገት ነው። የምርት ኃይሎች ዕድገት መንስዔ ምንድነው? ይህንን ቀጥለን ባጭሩ እንመለከታለን።

የምርት ኃይሎች ዕድገት መሠረት ሰው ኑሮውን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማሻሻልና ከፍተኛ እድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ያለው የማያከትም ፍላጎት ነው። ይህንን ፍላጎቱን እውን ለማድረግ የኑሮው ምንጭ ከሆነችው ከተፈጥሮ ጋር የማያቋርጥ ትግል ማካሄድ ይኖርበታል። ተፈጥሮ የሰው ሀብት ምንጭ የመሆኗንም ያህል አስከፊ ገጽታዎችም አሏት። ስለዚህ ይበልጥ በማምረት ፍላጎቶችን ለማርካትና

የተደላደለ ኑሮ ለመኖር የተፈጥሮን አስከፊ ገጽታዎች በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ባደረገው የማያቋርጥ ትግል ከጊዜ ወደ ጊዜ የማምረቻ መሣሪያዎችንና የሥራ መገልገያዎችን እያሻሻለ መጥቷል። ከማምረቻ መሣሪያዎችና የሥራ መገልገያዎች መሻሻል ጋር አዳዲስ የሥራ ተገብሮች በጥቅም ላይ እየዋሉ በመምጣታቸው በዚህ ሂደት ውስጥ ሰው ስለ ተፈጥሮ ያለው ዕውቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ መምጣ ችሏል። ከዕውቀት ዕድገት ጋር የሳይንስ በጥቅም ላይ መዋል ለምርት ኃይሎች ዕድገት የተሻለ መሠረት እያስገኘ መጥቷል።

ባጭሩ የምርት ኃይሎች ዕድገት መሠረት ሰው ሕይወቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማሻሻል ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርገው ትግል ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ የማምረቻ መሣሪያዎች መሻሻልና የሰው ዕውቀት ከምችት መጨመር የምርት ኃይሎችን በተከታታይ ለማዳበር አስችሏል። ስለዚህ የምርት ኃይሎች ሁኔታ ሰው የደረሰበትን ዕድገት ደረጃና በተፈጥሮም ላይ ያለውን የበላይነት ያመለክታል።//

## 3.6 የምርት ግንኙነት

ሰዎች በግለሰብነት ለብቻቸው ከሌሎች ጋር ግንኙነት ባይኖራቸው ሊያመርቱ አይችሉም። ቀደም ሲል እንደተገለጸውም ሰው ከእንስሳነት ዓለም ለመለየትና ራሱን ለማዳበር የቻለው ከመሰሎቹ ጋር በነበረው ግንኙነት ወይም ማህበራዊ ኑሮ በመመሥረቱ ነው። ስለሆነም የማምረት ሂደት ምንጊዜም በሕርይው ማህበራዊ ነው።

ህብረተሰብ በደረሰበት የመጀመሪያው ታሪካዊ የዕድገት ደረጃው የመሠረተው የምርት ሂደት በጋራ ጥረት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ማህበራዊ ባሕርይው በማያጠራጥር መልክ ጎልቶ ይታይ ነበር።

የምርት ኃይሎች ዕድገትና ባሕርይ የግል ንብረት እንዲያቆጠቁጥ ቢያደርግም በአጠቃላይ ግን የኅብረተሰብ የማምረት ተግባር ማህበራዊ ባሕርዮን አልለወጠም። የሥራ ክፍፍል መመሥረት የሸቀጥ ምርትና የዕቃዎች ልውውጥ መከሰትና ዕድገት አያንዳንዱ አምራች በሌሎች የበለጠ እንዲደገፍ ስላደረገው የምርት ሂደት ማህበራዊ ባሕርይ እየዳበረ ሊመጣ ችሏል።

በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል ብዙ ዓይነት ግንኙነቶች ሊመሠረቱ ይችላሉ። አንድ ፋብሪካን እንደምሳሌ እንውሰድ። እንበል ይህ ፋብሪካ /የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ/ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ በፋብሪካው ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ በሚሠሩት ሠራተኞች መካከል የሚፈጠር ግንኙነት አለ። የማዳወሪያ ክፍል ከቀለም ክፍሉ ሠራተኞች፣ የጥሬ ዕቃው ክፍል ከማምረቻው ክፍል ሠራተኞች ወዘተ... የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት የምርት ቴክኒካዊ ግንኙነት ይባላል።

ሰዎች በምርት ሂደት ውስጥ የሚፈጥሩት ግንኙነት ይህ ብቻ አይደለም። ሌላም ግንኙነት አለ። የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች ከሆኑት ከጥጥ አምራቾች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል። የማምረቻ መሣሪያዎችን ከሚያቀርቡለት ሌሎች ፋብሪካዎች ጋር ግንኙነት ይኖረዋል። በሠራተኛውና በአሠሪዎቹም መካከል የሚፈጠር ግንኙነት አለ። በመጨረሻም የምርቱ ውጤት ተጠቃሚ ከሆነው በላተኛ /ሸማች/ ሕዝብም ጋር ግንኙነት ይኖረዋል። ይህ ግንኙነት ከመጀመሪያው ዓይነት ግንኙነት የተለየ ነው። ሁለተኛው ግንኙነት ዕቃዎች መለዋወጥና ስአጠቃላይ ከጥቅም ጋር የተሳሰረ በመሆኑ መሠረቱ ቁሳዊ ነው። የምርት ግንኙነት ስንል የምንመለከተው ይህንን ዓይነት በሰዎች መካከል በቁሳዊ መሠረት ላይ የሚገነባውን ግንኙነት ነው። ስለሆነም ሰዎች የማቴሪያል ሀብት

በማምረት፣ በማሠራጨትና በመለወጥ ሂደት ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚፈጥሩት ግንኙነት የምርት ወይም የኢኮኖሚ ግንኙነት ይባላል።

የምርት ግንኙነት ባሕርይ በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ይወሰናል። በመሠረቱ የምርት መገልገያዎች በህብረተሰቡ አባላት በማህበር ወይም ከህብረተሰቡ አባላት መካከል በጥቂቶች በግል ሊያዙ ይችላሉ። የይዞታቸው ባሕርይ በሰዎች መካከል በምርት ሂደት ውስጥ የሚፈጠረውን ግንኙነት ባሕርይ ይወስናል። ስለሆነም የምርት መገልገያዎች በማህበር በተያዘባቸው ህብረተሰቦች ውስጥ በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት በእኩልነትና በጋራ መረዳዳት ላይ የተመሠረተ የጋርዮሽ የምርት ግንኙነት ይሆናል። የምርት መገልገያዎች በጥቂቶች ቁጥጥር ሥር በሆኑባቸው ህብረተሰቦች ውስጥ ግንኙነቱ የሚመሠረተው በእኩልነት ባይሆን የምርት መገልገያዎች ባለቤት በሆኑና ከሥራቸው በስተቀር ምንም ዓይነት የምርት መገልገያ በሌላቸው መካከል ስለሚሆን ግንኙነቱ በጭቆናና በምዝበራ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

## 3.7 ስለ ተምርት

እስከአሁን ድረስ አንዳንድ ጽንሰ ሃሣቦችን ቀለል ባለ መንገድ በመግለጥ የምርት ሂደትን በልዩ ልዩ መልኩ ለማመልከት ሞክረናል። ቀጥለን ሂደቱን በጥቅል ለማየትና ያሉትን ውስብስብ ግንኙነቶች ለማብራራት እንሞክራለን።

ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት የሚያከናውኑት የምርት ሂደት በማንኛውም የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ህብረተሰብ ሁለት መልኮች አሉት። እነዚህም የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ናቸው። የምርት ኃይሎች የሚያመለክቱት ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፣

ሰዎች በምርት ሂደት ውስጥ ከቴፕሮ ጋር ያሳቸውን ግንኙነት ነው። የምርት ወይንም የኢኮኖሚ ግንኙነቶች የምንላቸው ደግሞ የሚያመለክቱት በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶችን ነው። እነዚህ ሁለት ዓይነት ግንኙነቶች አንድ ህብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት እንዴት እንደሚያመርትና በምን እንደሚያመርት የሚያመለክቱ የማይነጣጠሉ የምርት ሂደት ገጽታዎች የሚያመለክቱት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች በአንድነት ስለ ተምርት ዝባለው ይጠራሉ። በሌላ አገላለጽ ሰዎች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት እንዴት እንደሚያመርቱ፣ በምን እንደሚያመርቱ፣ ያመረቱትን ምርት እንዴት እንደሚካፈሉ፣ እንደ ሚለዋወጡና በምርትና በልውውጥ ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት በአጠቃላይ ስለ ተምርት ይባላል። ስለዚህ ስለ ተምርት አንድ ህብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቱን የሚያረካባቸውን ዘዴዎች የሚያጠቃልል ነው።

ህብረተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚያረካባቸው ዘዴዎች ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተወሰኑ ሳይሆኑ ህብረተሰቡ እንደ ደረሰበት የዕድገት ደረጃ የሚለወጡ ናቸው። ስለሆነም ስለ ተምር ቶች ህብረተሰብ የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ በማንፀባረቅ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ፣ ደረጃ በደረጃ የማደግና የመለወጥ ባሕርይ አላቸው። በዚህ መሠረት በሰው ልጅ ረጅም ታሪክ ውስጥ አምስት ስለ ተምር ቶች ተከስተዋል። እነዚህም፡—

— የጥንታዊ ጋርዮሽ ስለ ተምርት

— የባሪያ አሳዳሪ ስለ ተምርት

— የፊውዳል ስለ ተምርት

— የካፒታሊስት ስለ ተምርት

— የሶሺያሊስት ስለ ተምርት የሚባሉት ናቸው። አንዱ ስለ ተምርት ከሌላው የሚለየውና የአያንዳንዱም ስለ ተምርት ማህበራዊ

ባሕርይ የሚወስነው በምርት ግንኙነት ነው። ስለዚህ ከአንድ ስልተ ምርት ወደሌላ ስልተ ምርት ለመሸጋገር የአሮጌው ስልተ ምርት የምርት ግንኙነት በአዲሱ ስልተ ምርት የምርት ግንኙነት መለወጥ ወይም መተካት አለበት። ህብረተሰብ ከአንዱ ስልተ ምርት ወደ ሚቀጥለው ከፍተኛ ስልተ ምርት እንዴት እንደሚሸጋገር ለመረዳት በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል ያለውን አንድነትና ቅራኔ መገንዘብ ያሻል።

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የምርት ኃይሎች አንድ የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በጊዜው ከነበሩና እስከዚያ ጊዜ ድረስ ከሞላ ጎደል የመጣጣምና የመደጋገፍ ግንኙነት ከነበራቸው ከምርት ግንኙነቶች ጋር የተፋፋመ ቅራኔ ይኖራቸዋል። ቅራኔው የሚፋፋምበትም ምክንያት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች እድገታቸው ስለማይመጣጠን ነው። ስለሆነም በጊዜው የነበሩት የምርት ግንኙነቶች ለምርት ኃይሎች ዕድገት አመቺ መሆናቸው ያበቃና እንደማነቆ በመሆን ይገቶታል። በዚህን ጊዜ ከአዲሱ የምርት ኃይሎች ዕድገት ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የምርት ግንኙነቶች ያስፈልጋሉ።

ለህብረተሰብ ማቴሪያል ዕድገት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች መጣጣም አስፈላጊ ቢሆንም የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ግን ተመሳሳይ ባሕርይ የላቸውም። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ሰው በየጊዜው እያደጉ የሚሄዱትን መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማርካትና የተፈጥሮን አስከፊ ገጽታዎች በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ባለው የማያቋርጥ ፍላጎት የምርት ኃይሎች ከጊዜ ወደጊዜ እያደጉና እየዳበሩ የመሄድ ባሕርይ አላቸው። በሌላ በኩል የምርት ግንኙነቶች የምርት መገልገያዎችን ይዞታና የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍሎች ማኅበራዊ ሥፍራና ጥቅም የሚመለከት እንደመሆናቸው ከምርት ኃይሎች ጋር ሲነፃፀሩ የወግ አጥባቂነት ወይም ለውጥን የመቋቋም ባሕርይ አላቸው።

ይህም ማለት የምርት መገልገያ ባለቤት የሆነው መደብ ጥቅሙ አንዳይ ነካና የምርት መገልገያዎች የኅብረተሰባዊ ይዞታ እንዳይኖራቸው ስለሚከላከልና አፍኖ ስለሚይዝ ነው። በመደብ በተከፋፈለ ኅብረተሰብ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የሚፈጠር ቅራኔ የሚፈታው፣ ማለትም አሮጌዎቹ የምርት ግንኙነቶች በአዲስ የምርት ግንኙነቶች ሊተኩ የሚችሉት፣ የሶሻል አብዮትን በማካሄድ ነው። በመሠረቱ ሶሻል አብዮት በባሪያው ሥርዓት በባሪያ አሳዳሪውና በባሪያው መካከል፣ በፊውዳሉ ሥርዓት በባለመሬቱና በገበሬ መካከል፣ በካፒታሊስት ሥርዓት በካፒታሊስቱና በወዝአደሩ መካከል የሚካሄድ የመደብ ትግል ውጤት ነው።

ለመሆኑ መደብ ስንል ምን ማለታችን ነው? ሌኒን አንዳለው፣

"መደቦች፣ በታሪክ በተወሰነ በአንድ ማኅበራዊ የማምረት ቅንብር ውስጥ .. ዙት ሥፍራ፣ ከምርት መገልገያዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት/ይህና ግንኙነት ብዙውን ጊዜ በሕግ የተወሰነና የተደነገገ ነው/፣ በሥራ ማኅበራዊ ቅንጅት ውስጥ በሚኖራቸው ሚናና በዚህም ሳቢያ በሚከናወነው የማኅበራዊ ሀብት ክፍያ የማግኛ ዘዴና መጠን የሚለያዩ ትላልቅ የሰዎች ክምችቶች ናቸው። መደቦች በአንድ በተወሰነ ማኅበራዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ ሥፍራዎችን በመያዛቸው አንዱ ሌላውን የሚበዘብዘበት የሰዎች ክምችቶች ናቸው"። /ሌኒን፣ ምርጥ ሥራዎች፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 248/።

ለምሳሌ በካፒታሊስት ስልተምርት ውስጥ የካፒታሊስቱ መደብና የወዝአደሩ መደብ ሁለቱ ዋና /መሠረታዊ/ መደቦች ናቸው። የካፒታሊስቱ መደብ የምርት መገልገያዎችን በግል ንብረትነት የያዙ ግለሰቦችን የሚያቅፍ ሲሆን የወዝአደሩ መደብ አባላት ግን ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት የተነጠሉ፣ ለመኖር ብቻ ለካፒታሊስቶች በደመወዝ ተቀጥረው ጉልበታቸውን በመሸጥ የሚኖሩ ናቸው። በባሪያ አሳዳሪው

ስልተ ምርት ውስጥ ባሪያ አሳዳሪውና ባሪያው፣ በፊውዳሉ ስልተ ምርት ውስጥ ፊውዳሊስቱና ገባሩ ሌሎች ዋና /መሠረታዊ/ መደቦች ናቸው። አንድ ስልተ ምርት ገናና በሰፈነበት ሕብረተሰብ ውስጥ የወደቀው ስልተ ምርት ቀሪት /ርዝራዥ/ መደቦችና አዲስ ስልተ ምርት ማቆጥቆጡን የሚያበስሩ የሽግግር መደቦች ሊገኙ የሚችሉ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም።

የምርት ግንኙነቶች እንደማነቆ በመሆን የምርት ኃይሎችን እድገት እፍነው በሚይዙበት ጊዜ በበዝባዥ መደብና በተበዝባዥ መደብ መካከል የነበረው ቅራኔ ይፋፋምና ለሶሻል አብዮት ፍንዳታ ዋና መሠረታዊ መንስዔ ይሆናል።

የምርት ግንኙነቶችና የምርት መገልገያዎች ማኅበራዊ በሆኑበትና የሰው በሰው መበዝበዝ በጠፋበት በሶሺያሊስት ህብረተሰብ ውስጥ የምርት ግንኙነትና የምርት ኃይሎች አብረው ስለሚዳበሩና ተፃራሪ ቅራኔ ስለሌለ የሶሻል አብዮት አያስፈልገም። በሶሻሊስት ህብረተሰብ በምርት ሂደት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ አንዳንድ ችግሮችም ቢኖሯ 'በመግባባትና በመወያየት ይወገዳሉ።

በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የሚገኘውን አንድነትና ቅራኔ ለማብራራት አንዳንድ ስልተ ምርቶችን ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንመልከት። በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር የምርት ኃይሎች እጅግ ኋላ ቀር የእድገት ደረጃ ላይ ይገኙ ነበር። አንድ ሰው በግሉ ገርደፍ መሣሪያዎችን በመጠቀም ከተፈጥሮና ከዱር እራዊት ጋር የነበረውን ቅራኔ ተቋቁሞ ለመኖር እጅግ ያዳግተው ነበር። ስለዚህ በዚያ ደረጃ ሰዎች የማምረቻ መሣሪያዎቻቸውን በጋራ ይጠቀሙባቸውና ምርትም የጋራ ስለነበረ በእኩልነት በግለሰቦች መካከል ይከፋፈል ነበር። እንዲህም ሆኖ የሥራ ምርታማነት ከዝቅተኛነት የተነሣ ፊሰስ ሊያስገኝ አልቻለም ነበር።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር ውስጥ የምርት ኃይሎች ቀስ በቀስ እያደጉ ሄዱ። ሥርዓተ ማኅበሩ በአርሻ፣ በከብት ርቢ፣ በዕደ ጥበባትና በመሳሰሉት መስኮች ያሳየው መሻሻል በውስጡ ከተከናወኑት የምርት ኃይሎች ዕድገት ተነጥሎ የሚታይ አይደለም። ይህ በጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር ውስጥ የታየው የምርት ኃይሎች መጠነኛ ዕድገት የሥራን ምርታማነት በማሳደግ ሰው ለመኖር የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ ፍላጎቶች ከሞላ ገደል ለማሟላት ከሚያስፈልገው በተጨማሪ ፈሰስ የሚሆን እንዲያመርት አስቻሉታል። ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እየዳበረ ሲሄድ የሥራ ምርታማነትም እንደዚሁ እያደገ ሄደ። የምርት ኃይሎች ዕድገትና ባሕርይ፣ የሥራ ምርታማነትና የሰው ተፈጥሮን በመጠኑም ቢሆን ለመቆጣጠር መቻል የሰውን በሕይወት ለመኖር በጋራ ማምረትን አስፈላጊ አላደረገውም። ስለሆነም የምርት መገልገያዎችን በጋራ ሀብትነት መያዝ የምርት መገልገያዎችን በግል ሀብትነት በመያዝ ሊተካ ቻለ።

የፊውዳል ስልተምርትን ብንወሰድ አመጣጡ የባሪያው የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን ዕድገት አፍነው የሚይዙበት ደረጃ በመድረሱ ነበር። ገባሮች የሚያርሱትን መሬት በግል ይይዙና አንዳንድ የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤት ስለነበሩ፣ እንዲሁም የገዢ መደብ አባላት በባሮች ላይ እንደነበራቸው በገባሮች ላይ ሙሉ በሙሉ ባለቤትነት ስላልነበራቸው የምርት ኃይሎች ሊያድጉ፣ ገባሮችም እስከተወሰነ ድረስ የጉልበታቸውንና የእርሻ መሬትን ምርታማነት ሊያሻሽሉ ችለው ነበር። ቀስ በቀስ ግን በፊውዳል ገዢ መደብ አባላት የሚደረግ ብዝበዛ ገባሮችን በይበልጥ እየተጫናቸው የሥራ ፍላጎታቸው እየቀዘቀዘ በመምጣቱ ይታረሱ የነበሩ መሬቶች በብዛት ጦማቸውን እያደሩ ሄዱ። በፊውዳሉ ስልተምርት ውስጥ ዕድገት በማሳየት ላይ የነበረውን

የሸቁጧ ሸቀጥ ፍላጎት በገባሮች ይካሄድ የነበረው የአርሻ እንቅስቃ
ሴና በጊዜው የነበሩት የዐደ ጥበባት የምርት ድርጅቶች ሊያሟሉ
አልቻሉም። የፊውዳሉ ሥርዓት በማደግ ላይ የነበሩት ካፒታሊስቶች
ለማምረቻ ድርጅቶቻቸው የሰው ጉልበትና ጥሬ ዕቃዎች እንደልብ እንዲ
ያገኙ አላስቻላቸውም። ምርታማነትና የሕዝቡን የኢኮኖሚ ኃይል
የፊውዳሉ ሥርዓት ስላቀረቀዘው ካፒታሊስቶች አስፈላጊውን ስፊ
ገበያም ለማግኘት አልቻሉም። በነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች
በአንድ በኩል በገባሮችና በፊውዳል ገዢ መደብ አባላት፣ በሌላ በኩል
በካፒታሊስቶችና በፊውዳሉ ገዢ መደብ አባላት መካከል ቅራኔው እየ
ተካረረ ሄደ። ይህም ቅራኔ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች
መካከል የነበረው ቅራኔ ነፀብራቅ በመሆኑ በካፒታሊስቱ መደብ
መሪነት ትግሉ ተካሄደ የፊውዳሉን ስልተምርት በመደምሰስ አዲሱ
የካፒታሊስት ስልተምርት ተመሠረተ።

በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የሚገኘው
ግንኙነት መሠረታዊ ግንኙነት በመሆኑ ወደፊት ስለእያንዳንዱ
ስልተምርት በሰፋት ስናወሳ የምንመለሰበት ጉዳይ ነው።

እዚህ ግን በአገራችን በኢትዮጵያ በቀደሙ አብዮትና አብዮቱ
ከፈነዳ በኋላ ስልተምርትን፣ በተለይም በምርት ኃይሎችና በምርት
ግንኙነቶች መካከል የነበሩትንና ያሉትን ግንኙነቶች፣ የሚመለከቱ
አንዳንድ ሃሣቦች ይሰነዘራሉ።

የቀደሙ አብዮት ኢትዮጵያ ስልተምርት ፊውዳላዊ ሲሆን
ካለፉት መቶ ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኢም
ፔሪያሊዝም ባሕርያት ባለው የካፒታሊስት የምርት ግንኙነትም በፊው
ዳሉ ማህፀን ውስጥ ማቆጥቆጥ ጀምሮ ነበር።

በፊውዳሊዊ ስለ ተምርት ውስጥ መሠረታዊ መደቦች የፊውዳሉ መደብና በዚሁ ይበዘበዝና ይመዘበር የነበረው የአርሶ አደር መደብ ነበር· በፊውዳሉ ስለ ተምርት የኢኮኖሚው መሠረት መሬት. በመሆኑ የፊውዳሉ ገዢ መደብ አባላት ልዩ ልዩ መልኮች የነበሩት ብዝበዛ፣ ማለት የጉልበት ሥራ፣ የምርት ግብር ዓይነትና የገንዘብ ክፍያ፣ በአርሶ አደሩ ላይ ያካሄዱበት ነበር። የካፒታሊስት ምርትም በመጠኑም ቢሆን በአገር ውስጥ አቆጥቁጦ፣ አዲስ የተፈጠረው የካፒታሊስቱ መደብ አብሮት የተፈጠረውን የወዝአደር መደብ በዝበዝታል። ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በተለይ ከፊውዳሉ ገዢ መደብ ጋር በጥቅም በመተሳሰርና የብዝበዛ መረቡንም በየኢኮኖሚው ዘርፍ በመዘርጋት ብዝበዛውን አጠናክሮት ነበር።

በአብዮቱ ዋዜማ የፊውዳሉ የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን እንዳያድጉ አፍነው ይዘዋቸው ነበር። በተለይ የሸቀጥ ልውውጥና የገንዘብ በሥራ ላይ መዋል እየዳበረ ሲመጣ የብዝበዛውም መጠን ያንኑ ያህል እየጨመረ በመሄዱ አርሶ አደሮች የራሳቸውንና የሚያርሱትን መሬት ምርታማነት የማሳደግ ችሎታም፣ ፍላጎትም አጡ። ገባሮች በዝቅተኛ ደረጃ እያመረቱ ከእጅ ወደአፍ የሆነ ኑሮ ሲኖሩ የተቀሩት ደግሞ የፊውዳሉ ሥርዓት ብዝበዛ አስመርሯቸው ወደ ከተማ ተሰደዱ። ይህ የገጠር ነዋሪዎች ወደከተማ መሰደድም አንዳንድ የፊውዳል ገዢ መደብ አባላት ጭሰኞችን በማባረር ሰፋፊ እርሻዎችን በማካሄዳቸው ወይ ገም ለካፒታሊስቶች በገንዘብ በማከራየታቸው እየተባባሰ ሄደ።


በአገር ውስጥ አቆጥቁጦ የነበረው የካፒታሊስት ምርት በፊውዳሉ ስለ ተምርት ኋላ ቀር ነት ምክንያት የአገር ውስጥ ገበያ አነስተኛ በመሆኑም በላይ የጥሬ ዕቃዎችም እጥረት በመኖሩ እንዲሁም የአገር

ውስጥ ካፒታል ከውጭ ካፒታል ጋር ለመወዳደር ባለመቻሉ ከዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ተጻእኖ ስለተደፈገበትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ቀጭጮ እንዲቀይ ተደርጎ ነበር ። በሌላ አንፃር ደግሞ ጥቅማቸው ከፊውዳሉ ገዢ መደብ አባላት ጋር ተሳስሮ የነበረው ካፒታሊስቶች ወዝአደሩን በአብዛኛው መሠረታዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ያህል እንኳን የማይበቃው ደመወዝ እየከፈሉ፣ ያሠሩት ስለነበር ምርትን የማሳደግ ችሎታውና ፍላጎቱ የመነመነ ነበር ።


ስለዚህ በአብዮቱ ዋዜማ በአገሪቷ ኢኮኖሚ ውስጥ በአጠቃላይ ኋላ ቀር የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን ዕድገት ገትተውት ስለነበር የምርት መጠን በአነስተኛ ደረጃ፣ ሥራ አጥነትና ረሀብ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ይገኙ ነበር ። በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የነበረው ቅራኔ እየተካረረ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ወዝአደሮች፣ አርሶ አደሮችና ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች በአንድነት ክንዳቸውን አስተባብረው በውስጥና በውጭ የመደብ ጠላቶቻቸው ላይ ትግላቸውን አፋፋሙ። ይህም የየካቲት 66ትን ሶሻል አብዮት አስከተለ ።

አብዮቱም ከፈነዳ በኋላ ኢትዮጵያ የምታካሂደው የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ሰው በሰው መበዝበዝ ለሚያከትምበት ሶሺያሊስት ስለ ተምርት የኢኮኖሚ መሠረት ለመጣል የሚያስችል የሽግግር ወቅት ሂደት ነው። በዚህም ሂደት ውስጥ የሶሺያሊስት የምርት ግንኙነቶች እየዳበሩ ሲሄዱ አሮጌው የምርት ግንኙነት እየከሰመ ይሄዳል ። በዚህም አንፃር ለሶሺያሊስት ግንባታ እስካሁን የተጣሉ መሠረቶች ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው/ና ቸው። የገጠር መሬት በአርሶ አደሩ ቁጥጥር ሥር መሆን የፊውዳሉን የምርት ግንኙነቶች ሊበጣጥሰቸው ችሏል ። ዋና ዋና የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶች፣ እንዲሁም ገንዘብ ነክ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ይዞታ ሥር መዋላቸው

ካፒታሊስቶች፣ በተለይም ኢምፔሪያሊስቶች፣ በአገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ የነበራቸውን ተጽእኖ በማዳከም ሰፊው ሕዝብ በአገሪቷ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ያለውን ወሳኝነትና ቁጥጥር እጅግ ከፍ ሊያደርገው ችሏል። እነዚህን ለምሳሌ ያህል ጠቀስናቸው እንጂ ሌሎችም መሠረታዊ የሆኑ የአብዮቱ ድሎች አሉ። የተያያዘ ነው የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ሰፊውን ሕዝብ ከብዝበዛ ለማላቀቅ ለሶሻሊስት ግንባታ ቁሳዊና ቴክኒካዊ መሠረትን ለመጣልና የሶሻል አብዮት ለማካሄድ አማራጭ የማናገኝለት የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ማኅበራዊ የሚሠሩትን ሶሻሊዝምን ለመገንባት የሚያስችል መንገድ ነው።



- ስለ ተምርት =
  - የምርት ኃይሎች =
    - ሥራ
    - /የሰው የሥራ ኃይል/
    - የምርት መገልገያዎች =
      - የሥራ መገልገያዎች
      - የሥራ ተገበሮች
  - የምርት ግንኙነቶች =
    - የምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ግንኙነቶች /የወል ወይም የግል/
    - የምርት ክፍፍል፣ ልውውጥና ፍጆታ ግንኙነቶች
    - መደቦችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በምርት ሂደት ውስጥ የሚይዟቸው ሥፍራዎች



## ጥያቄዎች

1. ሥራ ምንድነው? ሥራ መሥራት ለምን አስፈለገ?
2. ሥራ በህብረተሰብ ዕድገት ውስጥ የተጫወታቸው ሚናዎች ምንድናቸው?
3. ሥራ ከማናቸውም ዓይነት ምዝበራ ነፃ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?
4. የሥራ ተገብሮች የሚባሉት ምንድናቸው? ባሕርያቸውስ ምንድነው?
5. በተሰማራችሁበት የሥራ መስክ የምትጠቁሙ ቸው
   ሀ. የሥራ ተገብሮች
   ለ. የሥራ መገልገያዎች ምንድናቸው?
6. ከሥራ መገልገያዎች መካከል የህብረተሰብን የዕድገት ደረጃ የሚያመለክቱ የትኞቹ ናቸው? ለምን?
7. በቆሎ ልዩ ልዩ ጥቅሞች ካሉት አዝርዕት መካከል አንዱ ነው። ከብት ለማደለቢያ ሊጠቅም ይችላል፣ ለገበሬዎች በዘርነት ያገለግላል፣ አልፎ ተርፎም በፋብሪካዎች ውስጥ ዘይትና አንዳንድ መጠጦችንም ለማምረት ይጠቀማል። በተዘረዘሩት ጠቀሜታዎች አንፃር የበቆሎ ባሕርይ ምን ይሆናል?
8. አንድ የመንግሥት እርሻ የምርት መገልገያዎች ምን ነገሮችን ያጠቃልላሉ?
9. ሰዎች በምርት ሂደት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና ምንድነው?
10. የምርት ኃይሎች የምንላቸው ምንድናቸው? ባሕርያቸውስ ምንድነው?
11. በሰዎች መካከል በምርት ሂደት ውስጥ የሚፈጠሩት ግንኙነቶች ምንድናቸው? የእያንዳንዱ ግንኙነት ባሕርያትስ ምንድናቸው?
12. የምርት ኃይሎችና የምርት ግንኙነት አለመጣጣም ምንን ያስከትላል? አለመጣጣሙስ እንዴት ሊመጣ ይችላል?
13. በአገራችን በ1966 ማለት በአብዮቱ ፍንዳታ ገደማ በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነት መካከል የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?
14. ኋላ ቀር የምርት ግንኙነቶችን በአዲስና በተራማጅ የምርት ግንኙነቶች በመተካት ረገድ አብዮታችን ምን ምን ድሎችን አስገኝቶልናል?

# የሚነበቡ መጻሕፍት


1. F. Engels "The Part Played by Labour in the Transition from ape to man, <u>Selected Works</u>, Vol. 3 pp. 66 - 77.

2. F. Engels "Introduction to Dialectics of Nature" <u>Selected Works</u>, Vol. 3 pp. 58 - 66.

3. K. Marx - <u>Capital</u>, Volume I. pp. 173 - 180 (Progress Publishers).


4. V. Kelle & Kovalson <u>Historical Materialism</u>, pp. 46 - 57.
   /በአማርኛም ይገኛል/

5. <u>The Fundamentals of Marxist Philosophy</u>, Progress Publishers, pp. 289 - 230

6. P. Nikitin, <u>Fundamentals of Political Economy</u>, pp. 7 - 12
   /በአማርኛም ይገኛል/

7. M. Cornforth, <u>Historical Materialism</u>, pp. 55- 64.

8. <u>ABE of Dialectical and Historical Materialism</u>, Progress Publishers, pp. 274 - 291.

## ምዕራፍ ፪

## ቅድመካፒታሊስት ስለ ትምርቶች



# ምዕራፍ 2

## ቅድመ ካፒታሊስት ስልተ ምርቶች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሦስቱን ቅድመ ካፒታሊስት ስልተ ምርቶችን ማለትም ጥንታዊ ጋርዮሽን፣ የባሪያ አሳዳሪና የፊውዳል ስልተ ምርቶችን በተከታታይ እንመለከታለን።

በረዥምና ውስብስብ የተገለና የዕድገት ሂደት ህብረተሰብ ቀስ በቀስ መልክ እየያዘ ተፈጥሮን የበለጠ እየተቆጣጠረ ይመጣል። በምርት ኃይሎችና በምርት ዕድገት የወል ሥራ ይዞታ እንደዚሁም እኩል ክፍፍል ላይ የተመሠረተው የጋርዮሽ ስልተ ምርት ሥፍራውን ለባሪያ አሳዳሪ ስልተ ምርት ይለቃል። ይህ በታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው በመደብ የተከፋፈለው ህብረተሰብ በበኩሉ የምርት ኃይሎችን እስከ ተወሰነ የዕድገት ደረጃ ካደረሰ በኋላ የምርት ግንኙነቶች የዕድገት እንቅፋት በመሆናቸው ተበጣጥሰው አዲስ የፊውዳል ስልተ ምርት ቦታውን ይወስዳል። ይኸም የፊውዳል ሥልተ ምርት ሂደቱን ወርሶ የምርት ግንኙነቶች የምርት ኃይሎችን ዕድገት በመግታት ማነቆ ሲሆኑ በውስጡ ለሚያቆጠቁጠው ለካፒታሊስት ስልተ ምርት ቦታውን ይለቃል።

እነዚህን ሂደቶች በመጠኑም ቢሆንም ዝርዝር አድርገን በሚከተሉት ክፍሎችና ንዑስ ክፍሎች እናጠናቸዋለን።

## 1.0 የጥንታዊ ጋርዮሽ ስል ተምርት

በምዕራፍ አንድ ሰው መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት በአካባቢው የሚገኘውን የተፈጥሮ ልዩ ልዩ ክፍሎች መለወጥ እንዳለበት ይህንንም የሚለውጠው በሥራ መሆኑንና በዚህም ተፈጥሮን የመለወጥና የመሥራት ሂደት እንዴት ከእንስሳት ደረጃ ወደሰውነት እንደተለወጠና ሰውም ሆነ ሥራ ሁለቱም የማህበራዊ ሕይወት ውጤት መሆናቸውን አይተናል። ከዚህም በስተቁር የማምረቻ ተግባር ከክፍፍልና ከፍጆታ ጋር መያያዙን፣ የማህበራዊ ዕድገት የኢኮኖሚ ሕግጋት ምን እንደሆኑ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ፣ የምርት ግንኙነቶች፣ የምርት ኃይሎችና ከነዚህም ጋር የተዛመዱት ዐበይት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ጽንሰ ሃሣቦች ምን ምን እንደሆኑም በጥሩ ተመልክተናል።

ከዚህ ቀጥሎ ቀደም ሲል ያነሳናቸው መሠረታዊ ነገሮች በህብረተሰብ የመጀመሪያ የዕድገት ደረጃ ማለትም በጥንታዊ ጋርዮሽ ስል ተምርት ውስጥ ምን ሥፍራና ሚና እንዳላቸው በማየት የስል ተምርትን ዋና ዋና ባሕርያት ለማንባት ይሞክራል።

### 1.1 የህብረተሰብ አነሳስ

ሰው የረጂም ዘመን የዕድገትና የሽግግር ወቅቶችን ካሳለፈ በኋላ ነበር አሁን ያለውን ቅርጽ ይዞ በምድር ላይ ብቅ ሊል የቻለው። ሰው በምድር ላይ ብቅ ማለቱና ቀስ በቀስም የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን መሥራት መጀመሩ በምድር ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከተሏል። በእንስሳትና በሰው መሐከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ሰው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን በመሥራትና ተፈጥሮን ለውጦ ለራሱ ጥቅም ለማዋል መቻሉ ነው።

ባንዳንድ እንቅስቃሴዎቻቸው ከሰው ጋር የሚመሳሰሉት ጦጣዎችና ዝንጀሮዎች እንኳ ከዛፍ ላይ ፍሬ ለማውረድ በእንጨትና በድንጋይ ይጠቀሙ እንደሆን እንጂ የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን ሊሠሩ አይችሉም፡ ለምሳሌ መሬት ለመቆፈሪያ የሚሆን ዶማ፣ ዛፍ ለመቁረጫ የሚሆን መጥረቢያ ለመሥራት አይችሉም ። ሰው ግን ይህን ማድረግ ይችላል ። ሰዎች የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን ለመሥራት ከመቻላቸው በፊት ግን እጅግ በጣም ረጅም ዘመናት የፈጀ ጥረትና ድካም አድርገዋል ።

የሰው ታሪክ ሲመረመር ሰው በመጀመሪያ ድንጋይንና ቅሳን በማሾል ከአውሬ ራሱን ለመጠበቅና አውሬም ለማደን ይጠቀም እንደነበር ይታወቃል ። በዚህም ጊዜ አንድ ሰው ተፈጥሮን ብቻውን በመሥራት ሊቋቋም የማይችለው ስለነበር እንደመንጋ እየተሰባሰበ መኖር ጀመረ ። ሥራን አንድ ላይ ይሠራል ። የሥራውንም ውጤት በጋራ ይጠቀምበታል ። ስለዚህም ሥራ ሰውን እያቀራረበና እያገናኘውም ሄደ ። ሰው በጋራ ሥራን ማከናወኑ በዚህም ምክንያት ይበልጥ መቀራረቡ ቋንቋን፣ ንግግርን እንዲያዳብር ረዳው። ይህ ተቀራርቦና ተዳድቶ መኖር ሰው ህብረተሰብን መሥርቶ እንዲኖር አደረገው።

## 1.2 የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች ዕድገት

ሰው በምድር ላይ ብቅ ባለበት ጊዜ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የነበረው አቅም እጅግ ደካማ ነበር ። ሰው አካባቢውን ለመቆጣጠር እጅግ በጣም ረጅም ጊዜ ወስዶበታል ። ሰው በመጀመሪያ ላይ ይጠቀምበት የነበረው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያው እየተሻሻለ በሄደ መጠን አካባቢውንና ተፈጥሮንም ለመቆጣጠር የነበረው አቅም እየተሻሻለ ሄደ ። ከቅሳና ከሹል ድንጋይ ወደ መቆፈሪያና መቁረጫ መሥራት ሲሸጋገር ኑሮውም አብሮ ተሻሻለ ። በመጀመሪያ ላይ ተፈጥሮ የለገሰውን ምግብ በመልቀምና በአደን ላይ ብቻ ተሰማርቶ የነበረው የኋላ ኋላ መሬት መቆፈርና እንጨት መቁረጥ ሲጀምር በራሱ ጥረት ባመረተው መጠቀም ጀመረ ።

ሰው በየጊዜው የሚሠራቸው የሥራ መከናወኛ መሣሪያዎች እየተሻሻሉ ሲሄዱ እሳት እንዴት እንደሚቀጣጠል ለማወቅ ቻለ ። ሰው በእሳት መጠቀም መጀመሩ ተፈጥሮን ለመቆጣጠር ለሚያደርገው ትግል ድል ነበር ። በእሳት ምግብን ማብሰል ሲጀምር የሚበላው ነገር በመጠንም በዓይነትም እየጨመረ ሄደ ። እሳት ከተገኘ በኋላ ሰው የሚሠራቸው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች በጣም እየተሻሻሉ ሄዱ ። እሳት ከብርድ ሊከላከል በመቻሉ ሰዎች በምድር ላይ በሞቃት ሥፍራዎች ላይ ብቻ ይኖሩ የነበሩት በሁሉም ሥፍራ ተሰራጭተው ለመኖር ቻሉ ። እሳት ከዱር አራዊት ለመከላከል ከፍተኛ ጥቅም አስገኘ ።

ሰው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን ከድንጋይና ዱላ ወደ ብረት እንዲለውጥ የረዳው የእሳት መገኘት ነበር ። ሰው በተሻለ መሣሪያ ለምሳሌ በቀስትና በጦር እንሰሳትን በማደን ለሀይወቱ አስፈላጊ የሆነውን ምግብ የማግኘት ችሎታውን ከፍ እያደረገው መጣ ። ይህም በመሆኑ እንሰሳትን በቤት ውስጥ ወደ ማላመድና ወደ ማርባት አመራ ። እንደ ውሻ፣ ፍየል፣ በሬ፣ ላም፣ አሳማ፣ ፈረስና ሌሎችንም ለማዳ አደረጋቸው ።

ከዛፍ ላይ ወደመሬት የወደቁ ፍሬዎች እንደገና ሲበቅሉ የተመለከተው ሰው ለቁፋር የተሻለ መሣሪያ መሥራት ሲጀመር መሬትን መቆፈርና ለምግብ የሚሆኑ ፍራፍሬዎችን መትከል ጀመረ ። እንሰሳትን ለማዳ ማድረግና መሬት መቆፈር ሲጀምር ሰው በጥረቱ የሚያገኘው ምርት እየጨመረ ሄደ ። ኑሮውም ይበልጥ እየተደላደለ መጣ ። ቀድሞ ሀይወቱን ለማቆየት ከሥፍራ ሥፍራ እየተዘዋወረ ፍራፍሬ በመልቀምና በማደን ይኖር የነበረው አሁን ባንድ ሥፍራ ላይ በመስፈር የሚፈልገውን ነገር በአካባቢው እያመረተ መኖር ጀመረ ። ለዚህም መሠረታዊና ወሳኙ ነገር የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች በየጊዜው እየተሻሻሉና እየዳበሩ መምጣታቸው ነው ።

## 1.3 የጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ የምርት ግንኙነት

የጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ የምርት ግንኙነት መሠረት በጊዜው የነበረው የማምረቻ መሣሪያዎች የጋራ መሆን ነበር ። ይህ የወል ይዞታ ምርትንም የጋራ እንዲሆን አድርጓል ። በጊዜው የነበረው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያ እጅግ ኋላ ቀር በመሆኑ ሁሉንም አንድ ላይ ሰብስቦ የጋራ ኃይል መፍጠር ነበረበት ። ስለዚህም በነበረው ሁኔታ ሰዎች የጋራ ይዞታና የጋራ ሥራ ነበራቸው ። የጥንታዊ ጋርዮሽ ሰው ከዱር አራዊት ራሱን የሚጠብቅበት መሣሪያና የራሱ ወይም የቤተሰቡ መጠቀሚያ የሆኑ አንዳንድ ቁሳቁሶች ብቻ የግሉ ነበሩ ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ የነበረው የሥራ ማከናወኛ ኋላ ቀር ስለሆነ የሥራው ሂደት ወይም የአሠራሩ ዘዴ መረዳዳት ላይ የተመሠረተ ነበር ። ስለዚህም እጅግ በጣም ብዙ የሆነ የጉልበት ሀይልን በጣም ትንሽ ለሆነ ሥራ ውጤት ይውል ነበር ። ለምሳሌ ቁጥራቸው በጣም ብዙ የሆኑ ሰዎች አንድ አውሬ ለማደን ያለ የሌለ መሣሪያቸውን ይዘው ይዘምቱ ነበር ። ኩርማን እምታህል መሬትንም ለመቆፈር እንዲሁ የአካባቢ ሰዎች በሙሉ ባንድነት ይሠሩ ነበር ። በዚህ ሁኔታ የሚገኘው ምርት ለሁሉም እኩል መከፋፈሉ የተፈጥሮ ግዴታ ነበር:: ይህን ሁኔታ ባንዳንድ የአገራችን ክፍሎች በተለይም በአናሳ ብሔረሰቦች ዘንድ እንደሚገኝ ፀባረቅ ለመገመት ይቻላል ።

የጥንታዊ የጋርዮሽ ሕብረተሰብ አንዱ ባህርዩ የህብረተሰቡ የማምረት ችሎታ የህብረተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎቶች በመጠኑ ለማሟላት ያህል ብቻ መሆኑና ለብዙና ረጅም ዘመናት ፈሰስ ማስገኘት አለመቻሉ ነበር፤ የማምረቻ መሣሪያዎች እጅግ ኋላ ቀር በመሆናቸው ለህይወት አስፈላጊ የሆነው ጥቂት ምርት ብቻ ነበር የሚመረተው ። በዚህም የተነሳ አንዱ ሰው ሌላውን ሊበዘብዝ የሚያስችለው ሁኔታ አልነበረም ። ጥሩ

መደብ የሚባል ነገር በጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ አልነበረም :: በሁለት በተለያዩ ሥፍራዎች መሀከል የምርት ብዛትና የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን በማመለከት መጠነኛ ልዩነት ይኖር እንደሆነ እንጂ በያንዳንዱ ሥፍራ ባሉ ሰዎች መሀከል ግን ልዩነት አልነበረም ።

የጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግጋት የሚከተሉት ናቸው :: አንደኛ በጣም ኋላቀር በሆነ የሥራ ማከናወኛ መሣሪያ ለሕይወት ማቆያ ብቻ አጅግ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ማምረት :: ሁለተኛ የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችን በጋራ መያዝ :: ሦስተኛ በጋራ መሥራትና አራተኛ የተገኘውን ምርት እኩል መከፋፈል ነበር :: የስልተ ምርቱም አይነት ጥንታዊ የጋርዮሽ ስልተ ምርት በመባል ይታወቃል ::

## 1.4 ተፈጥሮአዊ የሥራ ክፍፍል

ኋላቀር የነበረው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያ በመጠኑም ቢሆን እየተሻሻለ ሲሄድ በሰዎች መሀል የሥራ ክፍፍል እየታየ መጣ :: በመጀመሪያ ላይ የነበረው የሥራ ክፍፍል ግን ይህ ዛሬ የምናየው የረቀቀ አይነት ሳይሆን ተፈጥሮአዊ የሥራ ክፍፍል በመባል ይታወቅ ነበር :: ለምሳሌ የሥራ ክፍፍሉ በጾታና በእድሜ፣ በገልማሶች፣ በልጆችና በሽማግሌዎች መሀከል የሚደረግ ዓይነት የሥራ ክፍፍል ነበር ::

ሰው ከእንስሳት ዓለም ቀስ በቀስ እራሱን እየለየና እያገለለ ሲሄድ በቡድን ከተፈጥሮ አደጋ ለመከላከልና ለህይወቱም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት መሰባሰብ ጀመረ :: ይህም በልዩ ልዩ አካባቢዎች በቡድን መሰባሰብ ከሥራ ማከናወኛ መሣሪያ ማደግ ጋር በዝርያና በሥጋ ዝምድና እየተጠናከረ ሄደ ::

በሥጋ ዝምድና ላይ በተመሠረተ /በዘር/ ሕብረተሰብ የመጀመሪያው ደረጃ ላይ ሴቶች በኅብረተሰቡ የማምረት ሂደት ውስጥ የበላይነት ነበራቸው ። ወንዶች በኅብረተሰቡ ውስጥ በነበራቸው የሥራ ድርሻ ምክንያት አደን በጣም ኋላቀር በሆነ መሣሪያ በአደን ሥራ ላይ በመሠማራታቸው አድነው የሚያመጡት ምርት ለኅብረተሰቡ በቂ አልነበረም ። አንዳንዴም አደኑ አይሳካላቸውም ነበርና ዝቅተኛ ምርት የሚያመርቱት ወንዶች ነበሩ ። በመኖሪያ አካባቢ ያለ ትንሽ መሬት ጫር ጫር አድርጥራጥሬ አትክልት መዝራት፣ መጠነኛ ቢሆንም እንስሳትን በቤት ውስጥ ማላመድ የሴቶች የሥራ ድርሻ ነበር ። በዚህ አንፃር የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስፈልገውን ምርት በአብዛኛው የሚያስገኙት ሴቶች ነበሩ ። ኅብረተሰብ በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ በነበረበት ጊዜ በህብረተሰቡ የምርት ሂደት ውስጥ ሴቶች ከፍተኛውን ሥፍራ ይዘው ቆይተዋል ። ይህም ዘመን የእማዊ ዘመን በመባል ይታወቃል ። ይህ የጥንታዊ ጋርዮሽ ባህርይ ባንዳንዱ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ዘንድ ሊኖር እንደሚችል ይነገራል ።

የማምረቻ መሣሪያዎች እየዳበሩና እያደጉ በሄዱ መጠን ግን ማህበራዊው የሥራ ክፍፍልም ሲስፋፋ በዘላንነት ኢኮኖሚ ላይ የተመሠረ ከብት ማርባትና እርሻ እያደገ በመምጣቱ ወንዶች በዚህ የሥራ መስክ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አገኙ ። በዚህ የዕድገት ደረጃ ላይ ወንዱ በኅብረተሰቡ የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና መጫወት ጀመረ ። ይህ ጊዜ የአባዊ ቤተሰብ ጊዜ በመባል የሚታወቅ ሆኖ በጥንታዊ ጋርዮ ሕብረተሰብ የመጨረሻ እድገት ደረጃ ላይ የታየ ነበር ።

## 1.5 የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍልና የምርት ልውውጥ አነሳስና እድገት

ሰው ከብት ማርባትንና እርሻን እየተላመደ ሲሄድ በኅብረተሰቡ ውስጥ የማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል እመርታ አደረገ ። በመጀመሪያ ልዩ ልዩ ቡድኖች ከዛም በኋላ በየቡድኑ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በተለያዩ

የምርት ተግባሮች ላይ ማተኮር ጀመረ ። ለምሳሌ የዘላን ኢኮኖሚና የርሻው ኢኮኖሚ የመጀመሪያውና ትልቁ ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍል ነበር ።

ከብት አርቢ ገሳዎች ከብቶችን መንከባከብና ማራባትን ብቻ ሲያያዙ በእርሻ ላይ የተሰማሩት ደግሞ እህል ማምረትን ብቻ ተያያዙት ። ከብት አርቢዎች ብዙ ስጋ፣ ለልብስ የሚሆን ፀጉርና ቆዳ እንደዚሁም ወተት ማምረት ጀመሩ ። ይህም የሥራን ምርታማነት ከፍ አደረገው ።

በእርሻ ላይ የተሰማሩ ጉሳዎች እህል በብዛት ማምረት ጀመሩ ። ይህም በበኩሉ የሥራን ምርታማነት ከፍ አደረገው ። በከብት ርቢ ላይ የተሰማሩት በእርሻ ላይ ከተሰማሩት ጉሳዎች እህል ይፈልጋሉ ። በእርሻ ላይ የተሰማሩትም ጉሳዎች ሥጋ፣ ወተት፣ ለልብስ የሚሆን ፀጉርና ቆዳ ይፈልጋሉ ። ስለዚህም አንደኛው ሊያመርት የማይችለውን ከሌላው በማግኘት በትርፍ የሚያመርተውን ለሌላው በመስጠት የምርት ልውውጥ ተጀመረ ። በዚህ ዓይነት መንገድ የተጀመረው የሥራ ክፍፍልና የምርት ልውውጥ እያደገ በመሄዱ ምርት በብዛትና በዓይነት ጨመረ ።

ሸክላ ሥራ፣ ሽማኔነት፣ ብረት ማቅለጥ የመሳሰሉት ሥራዎች ቀስ በቀስና ደረጃ በደረጃ ብቅ እያሉ መጡ ። በሸክላ ሥራ ልዩ ልዩ የማብሰያ እቃዎች ድስት፣ ጀበና፣ ማሰሮ ወዘተ... መሥራት ተጀመረ፣ በሽማኔ ሥራ ልዩ ልዩ ልብስ መሠራት ተጀመረ ። በተለይ ደግሞ ብረት ማቅለጥ ሲጀመር እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑ የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎች እንደ ዶማ፣ አካፋ፣ ጦር፣ ማረሻ፣ መጥረቢያ ሉሠራት ተጀመረ ። የሥራ ክፍፍሉና የምርት ልውውጡም ቀደም ሲል በሁለት ዓይነት የኢኮኖሚ ዘርፎች ማለት በከብት እርባታና በእርሻ ብቻ ተወስኖ የነበረው አሁን ተጨማሪ የኢኮኖሞ ዘርፍ በእደ ጥበብ አማካይነት ተፈጠረ ። በቀጥታ በእርሻ ላይ የተሰማራው ሰው የእርሻ መሣሪያውን መቆፈሪያ፣ ዶማ፣ አካፋ ጉጀራና ሌላም ነገር ከብረት አንጥረኛ ማግኘት ነበረበት ። በዚህ ዓይነት የሥራ ክፍፍልና የምርት ልውውጡ የበለጠ እያደገ ሄደ ።

## 1.6 የግል ሀብትና የመደቦች አነሳስ

በጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ የታየው የሥራ ክፍፍልና የምርት ለውጥ እድገት የማምረቻ መሣሪያው ከወል ወደ ግል ይዞታ እንዲለወጥ አደረገ ። ይህ እንዴት እንደሆነ ባጭሩ እንመልከት ።

ሰው የምርት ማከናወኛ መሣሪያዎችን እያሻሻለ በሄደ መጠን በኅብረተሰቡ ውስጥ አብሮ ያደገው የሥራ ክፍፍልና የምርት ለውጥ እያንዳንዱ ሰው በግል፣ በቤተሰብ ወይም በቡድን የተወሰነ ሥራን ብቻ እንዲሠራ አስገደደው ። ይህም የሥራን ምርታማነት ከፍ አደረገ ። ይህ ሁኔታ ደግሞ እያንዳንዱ ሰው የማምረቻ መሣሪያውን በግሉ እንዲይዝ የምርት ውጤቱንም በግሉ እንደመሰለው እንዲያከፋፍል አደረገው ። በጥንታዊ የጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ የነበረው የጋራ ሥራና የጋራ ኢኮኖሚ ቀስ በቀስ ወደማያስፈልግበት ደረጃ ላይ ደረሰ ። የጋራ ሥራ የጋራ ይዞታንና እኩል መከፋፈልን ሲጠይቅ የግል ሥራ ደግሞ የግል ይዞታንና በግል መጠቀምን ጠየቀ ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ሕብረተሰብ ውስጥ በመጀመሪያ የታየው የምርት ለውጥ በአንጋፋነቱና በህብረተሰቡ ውስጥ በያዘው ቦታ መሪ በሆነ ግለሰብ አማካይነት የሚካሄድ ነበር ። የሚያስቀምጠውም ምርት የጠቅላላው ሕብረተሰብ ይዞታ ነበር ።

በጥንታዊ የጋርዮሽ ዘመን መጀመሪያ ላይ ዋናው የመገበያያ መሣሪያ የከብት መንጋ ነበር ። ቀደም ሲል በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ይዘው የነበሩና ተሰሚነትም የነበራቸው ቀስ በቀስ ይህን ዋነኛ የመገበያያ መሣሪያ የነበረውን የከብት መንጋ በራሳቸው የግል ባለቤትነት ቁጥጥር ሥር እያዋሉት ሄዱ ። ከዚህ በኋላ መጀመሪያ ጠቅላላው የከብት መንጋ ቀጥሎም ቀስ በቀስና በጊዜ ውስጥ ጠቅላላው ምርት መሣሪያ በግል ባለቤትነት ተያዘ ። በወል ባለቤትነት ሥር ሆኖ ለብዙ ጊዜ የቆየው መሬት ብቻ ነበር ።

የምርት ሀይሎች እድገት መፋጠንና የግል ባለቤትነት ሥር መስደዱ ቀደም ሲል በቡድን ተሰባስቦ የነበረውን የሰዎች ክምችት መፈራረስ አስከተለ :: አነስተኛ ቡድኖች በሰፋፊ ቤተሰቦች ተተኩ :: ቀጥሎም እነዚሁ ሰፋፊ ቤተሰቦች በአነስተኛ ቤተሰቦች በመከፋፈል ልዩ ልዩ የምርት መሣሪያዎችን፣ የቤት ቁሳቁሶችንና የከብት መንጋዎችንም በራሳቸው ግላዊ ቁጥጥር ሥር ማዋል ጀመሩ :: እነዚሁ በአነስተኛ ቤተሰቦች የተሰባሰቡት ሰዎች የመንደር ማኅበረሰብ በዘርና በስጋ የተሳሰረ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎችንም የሚጨምር ነበር :: የጥንታዊ የጋርዮሽ ሕብረተሰብ በደረሰበት በዚሁ የእድገት ደረጃ ላይ ቤት፣ የቤት ቁሳቁሶች፣ ከብቶችና የመሳሰሉት በተለያዩ ግላዊ ቤተሰቦች በግል ባለቤትነት የተያዙ ነበሩ :: ይሁንና የግጦሽ ሜዳዎች፣ ውሀ፣ እንጨት፣ የርሻ መሬትና ሌሎች ተፈጥሮአዊ ሀብቶች እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ በወል የቁጥጥር ይዞታ ሥር ነበሩ ::

በጥንታዊ ጋርዮሽ ሥልተ ምርት የግል ሀብት መፈጠር የአመራረትንና የልውውጥን የአስተዳደርንና የአመራርን ለውጥ አስከተለ :: የግል ሀብት መፈጠርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሀብት ልዩነቶች ማቆጥቆጥ የኅብረተሰብ አባላት ፍላጐቶችን በዓይነትና በመጠን ከፍ አደረገው :: ይህ በኅብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ሰዎች ሀብት ባለቤቶች እንዲሆን አደረገ ::

የምርት ሀይሎች እያደጉ ሲሄዱ ቀደም በተወሰነ ምርት ላይ ብቻ ተወስኖ የነበረው ሥራ የተለያዩ ምርቶችን በመጠንም በዓይነትም ከፍ ማድረግ ጀመረ :: ይህ መሆኑ ደግሞ የትርፍ ሥራንና የፈሰሰን ባለቤትነት ፈጠረ :: በጥንታዊ የጋርዮሽ ህብረተሰብ ማክተሚያ ገደማ የተከሰተው የፍላጎት በመጠንና በዓይነት መጨመር ያስከተለው የሀብት ክምችት በተለያዩ ቤተሰቦችና መንደሮች መሀከል አንዱ ከሌላው የተሻለ የሀብት ክምችት በመሰብሰብ የቤተሰቡን ወይም የመንደሩን ፍላጎት ለማሟላት ሌላው ቤተሰብ ወይም መንደር ያመረተውን በኃይል እየነጠቀ መኖር ጀመረ :: ይህ በኃይል የመጠቀምና የመቀማት ገጽታ እየሰፋ በሄደ መጠን ደግሞ አንዱ ቤተሰብ

ወይም መንደር ሊሳውን ቤተሰብ ወይም መንደር በመውጋት የተመረተውን ምርት በመዝረፍና በምርኮኛነት የሚይዛቸውን ሰዎች ባሮች በማድረግ በምርት ተግባር ላይ በማሠማራት የህብረተሰቡ የምርት ፈሰስ መጠን እየ ጨመረ ሄደ ። ባለብዙ ሀብት የሆኑና እጅግ ሀይለኛ የነበሩ ቤተሰቦች የበርካታ ባሪያዎች ባለቤቶች ሆኑ ። በሀብት ልዩነት የተነሳ የሥራ ምርታማነት እየጐላና የግል ይዞታም ሥር እየሰደደ ሲሄዱ ራሳቸው በየእሥር ቤቱ ውስጥ ይማቀቁ የነበሩት ብቻ ሳይሆኑ እጅግ በጣም ደሀ የነበሩና እጅግ ብዙ እዳም የነበረባቸው የእስረኞች ዘመዶችም ጭምር ባሮች ተደረጉ። የግል ይዞታ የግል ሀብት እየተጠናከረ ሲመጣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተው የመጀመሪያው ኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈል ጀመረ ። ባንድ በኩል የባሪያ አሳዳሪዎች በሌላ በኩል ደግሞ የባሮች መደብ ብቅ አለ ። የሰው በሰው መበዝበዝ ሥርዓት ከዚህ ይጀምራል ። በዚህ ዓይነት ረጅምና ውስብስብ ሂደት በጥንታዊው ጋርዮሽ ስልተ ምርት ውስጥ የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ተፀንሶ ቀስ በቀስ እያደገ መጣ፣ በመጨረሻ ላይም ለምርት ሀይሎች እድገት እንቅፋት መሆን የጀመረው የጋርዮሽ የምርት ግንኙነት መለወጥ ግድ ስለሆነበት በማምረቻ መሣሪያዎች የግል ይዞታና የግል ሀብት ላይ የተመሰረተው የመጀመሪያው ስልተ ምርት ማለትም የባሪያ አሳዳሪው ሥልተ ምርት ተከሰተ ዋነኛው ወይም አቢይ ስልተ ምርት ሆነ ።

## አጭር ማጠቃለያዎች

1/ ሰዎች በሥራ አማካይነት ከእንሰሳት ዓለም ተላቀው ሰብእናን ተጎናፀፉ፣ ኅብረተሰብም ሕልውና አገኘ ።

2/ የጥንታዊው የጋርዮሽ ሕብረተሰብ የምርት ኃይሎች እጅግ ኋላ ቀር የነበሩ ከመሆናቸውም ሌላ የማምረቻ መሣሪያዎቹም እጅግ ጥንታዊ ነበሩ ። ይህ ሁኔታ የሥራንና የማምረቻ መሣሪያዎችን የወልነት

ፈጠረ ። ክፍፍልም በእኩልነት መሠረት ላይ የሚካሄድ ሆነ ።
በጥንታዊ የጋርዮሽ ዘመን የሀብት አለመመጣጠን ወይም በምርት ማካሄጃ መሣሪያዎች ላይ የነበረ የግል ባለቤትነት አልነበረም ።
ይሁንና የምርት ማካሄጃ መሣሪያዎች የወል ባለቤትነት ከልል እጅግ በጣም የተወሰነ ነበር፤ ይህ ባለቤትነት በመጠኑም ቢሆን ከሌላው በተለየው አነስተኛ ማኅበረሰብ ውስጥ ብቻ የተወሰነ ነበር።

3/ የጥንታዊ ጋርዮሽ ሕብረተሰብ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ህግ ለሰዉ ለ[illegible] ሕይወት የሚያስፈልጉትን ነገሮች በጥንታዊ የምርት መሣሪያዎች እጋዥነት በማምረት፤ የምርት መገልገያ መሣሪያዎችን በወል ባለቤትነት በመያዝ፤ በጋራ ሥራና በእኩል ክፍፍል ላይ የተመሠረተ ነበር ።

4/ ምንም እንኳን በጋራ የሚካሄድ ቢሆንም ለብዙ ጊዜ የሰዎች ሥራ ተመሳሳይነት የነበረው ነበር ። የምርት ማካሄጃ መሣሪያዎች ቀስ በቀስ መሻሻል በጾታና በእድሜ ላይ የተመሠረተን ተፈጥሮአዊ የሥራ ክፍፍል አስከተለ ። የምርት መሣሪያዎች እያደጉና እየተሻሻሉ ሲሄዱ ለሕይወት የሚበጁ ነገሮችን የማምረት ተግባርም ጎበረ ።
የከብት እርባታና የእርሻ ተግባሮችም ተስፋፉ፤ ይህም የሥራን ማኅበራዊ ክፍፍልና ልውውጥ፤ የግል ባለቤትን ሀልወናና የሀብት አለመመጣጠንን አስከተለ ። የኅብረተሰብ በመደብ መከፋፈልና የሰው በሰው መበዝበዝ እውን ሆነ ። ይህንን ያስከተለው ታዳጊው የምርት ኃይል ከማይንቀሳቀሰው የምርት ግንኙነት ጋር በመጋጨቱ ነው ።
በእነዚሁ መካከል ከፍተኛ ቅራኔ ተፈጠረ፤ በውጤቱም የጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት ፍጻሜ ሆኖ የባሪያ አሳዳሪው ስርዓት ተተካ ።

## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1/ በሰዉና በእንስሳት መሀከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ምንድነው?

2/ ሕብረተሰብ ማለት ምንድነው?

3/ ሰው ተፈጥሮን እንዴትና ለምን ይለውጣል?

4/ የጥንታዊ ጋር ዮሽ ሕብረተሰብ የምርት ግንኙነቶች ምን ምን ናቸው?

5/ ዚህ ስለ ተ ምርት የምርት ሀይሎች ምን ምን ናቸው?

6/ የጥንታዊ ጋር ዮሽን ሕብረተሰብ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ሕግ አብራራ?

7/ የሥራ ክፍፍል እንዴት መጣ? የሚጫወተው ሚናስ ምንድነው?

8/ የጥንታዊ ጋር ዮሽ ስለ ተ ምርት እንዴትና ለምን ፈረሰ?

## የሚነበቡ መፅሀፍት

1/ ቀደም ብለው የተጠቀሱት

2/ የቤተሰብ የግል ሀብትና የመንግሥት አመጣጥ — ፍ. ኤንግልስ

## 2.0 የባሪያ አሳዳሪ ስልተ ምርት

ከዚህ በላይ ባለው ምዕራፍ ውስጥ የባሪያው አሳዳሪ ስልተ ምርት በጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተ ምርት ማህፀን ውስጥ ማደጉንና ይሄኛው አርጅቶ አፍጅቶ ሲፈራርስ ያኛው በቦታው ላይ መተካቱን ተመለከትናል ::

የዚህ ስልተ ምርት ጉልህ ገጽታዎች፣

- ህብረተሰብ በመደብ የተከፋፈለበት በታሪክ የመጀመሪያው ስልተ ምርት፣
- አብዛኛው አምራች ህዝብ ነፃነቱንና የሰውነት ክብሩን ተገፍፎ እንደ ቁሳቁስ በመቁጠር ላፈጠጠና ላገጠጠ ግርፋፍ ጭቁናና ብዝበዛ የተጋለጠበት፣
- መንግስት የሚባለው የመጨቆኛ ተቋም ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ ያለበት፣
- የሰው አውቀት ሳይንሳዊ ቅርጽ የያዘበት ስነ ጥበብ ቅርጻ ቅርጽ ያበቡበት፣ ታላላቅ ሀውልቶችና ህንፃዎች የተሰሩበት ከተሞች· ብቅ ብቅ ያሉበት.... ስልተምርት ነበር ::

## 2.1 የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት አመጣጥና የምርት ግንኙነት

ሰው ፍላጎቶቹን ለማሟላት በአካባቢው የሚገኙትን ልዩ ልዩ የቁስ አካል ክፍሎች/አዳዲስ ሲለጠጥ ዘዴዎችንና መሣሪያዎችን ያገኛል፣ ይሠራል፣ ዕውቀቱ የሥራ ችሎታው ይዳብራል :: ይህ ሂደት የሥራ ክፍፍልን ያስከትላል:: ይህ ደግሞ መልሶ የምርት ኃይሎችን ያሳድጋል ያዳብራል:: በዚህም የተነሣ ምርት ያድጋል፣ ለፍጆታ ከሚያስፈልገው በላይ ይመረታል:: የምርት ልውውጥ ይስፋፋና ቀስ በቀስ የግል ንብረት ብቅ ይላል:: የሥራ ማከናወኛዎችና የሥራ ተግብሮች የግል ሀብት ወይም ንብረት ይሆናሉ፣ በጥቂቶች እጅ ውስጥ ይገባሉ:: በአጠቃላይ በጋራ ይዞታና በጋራ

ባለቤትነት በእኩልነት ላይ የተመሠረተው የጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተ ምርት ያከተመው በዚህ ሂደት ውስጥ አልፎ ሲሆን የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርትም በዚሁ ሂደት ውስጥ ሕልውናውን አገኘ::

በዚህ ሂደት ውስጥ ለመሆኑ ባርነት እንዴት መጣ? የባርነት አመጣጥ በሁለት መንገዶች እንደሆነ ይገመታል:: አንደኛ በልዩ ልዩ ማኅበረሰቦችና ጎሣዎች መካከል ግጭት ጦርነት ሲደረግ አንዱ ሲሸነፍ አንዱ ሲያሸንፍ ተሸናፊዎች ይማረካሉ፣ እሥረኞች ይሆናሉ፣ ምርኮኞችና የተሸናፊዎቹ ወገኖች በጅምላ ባሮች ይሆናሉ:: ሁለተኛው በአንድ ማኅበረሰብ ወይም ጎሣ ውስጥ ባለዕዳዎች ነፃነታቸውን አጥተው ባሪያ ይሆናሉ:: የትኛው ይቀድም የትኛው ይከተል በውል ባይታወቅም ባርነት የመጣው የምርት ኃይሎች የተወሰነ የእድገት ደረጃ ላይ ከደረሱና የሥራ ምርታማነት ከፍ ካለ በኋላ መሆኑ የታወቀ ነው፣ አንድ ሰው የሚያመርተው ከፍጆታው በታች ከሆነ ባሪያ ማሳደር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናልና ምርኮኛን ሆነ ባለእዳን ባሪያ ማድረግ ትርጉም አይኖረውም:: በቤተዘመዶች በጎሣዎች ወዘተ... መካከል ግጭት ጦርነት ስለነበር በመጀመሪያ ላይ ምርኮኞቹን በሙሉ ይገሉና አንዳንዴ ሥፍራም ይበሏቸው እንደነበረ በታሪክ የተመዘገበ ነው፣ ስለዚህ የሥራ ምርታማነት እንደታየ ወይም ሥራ ምርታማ መሆን እንደጀመረ በመጀመሪያ ላይ ይጨፈጨፉ የነበሩት የጦር ምርኮኞች ወደባርነት ተለወጡ ለማለት ይቻላል:: በእዳና በሌሎች ምክንያቶች ወደባርነት የሚለወጡት ግን የቤተዘመዱ ወይም የጎሣው አባሎች ስለሆኑና እንደዚሁ በቀላሉ ዘመድንና ወገንን ባሪያ ለማድረግ ስለማይቻል እንዚህን ባሪያ አድርጎ ለመበዝበዝ የሥራ ምርታማነት በጣም ከፍ ማለት ነበረበት:: በዚህ አስተሳሰብ በመጀመሪያ ምርኮኞች ከዚያ ባለእዳዎች ባሮች ሆኑ ለማለት ይቻላል:: በአገራችንም በአንዳንዱ ሥፍራዎች ባለፈት ክፍለ ዘመናት ምርኮኞች ወደባርነት ይለወጡ እንደነበረ ሲታወቅ በእዳ ግን እንደዚህ መደረጉ በውል አይታወቅም::

የባሪያ አሳዳሪው ሥልተ ምርት የምርት ግንኙነቶች የተመሠረቱት በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ ነው፣ እነዚህም ባሮች፣ ከብቶች እና ቁሳቁሶች ናቸው፣ እነዚህ ቀደም ብሎ በተጠቀሱት ምክንያቶችና ሂደቶች በባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት በጥቂት ግለሰቦች እጅ ውስጥ ገብተዋል::

የባሪያ አሳዳሪው የምርት ግንኙነት ሕጋጋት ባሮችን የመገ... በዘበዝ የገዥዎን መደብ አባላት ገን የሚያገደላቁ ቆናቸው:: በባሮች ላይ እስቃቂ ኢሰብአዊ የሆነ ጭቆናና ብዘበዛ ይፈጸምባቸዋል:: ይደበደባሉ፣ ይገረፋሉ፣ ይሸጣሉ፣ ይገደላሉ፣ የሚታዩትና የሚቀጡት ልክ እንደ እንስሳና እንደገዐዝ ዕቃ ነው:: ለመሥራት የሚያስችል እህል ውሃ ይሰጣቸውና የድካማቸው ፍሬ በሙሉ ለጌታ ይገባል::

በዚህ አገፀር ባሪያ አሳዳሪዎች ቁጥ ብሎ ከመብላት በስተቀር ባብዛኛው ምንም አይሠሩም:: በጥንታዊት ግሪክና ሮም የነበሩት ጌቶች በጊዜው ዓይነተኛ የነበረውን የጉልበት ሥራ በጣም ይፀየፉታል፣ የጉልበት ሥራ መሥራትን እንደተለቀ ውርደት ይቆጥሩታል:: ሆኖም ባሮች በፈጠሩት ሀብት በመጠቀም ከገዢው መደብ አባላት ጥቂቶች በአእምሮታዊ ተግባር ለምሳሌ በሳይንስ በሥነ ጥበብ በኪነት በቅርፃ ቅርጽ እና በመሳሰሉት መስኮች ተሰማርተው ለህብረተሰብ እድገት የሚረዳ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

## 2.2 የመንግሥት አመጣጥ

በጥቂቶች የማምረቻ መሣሪያዎችና የሥራ ተገብሮች ባለቤትነት ላይ የተመሠረተውን የምርት ግንኙነት ለመጠበቅ ለማረጋገጥና ለማዳበር መንግሥት የተባለው የአንዱን መደብ በሌላው ጠቅም - ጭዛ መሣሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባሪያ ሥርዓት ጋር ሕልውና አገኘ:: የከፋውንና የከረፋውን የብዙኃኑን አምራቶች ጭቆናና ብዝበዛ መልክና ሥርዓት ያስያዘውና የቋሚነት መልክ ያሰጠው ይህ በባሪያ አሳዳሪው መደብ የተመሠረተውና

የተደጎመው ተቋም ነው። የባሪያ አሳዳሪው መደብ ብዙኃኑን ባሮች ለጥ ሰጥ አድርጎ እንዲበዘበዝና እንዲጨቆን ማድረግ የዚህ የመጨቆኛ ተቋም ዋናው የሕልውናው ምክንያት ነበር።

ከጥንታዊ ጋርዮሽ ወደ ባሪያ አሳዳሪው ስልተምርት በተደረገው ረጂም ሂደት ውስጥ ነበር ይህ የመበዝበዣ ተቋም ቀስ በቀስ የተጸነሰውና ያደገው። የግል ሀብት ብቅ ሲል፣ የሥራ ማከናወኛዎች በጥቂቶች ቁጥጥር ሥር መዋል ሲጀምሩ፣ የጋርዮሽ ህብረተሰብ በመደብ መከፋፈሉ ቀራኒ. እየጎላ መምጣት ሲጀምር መንግሥትም ቀስ በቀስ በቅርጽም በይዘትም እየተሟላ መጣ። በጎሣ በነገድ በብሔረሰብ[x] ደረጃ ላይ የተከሰተው መንግሥት እየተስፋፋ በመሄድ ትልልቅ ግዛቶችን የሚያጠቃልሉ ለምሣሌ እንደ ቻይና እንደግሪክ ሮም ግብጽ ወዘተ... ያሉት መንግሥታት ተቋቁመው እንደነበረ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። ቅርፀቸውና መጠናቸው ይለያይ እንጂ ሁሉም የባሪያ አሳዳሪ መንግሥታት ነበሩ። የተሸነፉትና በቁጥጥር ሥር የዋሉት ጎሣዎች ብሔረሰቦች ነገዶች መንግሥታት አባላትና ዜጎች ወደባርነት ተለውጠው አስከፊውን የብዝበዛና የጭቆና ቀንበር ይሸከሙ ነበር። ከላይ እንደተመለከተው የባሪያ አሳዳሪው መንግሥት ዓላማና ተግባር ባሮችን ጨቁኖ በመያዝ የገዢውን መደብ ጥቅም ማስጠበቅ ነበር።

## 2.3 የምርት ኃይሎች

በባሪያ አሳዳሪው ስልተምርት ውስጥ የምርት ኃይሎች ከፍተኛ ዕድገት አሳይተዋል፣ በጥንታዊ ጋርዮሽ የተጀመሩት የብረት ሥራዎችና መሣሪያዎች የበለጠ ተጠናክረዋል፣ ተሻሽለዋል፣ ዐደ ጥበባትና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች አብበዋል፣ እርሻም ከፍተኛ ዕድገት አሳይቷል፣ የምርት ልውውጥ ንግድ በሰፊው ዘርግቷል። ቀደም ብለው የተከሰቱት ዐበይት

x ~~ብሔረሰብ~~ የባሪያ አሳዳሪው ስልተምርት ሲከሰትም የሚስፋፋውና የህብረተሰብ ዓይነተኛ መለያ የሚሆነው ግን በፊውዳል ስልተምርት መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ማኅበራዊ የሥራ ክፍፍሎች ማለትም ከብት ርቢ፣ ግብርና፣ ዕደ ጥበብና ንግድ የበለጠ ሥር በመስደዳቸውና በመስፋፋታቸው የምርት ኃይሎችን አሳ ደገዋቸዋል፣ አዳብረዋቸዋል:: ግድቦች መስኖዎች፣ ትላልቅ ሕንፃዎች አውራ ጎዳናዎች መርከቦች ስቱዋች በሰውና በእንስሳት የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች /ሁዊል/ የተሠሩት በዚህ ጊዜ ነበር፣ የፍራፍሬና የአትክልት እርሻም ተስፋፍቶ ነበር:: የምርት ኃይሎች የዳበረ ክፍል ሆነው የሰው ዕውቀትና የመሥራት ችሎታም በዚያው መጠን ዳበረ:: ሳይንስ ሥነ ጥበብና የመሳሰሉት መሠረታቸውን አጠናከሩው ብቅ ያሉት በዚሁ ዘመን ነበር::

በባሪያ አሳዳሪው ሥልተ ምርት ውስጥ ባሮች ዋና የምርት ኃይል ናቸው:: እንደመሣሪያ እንደ ቁሳቁስ ቢቆጠሩም የምርቱን ተግባር የሚያንቀሳቅሱት እነሱ በመሆናቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ዋና የሆነውን የምርት ተግባር ያከናውኑ ነበር:: በቤት ውስጥ ሥራ የጀመረው የባሮች ገሊጋሎት በግሪስ በሮም ወደሰፋፊ እርሻዎች ወደአነስተኛ እንዱስትሪዎች ደረጃ ደርሶ እንደነበረ በታሪክ የተመሠከረ ነው:: ዝነኞቹን የጥንታዊት ግብጽን ፒራሚዶች/ትልልቅ ድንጋይ ጠውልቶችና ካቦች/ የሠሩት በባርነት ቀንበር ሥር የነበሩት እሥራኤላውያን ነበሩ:: በምስፖታሚያ በባቢሎን በአሶሪያ በፋርስ በሕንድና በሌሎች አገሮች የሚገኙትን ትላልቅ ሕንፃዎች ቤተ መንግሥቶች፣ ቤተመቅደሶች፣.... የሠሩት ባሮች ነበሩ::በደገብ በጥናት ገና ባይረጋገጥም በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙትን እንደአክሱም ጠውልት ያሉትን ጥንታዊ ሕንፃዎች ባሮች የሠሩት ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል:: ከጥንታዊ ጋር ጸጃ ጋር ሲተያይ የሰው ልጅ በባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ወቅት የምርት ኃይሎችን በማሳደግ ብሎም በአካባቢው ላይ ቁጥጥሩንና የበላይነቱን አጉልቶ በማሳየት በኩል አመርቂ አድርጓል ለማለት ይቻላል::ይህ ታሪክ በሁሉም ህብረተሰብ የታየ ወይም የተከሰተ ነው ማለት አይደለም:: በአብዛኞቹ ግን የተከናወነ እንደሆነ ለመገመት ይቻላል::

## 2.4 የመደብ ቅራኔዎችና የስልተ ምርቱ መውደቅ

በአጠቃላይና በመሠረቱ የባሪያ አሳዳሪው ሥልተ ምርት የወደቀው በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል የተፈጠረው ቅራኔ ከማይታረቅበትና አብሮ ለመኖር ከማይችልበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ ነው ::

በአጠቃላይ የሕብረተሰብ ዕድገት ሕግ መሠረት ተን ቀባያዊና ታዳጊ የሆኑት የምርት ኃይሎችን አፍኖ የያዘው የባሪያ አሳዳሪው የምርት ግንኙነት መለወጥ አስፈላጊ ሆነ ::

የባሪያ አሳዳሪው ህብረተሰብ ሁለት ዐበይት ተፃራሪ መደቦችን ማለትም ጌቶችንና ባርችን በውስጡ ያቀፈ ነው :: እርግጥ አነስተኛ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች እንደነፃ አነስተኛ አምራቾች የዕደ ጥበብ ባለሙያዎች ወታደሮች፣ ቦዘኔዎች የመሳሰሉም አሉ :: ዋናው ቅራኔና ትግል የተካሄደው በሁለቱ ዐበይት መደቦች መካከል ቢሆንም እነዚህኞቹም በተለይ ነፃ አነስተኛ አምራቾችና በመጠኑም ቢሆን ደሆችና ቦዘኔዎች ከተበዝባዥችና ከጭቁኖች ጎን ሆነው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ::

የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት ዓይነተኛ /ምሳሌ የሆነውን ጥንታዊት ሮምን ወስደን የስልተ ምርቱን አወዳደቅና በሌላ መተካት እንመልከት :: ጭቁኖና በብዝበዛው አስከፊነት የተነሳ አምራቾቹ ባሮች በሥራ በመለገም የምርት መሣሪያዎችን በመሰባበር አለፍም በማመጽና በመነሳት የመደብን ትግል አፋፋሙት፣ ሥርዓቱን ከውስጥ አዳከሙት :: ለምሳሌ ስፓርታከስ በሚባለው ባሪያ የተመራውን ትግልና አመፅ መጥቀሱ ሁኔታውን ሊያስረዳ ይችላል :: ምርት እንዳይቀንስ እንዲያውም እንዲስፋፋ ለማድረግ የገዢው መደብ ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ የባሪያ መንጋ ስለአስፈለገው ለዚህ የጦር ኃይሉን አሳደገ ::

በወታደርና ተግባር የተሰማሩት ከፍተኛውን የገበር ሸክም የተጫኑት ነፃ አነስተኛ አምራቾች ነበሩ፤ እነዚህ ባንድ በኩል በሥራው ዓለም የሚወዳደሯቸውንና በሌላ በኩል ለፍተው ደክመው ሕይወታቸውን መስዋእት አድርገው ለገዥው መደብ ጥቅም የሚያገለግሉትን ባሮችን ማምጣትን በመጥላ ትና በመቃወም ባደረጉት ትግል የተልቀ የሮም ግዛት ይበልጥ ተዳከመ ::

በዚሁ ሁኔታ ውጤት የባሮች ቁጥር መቀነስ የዕደ ጥበባት የአነ ስተኛ ኢንዱስትሪዎች የትልልቅ እርሻዎች በአጠቃላይ የኢኮኖሚው መዳከምና የምርት መቀነስን አስከተለ :: ይህንን ለመቋቋም የገዥው መደብ አባላት መሬታቸውን ከፋፍለው ለነፃ አምራቾችና ለባሮችም ማከራየት ጀመሩ :: ይህም የአዲሱ ስልተ ምርት ጥንስስ ሆነ :: የባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ተከፋፍቶና ገና የነበረበት፣ የሮም ግዛት በውስጡ ተፈጥሮ በነበረው የመ ደቦች ቅራኔ ተቦርቡሮና ተዳክሞ ስለነበር በጀርመን ጎሳዎች ወረራ ይቀላሉ ሊፈራርስና ሊንኮታኮት ቻለ :: ሙሉ በሙሉ በባሪያ አሳዳሪው ስልተ ምርት ውስጥ ያሳለፉት ወረራዎች የጀርመን ጎሳዎች ሰፊውን የሮማውያን ግዛት አጥለቀለቀው ከሮማውያን የባሪያ አሳዳሪዎች ጋር በመሆን በማቆጥቆጥ ላይ የነበረውን የፊውዳል ስልተምርት አስፋፉ :: በዚህ ሁኔታ የምርት ኃይሎች በማንሰራራት እድገታቸውን ቀጠሉ ::

ከባሪያ አሳዳሪ ስልተ ምርት ወደፊውዳል ስልተ ምርት ለመሸጋገር አብዛኞቹ ህብረተሰቦች በዚህ ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ወይም ሂደት ውስጥ ነው ያለፉት :: ሆኖም እንደተጨባጭ ሁኔታዎች እንደ እድገት ደረጃዎች ሊለያዩ ይችላሉ :: በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የባሪያውን ስልተ ምርት የእ ድገት ደረጃ ሙሉ በሙሉ ሳይጨርሱ ወይም ገና እንደጀመሩ ወደፊውዳል ስልተ ምርት የተሳለፉ ሊኖሩ ይችላሉ :: እንዲያውም ከላይ እንደተመለከ ተው የመካከለኛው አውሮፓ ጎሣዎች ከሮማውያን ጋር በነበራቸው ቅራኔ

የተፈጸመው ወረራ ባስከተለው ውጤት ሂደቱን ሳይፈጽሙ ወደፊውዳል ስልቱ ወበ ምርት አለፈዋል :: በኢትዮጵያም የአክሱም መንግሥት አወዳደቅና የፊውዳል ስልተ ምርት ማቆጥቆጥ ከላይ የተመለከተውን ሂደት የተከተለ ለመስለ እንደሚችል ባንዳንድ የታሪክ መጻህፍት ተጠቅሟል :: ይህ የበለጠ የሚታወቀውና የሚረጋገጠው ግን ከሰፊና ጥልቅ ጥናትና ምርምር በኋላ ይሆናል ::

## አጭር ማጠቃለያ

1/ የባሪያ አሳዳሪ ስልተ ምርት የመጀመሪያው ሰዎች በመደብ የተከፋፈለበት ህብረተሰብ ሲሆን ይኸም በጥንታዊ ጋርዮሽ ማህፀን ውስጥ ቀስ በቀስ እያደገ የመጣ ነው ::

2/ ስልተ ምርቱ የተመሰረተው በምርት መገልገያዎች የግል ባለቤትነት ላይ ሲሆን አብዛኛው የህብረተሰቡ ክፍል የባርነት ቀንበር ተሸክሞ የሚያመርተውን በሙሉ ለጥቂቶች የገዥ መደቦች ያስረክባል፣ ለእሱ ግን ለህይወቱ ማቆያና እንዲያመርት የሚያስችለው ብቻ ይሰጠዋል :: ብዝበዛውና ጭቆናው እጅግ በጣም አስከፊና አሰቃቂም ነው ::

3/ መንግስት የሚባለው የአንዱን መደብ በሌላው የመጨቆኛና የመበዝበዣ መሳሪያ መጀመሪያ ላይ ብቅ ያለውና ስር እየሰደደ የሄደው በዚሁ ስልተ ምርት ወቅት ነው :: ባሮች ሰጥ ለጥ ብለው ይህንን አስከፊ ጭቆናና ብዝበዛ እንዲቀበሉ ለማድረግ መንግስት የሚባለው መሳሪያ የግድ አስፈለገ ነበር ::

4/ የባሪያ አሳዳሪው ስለተ ምርት ሊፈራርስ የቻለው በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መካከል በተፈጠረው ቅራኔ ባሮች ሌሎች ጭቆኖች ስርዓቱን ከውስጥ ስለቦረቦሩትና ስለአዳከሙት ነው ።

5/ በመደቦቹ መካከል የተካሄደው ውስብስብና ረዥም ትግል በመጀመሪያ ላይ ከፍተኛ እድገት አሳይቶ የነበረትን የምርት ኃይሎችን ስገ ኩሉ የያዘውን የምርት ግንኙነት በጣጠስ በርም የገባርና የፊውዳል ግንኙነት ቀስ በቀስ ስር ሰድዶ በመጨረሻ ላይ አርጌው ስለተ ምርት ሲገኮታኮት በሰፍራው የፊውዳል ስለተ ምርት ተመሰረተ ።

## ጥ ያ ቄ ዎ ች

1/ የባሪያ አሳዳሪ ስለተ ምርት ዋይነተኛ ባሕርያት ምን ምን ና ቸው? አብራራ

2/ የምርት ግንኙነቱስ እንዴት ነው?

3/ የመንግሥት አመጣጥ እንዴት ነበር?

4/ የባሪያ አሳዳሪው ስለተ ምርት ዋና ዋና መደቦችና ቅራኔዎች ምን ምን ና ቸው?

5/ የምርት ኃይሎች እድገት እስከምን ድረስ ነበር?

6/ የባሪያ አሳዳሪውን ስለተ ምርት ምንድነው የጣለው? ወይም እንዴት ነው የወደቀው?

7/ ተከው ወይም አዲሱ ስለተ ምርት እንዴት ተጸነሰ? የሽግግሩ ሂደት እንዴት ነበር?

## የሚነበቡ መጻሕፍት


1. ከዚህ በላይ የተመለከቱት

2. An Introduction to Economic History of Ethiopia
- R. Pankhurst
pp 3-16

## 3.0 የፊውዳል ስልተምርት

በህብረተሰብ የዕድገት ሕግጋት መሠረት አንድ ስልተምርት በሌላው እየተተካ ከዝቅተኛ ወደከፍተኛ ደረጃ እንደተመጣና እንደሚመጣ ከዚህ በላይ ተገልጿል። የፊውዳል ስልተምርትም ከህብረተሰብ ዕድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ ከባሪያ አሳዳሪው ስልተምርት ቀጥሎ የሚመጣ ነው። ይህም ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ተጠቅሷል። የፊውዳል ስልተምርትን ዓይነተኛ የሚያደርገው እንቅስቃሴውና ግንኙነቶቹም የሚመሠረቱት በእርሻ ላይ መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን አንድ ስልተምርት በተወሰነ የዕድገት ደ..ጃና ወቅት የአንድ ህብረተሰብ ዓይነተኛ ገጽታ ቢሆንም የቀደምው ቅሪቶችና የወደፊቱም ጥንስሶች መኖራቸው በታሪክ የተረጋገጠ ነው። በዚህም መሠረት ፊውዳሊዝም በሰፈነበት ህብረተሰብ ውስጥ የባሪያ አሳዳሪው ቅሪቶች ከዚህም አልፎ የጥንታዊ ጋርዮሽ ባሕርያትን የሚያንፀባርቁ ሁኔታዎች ይኖራሉ። እንደዚሁም ፊውዳሊዝምን የሚተካው ስልተምርት ማለትም የካፒታሊስት ስልተምርት ገጽታዎች በወቅሳነት ይንፀባረቃሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ በአጠቃላይ ሲታይ የ፡ብረተሰብ ዕድገት ከጥንታዊ ጋርዮሽ ወደባሪያ ከዚያ ወደፊውዳል ከዚህ ለጥቆ ወደካፒታሊዝም ከዚያም ወደሶሺያሊዝም መሆኑ ቢረጋገጥም በልዩ ልዩ አጋጣሚ ምክንያቶች አንዳንድ የዕድገት ደረጃዎች ሊዘለሉ ይችላሉ። ወደኋላ እንደምንመጣበት አንዳንድ ህብረተሰቦች በወረራ በጦርነት ወዘተ... ምክንያቶች ከጥንታዊ ጋርዮሽ ስልተምርት ወደፊውዳል ተሸጋግረው ተገኝተዋል። እንደዚሁም ከከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት ወደሶሺያሊዝም የተሸጋገሩና በመሸጋገርም ላይ ያሉ/ለምሳሌ የእኛ ሁኔታ/ ህብረተሰቦች አሉ።

## 3.1 የፊውዳል ስለ ተምርት አመጣጥ

ፊውዳሊዝም በባሪያ አሳዳሪው ስለ ተምርት ማህፀን ውስጥ ተጸንሶ ሊፈጠር የቻለው እንደሚከተለው ነው። የባሪያ አሳዳሪው ስለ ተምርት ምንም እንኳ ከጥንታዊው ጋርዮሽ ስለ ተምርት ጋር ሲወዳደር ከፍ ያለ የምርት ኃይሎችን ዕድገት ያመጣ ቢሆንም ካንድ ደረጃ በኋላ ግን ዕድገት እንዲቀጥል በሥርዓቱ ውስጥ ያለው የምርት ግንኙነት ሊፈቅድለት አልቻለም። ስለሆነም ለም መሬቶች ጠማቸውን እያደሩ፣ የዕደ ጥበባት ምርት እየቀነሰና የምርት ለውውጥም እየቀዘቀዘ ሄደ።

ምርት እየቀረ ቀዘ ሲሄድም ባሮች የመደብ ትግሉን አፋፋሙት፤ ሆኖም ባሮች ጌቶቻቸውን የሚጠሉና በጌቶቻቸውም ላይ ትግል ያካሄዱ ቢሆንም በንቃተ ሕሊና ዝቅተኝነትና በድርጅት ጉድለትም ምክንያት ትግላቸው የሰውን በሰው መበዝበዝን ሊያጠፉ የቻለ አልነበረም።

የባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት የገዢ መደብ አባላት ባሮችን እንደቀድሞ ለመበዝበዝ ባለመቻላቸው አዲስና የተለየ የብዝበዛ ዘዴና መንገድ ለመቀየስ ተገደዱ። እነዚህ የገዢ መደብ አባላት ፊት በግል ባለቤትነት ይዘውትና ባሮችን ያሠሩበት የነበረውን መሬታቸውን ለሁለት ከፍለው ከፊሉን በግል ይዞታቸው ሥር ሲያቆዩት ከፊሉን ባሮችና ነፃ መሬት አልባ ለነበሩ ግለሰቦች በግል ይዞታነት አከፋፈሏቸው። እነዚህ ቀድሞ ባሪያ የነበሩና መሬት አልባ የነበሩ የሚያርሱት መሬት በመጠኑም ቢሆን የራሳቸው የሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎች ስለነበራቸው በተጨማሪም ከሚያመርቱት ከፊሉን ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል በመቻላቸው የሥራ ፍላጎታቸው ከፍ ሊልና ምርታማነታቸው ሊጨምር ችሏል። ይሁን እንጂ የምርታቸውን ውጤት በከፊል ለገዢው መደብ አባላት ከመስጠታቸውም በላይ የጉልበት አገልግሎት መስጠት ስለነበረባቸው ነፃነታቸውም የተሟላ ስላልነበር የብዝበዛውና የጭቆናው ሁኔታ እምብዛም ከባሪያው ሥርዓት የተሻለ አልነበረም።

ፊውዳሊዝም በአጠቃላይ የህብረተሰብን ዕድገት ሕግጋት ተከተሉ የሚመጣ ሲሆን እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የተለየ ባሕርይ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ በምዕራብ አውሮፓ በመካከለኛው ዘመን ፊውዳሊዝም ሊፈጠር የቻለው በአንድ በኩል በዚያ ጊዜ የነበረውን የሮማውያንን የባሪያ አሳዳሪ ሥርዓት በውስጥ የመደብ ቅራኔና በውጭ ወረራ በመገርሰሱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወራሪዎች ገና ወደባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ያልተሸጋገሩ ስለነበሩ ይዘውት የመጡት በጎሣ ላይ የተመሠረተ የጥንታዊ ጋርዮሽ ሥርዓት በመፈራረሱ ምክንያት ነበር።

ቀደም ብሎ በባሪያው ስልተምርት ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ ወራሪዎች በማቆጥቆጥ ላይ የነበረውን የፊውዳል የምርት ግንኙነት በመከተል ራሳቸውን ከገዢው መደብ ጋር በማቀላቀልና በማዋሃድ የበለጠ አጠናከሩት። ይሁንና ዝብረትን፣ በተለይም መሬትን፣ በግል ባለቤትነት መያዝ በግለሰቦች መካከል የሀብት ልዩነትን አስፋፋ። ሀብታም የሆኑ የህብረተሰቡ አባላት ደሀ የሆኑትን የህብረተሰብ አባላት መሬት በመንጠቅ የበለጠ ትልልቅ ባለመሬቶች ሆኑ። ስለሆነም የገዢው መደብ የበለጠ ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ እየተደራጀ መጣ።

ከገዢው መደብ አባላት ገንባር ቀደም የጦር መሪዎች ጥቅም ላይ የተመሠረተ ጦርነቶችን አስነስተው አሸናፊዎች ራሳቸውን ንጉሥ አድርገው በመሰየም ንጉሣዊ አገዛዝን አቋቋሙ። ንጉሦችም በየግዛቶቻቸው የፊውዳሉ ሥርዓት ቁንጮ በመሆን ሰፋፊ መሬቶችን ከያዙ በኋላ ቀሪውን መሬት ለሹማምንቶቻቸው አከፋፍለው በምትኩም ንጉሦች በሚያካሂዱት ጦርነቶች እንዲካፈሉና ከዝርፊያውና ከብዝበዛው የሚገኘውን ሀብት እንዲያካፍሏቸው አደረጉ።

ኦክሲቴኒያም ለብዙ ዘመናት ያዚሁ ዓይነት ሁናቴ እንደነበር የታሪክ ማስረጃዎች አሉ።

ንጉሠ ነገሥቱ ለከፍተኛ ባለሟሎቻቸው ያከፋፈሉት መሬት "ፊፍ" ይባላል፡፡ ይህም ቃል "ፊውደም" ከተሰኘ የላቲን ቃል የመጣ ነው፡፡ የመሬት ስጦታ ያገኙት ባለሟሎች "የፊውዳል ገዢዎች" ተባሉ፡፡ የበዝባዥ ሥርዓቱም "ፊውዳሊዝም" እየተሰኘ ይጠራ ጀመር፡፡ የሃይማኖት ድርጅቶችና የድርጅቶቹ መሪዎችም መጠኑ ከፍ ያለ መሬት ከንጉሠ ነገሥቱ እየተሰጣቸው በምትኩም ንጉሣዊው አገዛዝ በሰፊው ሕዝብ መካከል ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ለፊውዳሉ የበዝባዥ ሥርዓት መጠናከርና በሰፊው ሕዝብ መካከል ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ለፊውዳሉ የበዝባዥ ሥርዓት መጠናከርና በሰፊው ሕዝብ ጫንቃ ላይ ተጭኖ ለመቆየት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

## 3.2 የፊውዳል ህብረተሰብ የምርት ግንኙነቶች

የፊውዳል ህብረተሰብ የምርት ግንኙነቶች የተመሠረቱት በፊውዳሊስቶች የመሬት የግል ባለቤትነትና በገባሮች ላይ ባላቸው ከፊል ባለቤትነት ላይ ነው፡፡ በፊውዳሉ ስር ተምርቶ ገባሩ የሚያርሰው መሬት ይዞታና አንዳንድ የማምረቻ መሣሪያዎች ባለቤት ስለሆነ ሁኔታው ከባሪያው የተለየ ነው፡፡ ስለዚህ ገባሩ ከባሪያ ጋር ሲነፃፀር ምርታማነትን ለማሳደግ ከፍ ያለ ፍላጎት አለው፡፡

የፊውዳሉ ገዢ መደብ አባላት በግል ባለቤትነት ከያዟቸው ትልልቅ መሬቶች በአብዛኛው በግላቸው በመያዝ ቀሪውን በተቆረጡ ስብታቶቻቸውና በመጠረሻም ለገባሮች ያከፋፍሏቸው ነበር፡፡ በገባሮቻቸው ላይ ያላቸው ሥልጣን ከፍተኛ ሲሆን ገባሮች የሚሸከሙት የጭቆናና የበዝበዛ ቀንበር እጅግ የከፋ ነው፡፡

የፊውዳል በዝበዛ ዓይነቶች አያሌ ሲሆኑ የጉልበት ሥራ/አገልግሎት፣/ የምርት ክፍያ ወይንም የገንዘብ መልክ ሊይዙ ይችላሉ፡፡ ፊውዳሊዝ

ምን በሚመለከት ረገድ በቀጥታ በጉልበት መልክ የተደረገ ብዝበዛ ዋናው የብዝበዛ ዓይነት የነበረው በተለይ በፊውዳሉ ዘመን መጀመሪያ ክፍል ላይ ነበር። በዚህ የብዝበዛ ዓይነት መሠረት ገበሬ በሣምንት ለተወሰኑ ቀናት፣ ለምሳሌ ለሦስት ቀናት፣ ለፊውዳል ገዢው ይሠራና በቀሩት ቀናት ውስጥ የራሱ ይዞታ በሆነው መሬት ላይ ይሠራ ነበር። በተለይ የፊውዳል ገዢው ይዞታ የሆነውን መሬት በሚያለማበት ወቅት ገበሬ የጉልበትን ምርታማነት ከፍ ለማድረግ ምንም ዓይነት ፍላጎት አልነበረውም። ስለሆነም የፊውዳል ገዢዎች ተቆጣጣሪዎችን በማሰማራት ገባሮች በኃይል እንዲሠሩ ያስገድዷቸውና እንዳንዷም በሰውነታቸው ላይ ጉዳት ያደርሱባቸው ነበር።

የፊውዳሉ ሥርዓት እየዳበረ ሲሄድ በምርት ዓይነት የሚደረግ ብዝበዛ እየተጠናከረ፣ በጉልበት ሥራ መልክ ከሚደረገው ብዝበዛ ጋር ጎን ለጎን ብሎም እየተካው መሄድ ጀመረ። ጉልበትን በቀጥታ ከማስበዝበዝ ሌላ/ማለት አገልግሎት ከመስጠት ሌላ/ መጠኑ ከፍተኛ የሆነ እህል፣ ከብት፣ ዶሮ፣ ሌሎች የእርሻ ምርት ዓይነቶች እንዲሁም ልዩ ልዩ የዕደ ጥበባት ምርቶች ገበሬ ለፊውዳል ገዢው መስጠት ነበረበት።

በተለይ በፊውዳሉ ዘመን መጨረሻ ክፍል የሸቀጣ ሸቀጥና የገንዘብ ልውውጥ ስለዳበረ የፊውዳሉ ብዝበዛ የገንዘብ ይዘት ተጠናከረ። ይህ የገንዘብ መልክ የያዘ ብዝበዛ በሰዎች መካከል የነበረውን የግል ሀብት መጠን ልዩነት እያሰፋው በመሄዱ ለካፒታሊዝም ማቆጥቆጥ መሠረት ሆነ።

በብዙ አገሮች፣ በኢትዮጵያም ጭምር፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሦስቱ የፊውዳሉ ሥርዓት የያዟቸው የብዝበዛ መልኮች በአንድነት ሊካሄዱ ችለዋል። የፊውዳሉ የብዝበዛ ቀንበር በጫንቃቸው ላይ የተጫነባቸው ገባሮች በጭማሪም እንደየአገሩ ሁኔታ ለሚጠቀሙበት የእህል ወፍጮ፣

የዐደ ተበባት ማምረቻ ቦታዎችና መሣሪያዎች፣ ከብቶቻቸውን ሣር ለሚያስገጡበትና ውሃ ለሚያጠጡበት እንዲሁም እንጨት ለማሠብሰቢያ ቦታዎች፣ ለሚጠቀሙባቸው መንገዶች፣ የገበያ ቦታዎችና ፍርድ ቤቶች እንዲሁም ለመጠቀሚያ፣ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለፊውዳል ገዢዎች ያደርጉ ነበር።። በእነዚህ ሁሉ የብዝበዛ ዓይነቶች ላይ ለመንግሥት በልዩ ልዩ ደረጃ ይከፈል የነበረውና ለሃይማኖት ድርጅቶች ይገባ የነበረው ገበር፣ በየስሙ "ክብሪታ" መልክ ለፊውዳል ገዢ መደብ አባላት ይደረግ የነበረው ክፍያ ሲታከልበት የብዝበዛው አስከፊነት ምን ያህል እንደነበር ለመገመት አያዳግትም።።

በቀድሞ አብዮት ኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረው የፊውዳል ሥርዓትም በምዕራብ አውሮፓ በመካከለኛው ዘመን እንደነበረውና እንደዓንኛውም ሌላ የፊውዳል ሥርዓት የራሱ የሆነ ባሕርይ ነበረው።።

በሰሜን ኢትዮጵያ የርስት ሥሪት፣ በደቡብ ኢትዮጵያ የገባር ስሪት፣ ኋላም የባለመሬትና የጭሰኛ ግንኙነት ዋና ዋናዎቹ የመሬት ሥሪቶች ይሁኑ እንጂ በሰሜንም ሆነ በደቡብ አምራቾች ለፊውዳል ገዢዎች ጉልበታቸውን ሲያስበዘብዙ መኖየታቸው የታወቀ ነው።። በሰሜን የነበረው የቤተዘመድ የጋርዮሽ የመሬት ይዞታ ምንም እንኳ ከደቡብ ጋር ሲወዳደር ብዙ ተለለቀ ባለመሬቶችን ያልፈጠረ ቢሆንም አርሶ አደሩን ከፊውዳል ገዢዎች ብዝበዛ ሊያድነው አልቻለም።። ከነጭ ለባሹና ከጭቃ ሹም እስከ ከፍለ ሀገር ፊውዳል ገዢ፣ ከዚያም እስከ ፊውዳሉ ሥርዓት ቁንጮ የነበረው ንጉሠ ነገሥት ድረስ የአርሶ አደሩን ምርት ደረጃ በደረጃ ሲጋፈፈሉት ኖረዋል።። የሃይማኖት ድርጅቶችና መሪዎቻቸም ከጠቀላላው የእርሻ መሬት ከሦስት እጅ አንድ ያክላል ተብሎ የሚገመተውን በባለቤትነት በመያዝ በከፍተኛ ደረጃ የብዝበዛው ሥርዓት ተባባሪና ከሥርዓቱም ተጠቃሚ ነበሩ።።

በሰሜን ኢትዮጵያ አርሶ አደሩን ለብዝበዛ የዳረገው በወል የመሬት ይዞታ ላይ ተዋቅሮ የነበረው ጕልታዊ ሥርዓት ብቻ አልነበረም። በመሬት ይዞታ ስለመስተካከል/በመሬት መከፋፈልና መሬት የሌላቸው ከሌላ ሥፍራ ተሰድደው የመጡና ዐደ ጠባገ/ ምክንያት ጭሰኝነትም ነበር። በሰሜን በፖለቲካ ሥልጣን፣ በሃይማኖትና በሌሎችም ልዩ ልዩ ዘዴዎች በመጠቀም ሰፋፊ መሬት የያዙ ገለሰቦች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች ነበሩ። እንግዲህም የሥጋ ዝምድና ላይ የተመሠረተ የጋርዮሽ የመሬት ይዞታ ከትውልድ ወደትውልድ የሚያልፍ በመሆኑ ከመጀመሪያው ሰፋፊ መሬት በያዙና በሌሎች ቤተሰቦች መካከል የማይናቅ የመሬት ይዞታ መጠን ልዩነት ይታይ ነበር። ስለሆነም በሰሜን.ከአርሻው መሬት ፊገምት አሥራ አምስት በመቶ ያህሉ በቅድመ አብዮት ይታረስ የነበረው በጭሰኞች ነበር። እነዚህም የሰሜኑ ክፍለ ሀገር ጭሰኞች ከባለመሬቶች ጋር የነበራቸው የምርት ግንኙነት በደቡብ ክፍለ ሀገር የነበሩት ጭሰኞች ከነበራቸውና ከዚህ በታች ከሚዘረዘረው እምብዛም የተለየ አልነበረም።

የገባር ስሪት፣ ኋላም ጭሰኝነት ሰፍኖበት በነበረው በደቡብ ኢትዮጵያም የፊውዳል ብዝበዛው አድግ የከፋ ነበር። አርሶ አደሩ መሮባት ከነበረበት ገዳጅ መካከል አርቦ ወይንም ሲሦ ማፍሰስ፣ አሥራት መክፈል፣ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ማር፣ እንጨት በነፃ.ማቅረብ፣ ለፊውዳል ገዢው ያከፈለውን እህል መፍጨት፣ እህልና ዱቄት ወደ ባለመሬቱ ቤት ማጓጓዝ፣ ለባለመሬቱ ቤት መሥራት፣ አጥር ማጠር፣ ከብት መጠበቅ፣ እንደዕቃ ተሸካሚ፣ ተላላኪና አጃቢ ሆኖ ማገልገል፣ በየዓመት በዓሉ፣ ባለመሬቱ ሲሞት፣ ሲያገባ፣ ሲወልድና በሌሎች ልዩ ልዩ ወቅቶች በገንዘብና በዓይነት "ስጦታ" ማበርከት ነበር። ለመትከያ፣ ለዳኝነት እየተባሉ ለባለመሬቱ ይደረጉ የነበሩ ክፍያዎች ቢጨመሩም እንኳ የነበሩት የብዝበዛ ዓይነቶች ዝርዝር የተሟላ ሊሆን የሚችል አይደለም። በተለይ የገባር ስሪት

በጭሰኝነት ከተቀየረ በኋላና በገንዘብ መልክ የሚደረገው ክፍያ ጎልቶ መታየት ከጀመረ ወዲህ የፊውዳል ገዢዎች የገንዘብ ጥም ሊረካ ባለመቻሉ በዝበዛውም ያገኑ ያህል የበለጠ እየከፋ ሄደ:: ይህም ለአብዮቱ ፍንዳታ አንድ መሠረታዊ ምክንያት መሆኑ የሚካድ አይደለም::

በመካከለኛው ዘመን በምዕራብ አውሮፓ የነበረው የፊውዳል ስልተ ምርት በቅድመ አብዮት በአገራችን ከነበረው ጋር ሲወዳደር የምዕራብ አውሮፓው ከፍተኛ የዕደ ጥበባት ምርት ዕድገት ደረጃ ታይቶበታል:: በምዕራብ አውሮፓ የሸቀጣ ሸቀጥ ምርት ከማደጉ ጋር ተያይዞ የዕደ ጥበባት ምርቶች እየዳበሩ፣ የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች አብዛኞቹ ያከናውኑት የነበረውን የእርሻ ሥራ ቀስ በቀስ በመተው በከተሞች ውስጥ ከተሙ:: የከተማ ነዋሪዎችም በአብዛኛው የዕደ ጥበባት ባለሙያዎችና ነጋዴዎች ሆኑ:: እነዚህ በከተሞች ይገኙ የነበሩ የዕደ ጥበባት ባለሙያዎችም የፊውዳሎችን ብዝበዛ ለመከላከልና ከገጠር ወደ ከተማ ከሚፈልቁ ዕደ ጥበባት ባለሙያዎች የሚያጋጥማቸውን ውድድር ለማክሸፍ በየሙያ ማህበራት ተደራጁ:: የየሙያ ማህበራቱ አባል ለመሆን የሚችሉትም በጀማሪ ደረጃ በሙያ የሚሰለጥኑ ሰዎችና መካከለኛ የሙያ ችሎታ ያላቸውን ሰዎች በሥራቸው ያስተዳድሩ የነበሩ ከፍተኛ የዕደ ጥበብ ሙያ እንዳላቸው የተመሰከረላቸው ሰዎች ብቻ ነበሩ:: እነዚህ የሙያ ማህበራት ስለሥራ ሰዓት፣ ስለምርት መጠንና ጥራት፣ ስለ ዋጋና በለመሳሰሉት ጉዳዮች ውሳኔዎች ያስተላልፉና ውሳኔዎችንም በሥራ ላይ ያውሉ ነበር:: በየከተማው ይኖሩ የነበሩ ነጋዴዎችም እንደዚሁ ጥቅማቸውን ለማስከበር የነጋዴዎች ማህበራትን አቋቋሙ::

በመጀመሪያ የሙያ ማህበራት በከተማ ውስጥ የዕደ ጥበባት ምርቶች እንዲዳበሩና የምርቱም ጥራት እንዲሻሻል አስተዋጽኦ አድርገው ነበር:: የኋላ ኋላ ግን ለምርት ኃይሎች ዕድገት እንቅፋት እየሆኑ ሄዱ::

የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች ማኅበራት ስለዕደ ጥበባት ምርት ይከተሏቸው የነበ፣ ጥብቁ ደንቦች የባለሙያዎችን የመፍጠር ችሎታ አፍነው ከመያዛቸውም በላይ የምርት ቴክኒክን መዳበር አገቱ። አባላቱ ውድድር እንዳይበዛባቸው ሲባል አዲስ ባለሙያዎችን በአባልነት ሲሰመቀበለ የየሙያ ማኅበራቱ ልዩ ልዩ እንቅፋቶችን ይፈጥሩ ነበር። ስለሆነም በከፍተኛ ባለሙያዎች ሥር ይሰለጥኑ የነበሩ ሰዎች ከፍተኛ ሙያ እንዳ ሳቸው [illegible]ሰከርላቸው የየሙያ ማኅበራቱ አባል ለመሆን ይህም የሚያስከትለውን ወጪ ለማግኘት ሳይችሉ ቀርተው ሕይወታቸውን በሙሉ ተቀጣሪ ምንደኛ ሆነው እንዲኖሩ ተገደደው ነበር። ቀደም ሲል ከሙሉ ገደል በአባትና በልጅ መካከል የነበረ ግንኙነት ይመስል የነበረው በከፍተኛ ባለሙያዎችና ያሰለጥኗቸው በነበሩ ሰዎች መካከል የነበረው ግንኙነት ጠባዩን ቀየረ። ያሰለጥኗቸው የነበሩትን ሰዎች በአነስተኛ ክፍያ ከ14 እስከ 16 ሰዓት በቀን በማሠራት ከፍተኛ ባለሙያዎች በዝበዛውን አባባሉት። ተበዝባዦቹም፣ በተለይም መካከለኛ የሙያ ችሎታ የነበራቸው፣ ጥቅማቸውን ለማስከበር ሲሉ በሕቡዕ የወገንማማችነት ድርጅቶች ውስጥ ተሰባሰቡ። ይህም ድርጊት በበኩሉ ከየሙያ ማኅበራቱና ከየከተሞች ባለሥልጣኖች ተጨማሪ ተጽእኖን ሊያስከትል ችሎ ነበር።

በአገራችን የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች ለህብረተሰቡ አስፈላጊ የሆኑ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን፣ ልብሶችን፣ የእርሻና የጦር መሣሪያዎችን፣ ጌጣጌጦችንና ሌሎችንም የምርት ዓይነቶች እየሠሩ ሲያቀርቡ ኖረዋል። በተለይም ባለሙያዎች ምርቶቻቸውን ለፊውዳል ገዢዎች በነፃ ወይንም ለስሙ በአነስተኛ ክፍያ እንዲያቀርቡ ይገደዱ ነበር። ሆኖም በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ዕደ ጥበባት ባለሙያዎች በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲናቁና ዝቅተኛ ቦታ እንዲኖራቸው ከመደረጉም ሌላ በማኅበር ተደራጅተው ጥቅማቸውን ለማስከበር እንዳችም መብት አልነበራቸውም። ይህም የሥራ ምርታማነትንና የምርት ኃይሎችን ዕድገት አፍኖ ይዞ ነበር።

## 3.3 የምርት ኃይሎች ዕድገት በፊውዳሉ ህብረ ተሰብ

የፊውዳሉ ስልተምርት በተለይ በምዕራብ አውሮፓ ተንሰራፍቶ በነበረበት በመካከለኛው ዘመን በምርት ኃይሎች በኩል ከፍተኛ ዕድገት ሊታይበት ችሏል:: የምርት ዕድገት ከፍተኛነትም ጉልህ ሆኖ የሚታየው በባሪያ አሳዳሪው ሥርዓት ዘመን ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ነው::

በእርሻው መስክ የተሻሻሉ የአመራረት ቴክኒኮች በሥራ ላይ ሊውሉ ችለዋል:: የብረት ማረሻና ሌሎችም ከብረታ ብረት የተሠሩ መሣሪያዎች በሰፊው ሥራ ላይ ውለዋል:: ለንደወይን እርሻ፣ የፍራፍሬ እርሻ፣ ለገበያ የሚሆን ምርት የሚያስገኝ የጓሮ አትክልት የመሳሰሉ አዳዲስ የእርሻ መስኮች ዳበሩ:: የእንስባት እርባታ፣ በተለይም የፊውዳል ገዢዎች ለጦርነት ይጠቀሙባቸው የነበሩ ፈረሶች እርባታ ዳበሩ::

ቀስ በቀስም የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች የሚጠቀሙባቸው የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎችና ጥሬ ዕቃዎችን የመለወጥ ዘዴዎች ከፍተኛ መሻሻልን አሳዩ:: ለምሳሌ ሸማን በሚመለከት ረገድ በጥጥ ፈትል፣ በማዳወርና በሸማ ሥራ በኩል የተገኙ ለውጦች ከፍተኛ ነበሩ:: ብረት በማቅለጥና በመቀጥቀጥ በኩል የተደረገውም ከፍተኛ መሻሻል ካስከተላቸው ከፍተኛ ለውጦች መካከል የሥራ ማከናወኛ መሣሪያዎች ተሻሽለው መሠራት ይገኙበታል::

የአቅጣጫ ማሳያ መሣሪያ/ኮምፓስ/ና የመሬት ካርታ መሠራት፣ እነዚህም በውቅያኖስ ላይ ጉዞ በኩል ያስከተሉት ከፍተኛ መሻሻል፣ የወረቀት መሠራትና የህትመት ሥራ መጀመር፣ ነፋስንና ውሃን በመሳሰሉ የተፈጥሮ ኃይሎች ከባድ ሥራዎችን መሥራትና ማንቀሳቀስ በፊውዳሉ ስልተምርት ውስጥ ለምርት ኃይሎች ዕድገት ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት ከነገሮች መካከል የሚገኙ ናቸው::

የምርት ኃይሎች ዕድገት እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ቢቀጥልም የፊውዳሉ የምርት ግንኙነት ባለው የጎታችነት ባሕርይው ለዕድገቱ ማነቆ እየሆነ ሄደ። ስለሆነም ታዳጊ በሆኑት የምርት ኃይሎችና ጎታች በሆነው የፊውዳል የምርት ግንኙነት መካከል ጉልህ የሆነ ቅራኔ በመታየቱ ወደ ታዳጊዉና ተራማጅ ስልተ ምርት መሸጋገር አስፈላጊነቱ እየተከሰተ መጣ። ይህም ከፒታሊዝም በፊውዳል ማህፀን ውስጥ እንዴት እያደገና እየዳበረ እንደሚመጣ በሚከተሉት ገጾች ውስጥ ይብራራል።

በአገራችን ሰፊው አርሶ አደርና ዕደ ጥበባት ባለሙያዎች ለዘመናት ይጠቀሙባቸው የነበሩ መሣሪያዎችና የአሠራር ዘዴዎች በአብዛኛው ኋላ ቀር እንደ ነበሩ የታወቀ ነው። ሆኖም የፊውዳሊዝምና የካፒታሊዝም ቅንጅት ያስከተለው የተዛባ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአንዳንድ መስኮች በተለይ ከውጭ የመነጩ የምርት ኃይሎች በሥራ ላይ እንዲውሉ አስችሎ ነበር። ለምሳሌ ቁጥራቸው ውሱን በሆነ ሰፋፊ እርሻዎችና ፋብሪካዎች ዘመናዊ መሣሪያዎችና የአሠራር ዘዴዎች በሥራ ላይ ውለዋል። አድኃሪው የፊውዳሉ የምርት ግንኙነትና ዓለምአቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ባደረጉት ተጽዕኖ እነዚህ የምርት ኃይሎች ለማደግ አልቻሉም ነበር። በአብዮታችን የተቀዳጀነው ድል አዲስ የምርት ግንኙነቶችን በመፍጠር ለምርት ኃይሎች መዳበር አመቺ ሁኔታን አስገኝቷል። የዚህ ውጤት ጎልቶ የሚታየው በተለይ በእርሻ በኩልና በገጠር ነው። በሌላውም መስክ ወደፊት አብዮቱ ጠላቶችን በመደምሰስ ሥር እየሰደደ ሲሄድ የምርት ኃይሎች በሁሉም መስክ ያድጋሉ፣ ይዳብራሉ።

## 3.4 የካፒታሊዝም በፊውዳሉ ሥርዓት ማህፀን ውስጥ መጸነስ

በፊውዳሉ ዘመን ከጊዜ ወደጊዜ የሸቀጣ ሸቀጥ ምርት እያደገና እየዳበረ በመምጣቱ በተለይ የገጠሩ የእርሻ ምርትና የከተማው የዕደ ጥበባት ምርት፣ በበዛት ለለውጥ ወደገበያ መቅረብ ጀመረ። በሰዎ ሰዎ ክፍላተ ሀገር መካከል የነበረው የኢኮኖሚ ግንኙነት እንቅፋት /ለምሳሌ የኬላ ቀረጥ፣ የመጓጓዣ ችግር፣ ወዘተ/ እየተወገደ ብሔራዊ ገበያ ተዘረጋ። በውቅያኖስ ላይ ጉዞ በኋላ የተደረጉ መሻሻሎች ለውጭ ንግድ መዳበርና ለዓለም አቀፍ ገበያ መደራጀት መሠረት ጣሉ።

ንግድ እየዳበረና የዓለምአቀፍ ገበያ እየተስፋፋ በሄደ መጠን በየሙያ ማህበራት ተጽእኖ ሥር የነበሩት የዕደ ጥበባት የምርት ድርጅቶች ከፍተኛ ዕድገት በማሳየት ላይ የነበረውን የሸቀጣ ሸቀጥ ፍላጎት ለማሟላት አልቻሉም። ሆኖም የሸቀጣ ሸቀጥ ምርት መስፋፋቱ በተንገሸ ዕደ ጥበባት አምራች ድርጅቶች መካከል መታየት ጀምሮ የነበረውን የመጠን ልዩነት ስላባባሰው አንዳንዶቹ ድርጅቶች በከፍተኛ መጠን በመደራጀትና ቀጥር ጉልበት በመበዝበዝ ወደሚካሄድ የካፒታሊስት ማምረት ተግባር ሊሸጋገሩ ቻሉ።

በከተሞች አካባቢ የንግድና የዕደ ጥበባት ምርት ወደካፒታሊስታዊ ምርት መሸጋገር የተከናወነው በሁለት መንገዶች ነው። አንደኛው መንገድ እላይ እንደተመለከተው በዕደ ጥበባት ባለሙያዎች መካከል የነበረው የሀብት ልዩነት እየሰፋ በሄደ ቁጥር ከመካከላቸው ጥቂቶቹ አብዛኞቹን የማምረቻ መሣሪያዎች በቁጥጥራቸው ሥር አዋሉ። ብዙኃኑ ባለሙያዎች ከመሣሪያዎቻቸው ተላቀው ለጥቂቶች በክፍያ ተቀጥረው ጉልበታቸውን ለማስበዝበዝ ተገደዱ።

ሌላው መንገድ ነጋዴዎች የንግድ ካፒታላቸውን ወደኢንዱስትሪ ካፒታል መቀየራቸውና ዕደጥበባት አምራቾችን ቀስ በቀስ በቁጥጥራቸው ሥር ማዋላቸው ነበረ። አደማመሩና ሂደቱ እንደሚከተለው ነው። ነጋዴዎች በመጀመሪያ በአርሶ አደሩና በዕደ ጥበባት አምራቾች መካከል የሸቀጣ ሸቀጥ ልውውጥ እንዲደረግ በደላላነት ማገልገል ይጀምራሉ። በኋላም በቀጥታ ከአምራቾች ሸቀጣ ሸቀጦችን በመግዛት ራቅ ወዳሉ ሥፍራዎች እየወሰዱ በትርፍ ይሸጧሉ። እንዲሁም ለዕደ ጥበባት አምራቾች ገንዘብ እያበደሩና ለምርት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን እያቀረቡ ምርታቸውን በተወሰነ ዋጋ እንዲሸጡላቸው አምራቾችን ግዴታ ውስጥ ያስገቧቸዋል። በተለይ የደከሙ ዕደጥበባት ባለሙያዎችን በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል ለምርት የሚያስፈልጓቸውን ዕቃዎች እያሟሉላቸው የተወሰነ የምርት ዓይነትና መጠን አምርተው በተወሰነ ዋጋ እንዲያቀርቡላቸው በማድረግ ነጋዴዎች አሰሪዎችም አከፋፋይም ይሆናሉ። ቀስ በቀስም ነጋዴዎች ለአምራቾች ጥሬ ዕቃዎችን ከማቅረብ አልፈው የምርት መሣሪያዎችንም ያቀርባሉ። በዚህ አኳኋን ዕደ ጥበባት ባለሙያዎች የምርት መሣሪያዎች ባለቤትነታቸውን ይገፈፋና ተቀጥረው በምንዳ መተዳደር ይጀምራሉ። የንግድ ካፒታሊስቶችም የኢንዱስትሪ ካፒታሊስቶች/ባለኢንዱስትሪዎች/ ይሆናሉ። ይህ ሂደትና ሁኔታ በሥራ ክፍፍልና አደረጃጀት በምርት ኃይሎች መሻሻልና ዕድገት ብሎም በምርት ዕድገት በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

በገጠርም የፊውዳሉ የምርት ግንኙነት መፈራረስና በካፒታሊስት የምርት ግንኙነት መተካት ሂደት ከዚህ የተለየ አልነበረም። የሸቀጣ ሸቀጥ ምርት እያደገ ሲሄድ የፊውዳል ገዢዎች በዓይነት ይቀበሉት የነበረውን ክፍያ በይበልጥ በገንዘብ መልክ ይቀበሉ ጀመር። የሸቀጣ ሸቀጥ ምርትና የገንዘብ በሥራ ላይ መዋል መስፋፋት የፊውዳሉን ሥርዓት ብዝበዛ ከማባባሱም ሌላ በአርሶ አደሩ መካከል የነበረውን የሀብት አለመመጣጠን

በአፋጣኝ እያሰፋው ሄደ። አብዛኛው ትንንሽ ገበሬ ሲደኸይ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነው ገበሬዎች ሀብት እያከማቹ ከሌሎች አራጣ አበዳሪዎች ጋር ለትንንሽ ገበሬዎች ገንዘብ በከፍተኛ ወለድ በማበደር ምርታቸውን፣ አንዳንዱም ከዚያም አልፎ መሬታቸውን በዝቅተኛ ዋጋ ሊገዟቸው ችለዋል። የካፒታሊስት ስልተምርት በፊውዳሉ ሥርዓት ማህፀን ውስጥ ቀርጾ ሊይዝና ሊያድግ የቻለው በእንደዚህ ዓይነት ዘዴና ሂደት ነው።

## 3.5 የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት

ለካፒታሊዝም ስልተምርት ማቆጥቆጥ ያስቻለውን ሂደት ካርል ማርክስ "የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት" የሚል ስያሜ ሰጥቶታል። እንደካርል ማርክስ አባባል የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ብዙኃኑን አምራች ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ያለያየ ወይም የምርት መገልገያ ባለቤትነትን ያሳጣ የታሪክ ሂደት ነው። "የመጀመሪያ ደረጃ" የተባለበትም ምክንያት ለካፒታልና ለካፒታሊስት ስልተምርት መከሰት ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ ነው።

የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ሁለት ገጽታዎች ሲኖሩት አንዱ ገጽታው ከሚሸጡት ጉልበት በስተቀር ሌላ ምንም መተዳደሪያ ንብረት የሌላቸው ቁጥራቸው በርከት ያለ ሰዎች መኖር ሲሆን ሌላ ገጽታው ደግሞ መጠኑ ከፍተኛ የሆነና የካፒታሊስት ምርት ድርጅቶችን ለማቋቋም የሚሆን ሀብት በጥቂት ሰዎች እጅ ተከማችቶ መገኘት ነው።

በየጊዜው ከሚጠቀሱ የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ሂደቶች መካከል በእንግሊዝ አገር ከ15ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ለረጅም ጊዜ የተካሄደው ሂደት ይገኛል። ይኸውም የእንግሊዝ አገር የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት የተካሄደው በልዩ ልዩ መንገዶች ነበር።

ዋነኛው መንገድ ግን የፊውዳል ገዢዎች ገበሮቻቸውን ከመሬቶቻቸው በማባረር መሬቶችን ለግጦሽና ለከብት እርባታ በመከለል ለሀብት ክምችት በማዋላቸው ገበሮች ከየቀያቸው ተባርረው ሥራ ፍለጋ ወደከተሞች በመፍለስ የከተሞችን መንገዶች እንዲያጥለቀልቁ ያደረጋቸው ነው። መንግሥትም በአንድ በኩል ቦዘኔነትን የሚቃወም ሕግ አውጥቶ በሌላ በኩል ግን ለመኖሪያ የሚሆን ደመወዝ ወለል ሳይወስን የሥራ ሰዓት እንዲራዘም በመደንገግ ከገጠር ወደ ከተማ የፈለሱትን ሰዎች እጅግ አነስተኛ በሆነ ደመወዝ ተቀጥረው በካፒታሊስቶች እንዲበዘበዙ በማድረግ ለካፒታል ክምችት ዕድገት በጣም ረድቷል።

የአዲስ አህጉራት/አሜሪካ፣ አውስትራሊያ/ መገኘት፣ የቀኝ ግዛት መስፋፋት ያስከተለው ዘረፋ፣ የባሪያ ንግድ፣ መንግሥት በታክስ መልክ ከሰፊው ሕዝብ ሰብስቦ ለበዝባዦች የሰጠው ብድርና የመሳሰሉት ሀብት በጥቂት ሰዎች እጅ እንዲከማች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይህም የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት እንደየአገሩ የታሪክ ሂደት ሊከናወን ቢችልም መሠረታዊ ምንጩ የየህብረተሰቡ አምራች ክፍል መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። በኢትዮጵያም ውስጥ ከመቶ ዓመት ወዲህ የታየው እንቅስቃሴ በመጠኑም ቢሆን ከላይ የተጠቀሰውን ሂደት አንዳንድ ባሕርያት ያንፀባርቃል። የፊውዳል ገዢ መደብ አባላት የገባሮቻቸውን ብዘበዛ ማባባሳቸው አልበቃ ብሏቸው ገባሮቻቸውን ከየቀዬአቸው በመንቀል ሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎችን በማካሄዳቸው ወይንም ለካፒታሊስቶች መሬቶቻቸውን በማከራየታቸው ቀጥራቸው ከፍ ያለ አርሶ አደሮች የዕለት ጉርሳቸውን ፍለጋ ወደየከተማው እንዲፈልሱ ተገደው ነበር። በጥቂት ከተሞች ተከማችተው የነበሩት ቁጥራቸው ውሱን የነበረው መለስተኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች /ለምሳሌ የእህል ወፍጮ፣ የምግብ ዘይት፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የመጠጥ፣ ወዘተ.../ ባለቤቶች መሠረታዊ ፍላጎቶችን እንኳ ለማሟላት የማይበቃ አነስተኛ ደመወዝ በመክፈል ወዝአደሩን በመበዝበዝ ሀብትን አካብተዋል።

## 3.6 የፊውዳሉ ሥርዓት ውድቀት

የፊውዳሊዝምን የብዝበዛ ሥርዓት ለመገርሰስ ዋናው መሠረታዊ ምክንያት የገበሮች ንቅናቄ ነበር። ምንም እንኳ ገባሮች በነጠላ ወይም በኅብረት በፊውዳሉ ሥርዓት ዘመን ከገዢዎቻቸው ጋር በየጊዜው ትግል ያካሄዱ ቢሆኑም ትግሉ እየተካረረ የሄደው በፊውዳሉ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ነበር።

ገባሮች በህብረት ተነስተው የፊውዳሊዝምን የብዝበዛና የጭቆና ቀንበር ከጫንቃቸው ላይ ለማውረድ በየጊዜው ካደረጉቸው ንቅናቄዎች መካከል በአሥራ አራተኛው መቶ ዘመን በፈረንሣይ አገር ያካሄዱትና በታሪክ ውስጥ "ዢከሪ" በመባል የሚታወቀውን ጦርነት መጥቀስ ይቻላል። ሌሎችም ከፍተኛ የገበር ንቅናቄዎች በሌሎችም አገሮች ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር፣ በጀርመን፣ በሩሲያ ተካሂደዋል።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት የአርሶ አደሩ ንቅናቄዎች የፊውዳሊዝምን ሥርዓት መሠረት አናጉት፣ አዳከሙት። የካፒታሊዝም በፊውዳሉ ሥርዓት ውስጥ ማቆጥቆጥም የፊውዳሊዝምን ውድቀት ረድቷል። ፊውዳሊዝም ሊደመሰስና ባዲሱ ሥርዓት ሊተካ የቻለው በውስጡ ያዘላቸው ባንድ በኩል በገባሮችና በፊውዳል ጌቶች በሌላ በኩል በማቆጥቆጥ ላይ በነበረው ቡርዧ መደብና በፊውዳሉ መደብ መካከል ያሉት የመደብ ቅራኔዎች ተካርረው የሰሻለ አብዮት በመፈንዳቱ ነው። በምዕራብ አውሮፓ በወቅቱ ንቃት የነበረውና ተራማጅ የምርት ግንኙነቶችን የሚወክለው የካፒታሊስት መደብ ገባሮችን፣ ወዛደሮችንና ሌሎችንም ተራማጅ የህብረተሰብ ክፍሎች "ነፃነት፣ እኩልነት፣ ወንድማማችነት" በሚለው መፈክር ሥር አሰልፎ ፊውዳል ስለተምርትን በመደምሰስ በራሱ ጥቅም ላይ የተመሠረተውን የካፒታሊስት ስለተምርት መሠረተ፣ የፖለቲካውንም በትረ ሥልጣን ጨበጠ።

በቀደሙ አብዮት ኢትዮጵያ የፊውዳሉ ሥርዓት ተንሰራፍቶ በነበ
ረበት ጊዜ ሁሉ አርሶ አደሩ በፊውዳል ገዢዎች ላይ በነጠላም ሆነ
በህብረት በየጊዜው ማመፁ አልቀረም፡፡ ምንም እንኳን አርሶ አደሩን
በሃይማኖት፣ በጎሣ፣ በቋንቋ... ከፋፍለው ያለቀ ቀሚ ሊገዙት፣ ሊበ
ዘብዙት በሞከሩም ይህንን አሜን ብሉ በደስታ የተቀበለበት ጊዜ አልነበ
ረም፡፡ የሸቀጥ ምርትና የገንዘብ በሥራ ላይ መዋል እየዳበረና በመጠኑም
ቢሆን የአርሶ አደሩም ንቃተሕሊና እያደገ ሲመጣ ትግሉ ተፋፍሟል፣
ለምሳሌ የኢጣልያ ፋሺስቶች ከአገራችን ከተባረሩ በኋላ ያለውን ጊዜ
ብቻ እንኳ ብንወስድ አርሶ አደሮች በየጊዜው የህብረት ክንዳቸውን በጨ
ቋኞቻቸው ላይ በማንሳት ትግላቸውን አካሂደዋል፡፡ በዚህ አንፃር በጎጃም፣
በጎንደር፣ በትግራይ፣ በባሌ፣ በሲዳሞ፣/ደራሳ/ እና በሌሎችም ክፍለ ተ
ሀገር የተደረጉ ንቅናቄዎችን ለመጥቀስ ይቻላል፡፡ አብዮቱ የካቲት
1966 እንደፈነዳም አርሶ አደሩ ከቀሩት ጭቁን የህብረተሰቡ አካሎች
ጋር በመሰለፍ የፊውዳሉን ሥርዓት ሊገረስሰው ችሏል፡፡ አብዮታችን ካጎናጸ
ፈን ዐበይ ድሎች አንዱ የሆነው የመሬት ይዞታ ለውጥ በመሬት ባለቤትነት
ላይ የተመሠረተ የሰው በሰው መበዝበዝ እንዲያበቃና መሬት ለአራሹ እንዲ
ሆን አድርጓል፡፡

በየአገሩ ለፊውዳሉ ሥርዓት ውድቀት የአርሶ አደሩ ንቅናቄ ከፍ
ተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን ሌሎችም ምክንያቶች አሉ፡፡ ቡርዧው፣
ንዑስ ከበርቴው፣ ወዛደሩና ሌሎችም ያካሄዱት ትግል ወሳኝነት ነበረው፡፡
ከዚሁ የሚመነጨው ሌላው ምክንያት ደግሞ የፊውዳሉ ሥርዓት የምርት ግን
ኙነት የምርት ኃይሎችን ጠፍሮ በመያዝ ምርት እንዲዳበር ለማድረግ አለ
መቻሉ ነው፡፡ እርግጥ ነው የፊውዳሉ ሥርዓት በተመሠረተበት ወቅት ከባ
ሪያው ሥርዓት ጋር ሲነፃፀር ተራማጅ ስለነበር አዲስ ያስተራረስ ዘዴ
በሥራ ላይ እንዲውልና በጠቅላላውም ምርታማነት ከፍ እንዲል ለማድረግ

ችሎ ነበር ። ሆኖም በተለይ በፊውዳል ዘመን ወደመጨረሻው ክፍል ላይ የሥራና የመሬት ምርታማነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ሊቆይ እንዲሁም ሊያሽቆለቁል ቻለ ። በአንድ በኩል አርሶ አደሩ መሬቱ እንዲዳብር የመዋዕለ ንዋይ ወጭዎችን ለማድረግ አቅምም ፍላጎትም አጣ ። እየጠና የሚሄደው ብዝበዛ አርሶአደሩ ከእጅ ወደአፍ የሆነች ኑሮ እንዲኖር አደረገው ። አንዳንድ ገበሬዎች በእርሻ ቦታዎች ላይ የተወሰኑ ማሻሻያዎችን ቢያደርጉም ምርት ቢያድግ በይበልጥ ተጠቃሚዎቹ ባለመሬቶቹ ሆኑ፣ እርሻው በመሻሻሉ ምክንያት ገባሩ ለግል ጥቅሙ ያገኘው የነበረው ምርት እርሻውን ለማሻሻያ ያወጣውን ወጭ እንኳ ሊሸፍንለት አይችልም ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ ያለብዙ ማሻሻያ ለዘመናት የታረሰው መሬት ለምነቱን እያጣ ስለሄደ የመሬቱ ምርታማነት ሊቆረቁዝ ቻለ ።

በፊውዳሊዝም ስርዓት መደምደሚያ ክፍለ ዘመን ገባሩ ትግሉን ከማፋፋሙና ምርትንና ምርታማነትን የማሳደግ ፍላጎት እየጠፋ ከመሄዱ ጋር የግል ንብረት ባለቤትነት እየዳበረ፣ በጥቂት ሰዎችም እጅ እየተከማቸ ሄደ ። የምርት መገልገያዎች በጥቂት ሰዎች እጅ እየተከማቹ መሄዳቸው ለሸቀጥ ምርት መዳበር አመቺ ሁኔታን ፈጠረለት ። ብዙኃኑ ትንንሽ አምራቹና ገባር የነበሩ ግለሰቦችም ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት እየተላቀቁ ለመኖር ጉልበታቸውን ከመሸጥ ሌላ ምንም መንገድ እያጡ ሄዱ ። በዚሁ ከፊውዳሊዝም ወደካፒታሊዝም ሽግግር ሂደት ውስጥ ሁለት አዲስ መደቦች ተፈጠሩ ። እነዚህም የካፒታሊስት መደብና የወዝአደሩ መደብ ናቸው ። የካፒታሊስት መደብ አባላት ሀብትን አከማችተውና የምርት መገልገያዎች ባለቤት ሆነው ሠራተኞችን በደመወዝ ቀጥረው የሚያሠሩ ናቸው ። የወዝአደሩ መደብ አባላት ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነት ተላቀቀው ለመኖር ለካፒታሊስቶች ጉልበታቸውን ለመሸጥ የሚገደዱ ናቸው ።

በአጠቃላይ የፊውዳሊዝምን ውድቀት ለማምጣት ተፋፍመው ከነበሩት ዐበይ ቅራኔዎች መካከል በገባሩና በፊውዳል ባለመሬቶ መካከል ያነበረው ቅራኔ፣ በአንድ የፊውዳል ገዥና በሌላው የፊውዳል ገዥ መካከል የነበረው ቅራኔና ፊውዳል ገዥዎች ከነጋዴዎችና በማቆ ጥቆጥ ላይ ካሉ ካፒታሊስቶች ጋር የነበራቸው ቅራኔ ይገኙባቸዋል። ቅገሉ እየተፋፋመ ሲሄድ የፊውዳሊስቶቹ ኃይል መሠረቱ በበለጠ እየተ ናጋ፣ እየጠበበና እየተዳከመ በመሄዱ በቦታው የካፒታሊዝም ስለ ተምርት እየተተካ መጣ።

## አጥር መደምደሚያ

በህብረ ተሰብ ዕድገት ሕገጋት መሠረት የፊውዳሊዝም ስለ ተምርት የባሪያ አሳዳሪ ስለ ተምርትን በመተካት ይፈጠራል፣ ዋናው አንቀስቃሹና በመደቦች መካ ከል የሚፈጠረውም ግንኙነት በመሬት ላይ ያተከረ ነው። ሆኖም በአንዳንድ የታ ሪክ አጋጣሚዎች ምክንያት ፊውዳሊዝም የባሪያ አሳዳሪ ስለ ተምርት ባልዳበረ በት ህብረ ተሰብ ውስጥ ለመጣ ይችላል። የፊውዳሊስቶች የመሬት የግል ባለቤትነትና በገባሮች ላይ ያላቸው ከፊል ባለቤትነት ለፊውዳል ህብረ ተሰብ የምርት ግንኙነት መሠረቶች ናቸው። ገባሮች ለፊውዳሉ ሥርዓት የገዢ መደብ አባላት በቀጥታ ጉልበታቸውን፣ እንዲሁም የሥራቸው ውጤት የሆነውን ምርታ ቸውንና ገንዘባቸውን የማስበዝበዝ ግዳጅ ነበረባቸው። ይህም ገባሮች መውጣት የነበረባቸው ግዳጅ ባሮች ከተፈጸመባቸው ጥቃና ብዝበዛ አብዛኛውን ጊዜ ያነሰ አልነበረም። ሆኖም ገባሩ የሚያርሰውን መሬትና አንዳንድ የማምረቻ መሣሪያዎችን በግሉ ስለሚይዝ፣ እንዲሁም ከባሪያው ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ነፃነት ስለ ነበረውና እንዲሠራም ብዙ ግዳጅ ስላል ነበረበት የጉልበቱንና የመሬቱን ምርታማነት የማሳደግ ፍላጎቱ የተሻለ ነበር።

በፊውዳሉ ዘመን እርሻ ዋነኛው የኢኮኖሚ መስክ ስለነበር ዋንኛው ተበዝባዥ አርሶ አደሩ ነበር። ሆኖም ለህብረተሰቡ፣ በተለይም ለፊውዳል ሥርዓቱ ገዢ መደብ አባላት ልዩ ልዩ የዕደ ጥበባት ምርቶችን የሚያቀርቡ ባለሙያዎች ኃብታቸውን በነፃ ወይንም በአነስተኛ ክፍያ ለፊውዳል ገዢ መደብ አባላት እንዲያስበዘብዙ ይገደዱ ነበር።

በፊውዳሉ ዘመን በአብዛኛው ምርት ያገለገለ የነበረው ለለውጥ ሳይሆን የፍጆታ ፍላጎትን በቀጥታ ለማርካት ነበር። ገባሮች ለፊውዳሉ ገዢ መደብ አባላትና ለጭፍሮቻቸው፣ እንዲሁም ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ፍጆታ የሚሆን ምርት ማምረት ነበረባቸው። ሆኖም የገባሮች የሥራ ውጤት ለገዢው መደብ አባላት መገደሳቀቂያ ሲሆን የነሱ ኑሮ ግን ከእጅ ወደአፍ ነበር።

የሸቀጣ ሸቀጥ ምርት እየዳበረ ሲሄድ አብዛኛው ገባሮችና ዕደ ጥበባት ባለሙያዎች የበለጠ እየደኸዩ፣ ከምርት መገልገያዎች ባለቤትነትም ፈጽመው እየተላቀቁ ሄዱ። በአንፃሩም እንደትልልቅ ባለመሬቶች፣ ትልልቅ ነጋዴዎችና አራጣ አበዳሪዎች ያሉ ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑ ሰዎች ሀብትን ለማከማቸት በቁ። ይህም የብዙ ሰዎች ከሚሸጡት ኃብት በስተቀር የሌላ መተዳደሪያ ማጣትና የጥቂት ሰዎች ከፍተኛ ሀብት ማከማቸት ለፊውዳሊዝም የበዘበዘ ሥርዓት በካፒታሊዝም ለመተካት ቅድመ ሁኔታን ፈጠረ። ይህም ቅድመ ሁኔታ የመጀመሪያው ደረጃ የካፒታል ክምችት የሚባለው ነው።

በፊውዳሉ ዘመን የኋለኛ ክፍል የፊውዳሊዝም የምርት ግንኙነቶች፣ የገባሩና የዕደ ጥበባት ባለሙያዎች በተለይ በማደግ ላይ ከነበረው የሸቀጣ ሸቀጥ ፍላጎት ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ምርታማነት ለምርት ኃይሎች ዕድገት በይበልጥ እንቅፋት እየሆኑ ሄዱ። ገባሮች በፊውዳሉ ሥርዓት የገዢ መደብ አባላት ላይ በየ

ሂደው ያደርጉ የነበረውን አመጽ አፈፈሙ። ሆኖም የፊውዳሊዝምን ሥርዓት ለመገርሰስ ለሚደረገው ትግል ካፒታሊስቶች መሪነቱን ያዙ። የፊውዳል ሥርዓትም ሲገረሰስ ካፒታሊስቶች የፖለቲካ ሥልጣን ጨበጡ። የፊውዳል በዝበዛን በካፒታ ሊስት በዝበዛ ለመተካትም ቻሉ።

በቀደሙ አብዮት ኢትዮጵያ የፊውዳል በዝበዛ የተለያዩ ገጽታዎች ይኑሩት እንጂ የፊውዳሊዝም መሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ ሕግ በሥራ ላይ ውሎ ነበር። ይኸውም መሠረታዊ ሕግ የፊውዳል ገዢ መደብ አባላት በጉል ባለቤትነት የያዙትን መሬት ለገባሮች በማከፋፈል ገባሮች የድካማቸውን ፍሬ እንዲያስበዘብዟቸው ማስገደድ ነው። አብዮታችን ፈንድቶ ከተገናጸፍናቸው ዐቢይ ድሎች መካከል መሬት የሰፊው ሕዝብ ንብረት መደረጉ ይገኛል። ይኸውም ለውጥ የፊውዳሉን ሥርዓት የምርት ግን ኙነት መሠረት ሊያፈራርሰው በመቻሉ ለህብረተሰቡ ፈጣን የዕድገት በር ሊከፍት ችሏል።

## ጥያቄዎች

1. የፊውዳል ስል ተምርት ሊፈጠር የሚችለው እንዴት ነው?
2. በፊውዳል ህብረተሰብ ውስጥ መሠረታዊ የሆነው የምርት ግንኙነት የትኛው ነው?
3. በቀደሙ አብዮት ኢትዮጵያ የፊውዳሉ ገዢ መደብ አባላት አርሶ አደሩን የመበዝበዣ ልዩ ልዩ መንገዶች የትኞቹ ነበሩ?
4. የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት ምንድነው? "የመጀመሪያ ደረጃ" የተባለውስ ለምንድነው?
5. በምዕራብ አውሮፓ የፊውዳል ሥርዓት እንዴት ሊገረሰስ ቻለ? በአገራችንስ?

<ins>የሚነበቡ መጻሕፍት</ins>


1. L. LEONTYEV - POLITICAL ECONOMY: A CONDENSED COURSE, PP. 27 - 32.

2. P. NIKITIN- FUNDAMENTALS OF POLITICAL ECONOMY, PP. 25 - 29


3. JOHN EATON - POLITICAL ECONOMY, PP. 15 - 21

4. G.A. KOZLOV(ED.) - POLITICAL ECONOMY: CAPITALISM, PP. 45- 55

5. RICHARD PANKHRUST - AN INTRODUCTION TO THE ECONOMIC HISTORY OF ETHIOPIA FROM EARLY TIMES TO 1800, pp. 175 - 214

6. RICHARD PANKHRUST - ECONOMIC HISTORY OF ETHIOPIA 1800-1935 PP. 135 - 183; 346 - 459; 504 - 544

7. JOHN MARKAKIS - ETHIOPIA ANATOMY OF A TRADITIONAL POLITY, PP.73-140

# የቃላት መግለጫ

1. ፍላጎት = NEED - WANT
2. መሠረታዊ ፍላጎቶች = BASIC NEEDS
3. ጽንሰ ሃሳብ = CONCEPT
4. ንድፈ ሃሳብ = THEORY
5. ሕግጋት = LAWS
6. ነባራዊ = OBJECTIVE
7. ሂደት = PROCESS
8. ክስተት = PHENOMENON
9. ህብረ ተሰብ = SOCIETY
10. ጥንታዊ ጋርዮሽ = PRIMITIVE COMMUNAL
11. ባሪያ አሳዳሪ = SLAVE OWNING
12. ፊውዳል = FEUDAL
13. ካፒታሊስት = CAPITALIST
14. ሶሺያሊስት = SOCIALIST
15. ኮምዩኒስት = COMMUNIST
16. ስልተ ምርት = MODE OF PRODUCTION
17. ሥርዓተ ማኅበር = SOCIO-ECONOMIC FORMATION
18. ሥራ = LABOUR
19. ማምረት = PRODUCTION
20. ምርት = PRODUCT
21. የማምረቻ መሣሪያ = INSTRUMENTS, IMPLEMENTS, TOOLS OF PRODUCTION
22. የሥራ ተገበሮች = OBJECTS OF LABOUR
23. ጥሬ ዕቃዎች = RAW MATERIALS
24. የሥራ መገልገያዎች = MEANS OF LABOUR

25. የሥራ ማከናወኛዎች = INSTRUMENTS OF LABOUR

26. የሥራ ኃይል/ጉልበት/ = LABOUR POWER

27. የምርት ኃይሎች = PRODUCTIVE FORCES

28. የምርት ግንኙነቶች = RELATIONS OF PRODUCTION

29. የግል ይዞታ = PRIVATE POSSESSION

30. የግል ባለቤትነት = PRIVATE OWNERSHIP

31. የወል ይዞታ = COLLECTIVE POSSESSION

32. የወል ባለቤትነት = COLLECTIVE OWNERSHIP

33. ባሪያ = SLAVE

34. ገባር = SERF

35. ወዝአደር = PROLETARIAT

36. ሠራተኛ = WORKER

37. ካፒታሊስት = CAPITALIST

38. ቡርዧ = BOURGEOIS

39. ማህበራዊ = SOCIAL

40. እሴት = VALUE

41. ትርፍ እሴት = SURPLUS VALUE

42. ሸቀጥ = COMMODITY

43. ገንዘብ = MONEY

44. ይዘት = CONTENT

45. ቅርጽ = FORM

46. ልውውጥ = EXCHANGE

47. ክፍፍል = DISTRIBUTION

48. ፍጆታ = CONSUMPTION

49. መደብ = CLASS

50. መሠረታዊ መደቦች = BASIC CLASSES

51. ቅራኔ = CONTRADICTION

52. ተፃራሪ = ANTAGONISTIC

53. ትግል = STRUGGLE

54. የሥራ ክፍፍል = DIVISION OF LABOUR

55. ማህበራዊ የሥራ ክፍፍል = SOCIAL DIVISION OF LABOUR

56. [illegible]ሯዊ የሥራ ክፍፍል = NATURAL DIVISION OF LABOUR

57. ተፈጥሮ = NATURE

58. ቁስአካል = MATTER

59. ቁሳዊ = MATERIAL

60. ተግባር = ACTIVITY

61. ማህበረሰብ = COMMUNITY

62. እማዊ = MATRIARCHAL

63. አባዊ = PATRIARCHAL

64. ቤተሰብ = FAMILY

65. ቤተዘመድ = EXTENDED FAMILY

66. ጎሣ = CLAN

67. ነገድ = TRIBE

68. ብሔረሰብ = NATIONALITY

69. ብሔር = NATION

70. ዕደጥበብ = HANDICRAFT

71. መዋዕለ ንዋይ = INVESTMENT

72. የመጀመሪያ ደረጃ የካፒታል ክምችት = PRIMITIVE ACCUMULATION OF CAPITAL

proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com

